# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

## የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ/2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ማውጫ ገጽ

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ /ድርሞ/ ........ i
/Executive Summery / ........ i
ክፍል አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
ኤጀንሲው የተቋቋመበት ራዕይ፣ ዓላማ እና ተልዕኮ ........ 2
የኤጀንሲው ራዕይ ........ 2
የኤጀንሲው ዓላማዎች ........ 2
የኤጀንሲው ተልዕኮ ........ 3
የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር ........ 4
የሥራ ዕድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ........ 6
የምግብ ዋስትና ዘርፍ ........ 6
የኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል ........ 7
የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ ........ 7
የኦዲቱ አላማ ........ 8
ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ........ 8
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና የመመዘኛ መስፈርቶች ........ 8
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 9
የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም የአሰራር ሥርዓትመግለጫ /Process description/ ........ 11
የሥራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ ........ 11
የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በተመለከተ ........ 11
የገበያ ልማትና ግብይትን በተመለከተ ........ 11
የከተሞች ሴፍቲኔትን በተመለከተ ........ 12
ክፍል ሁለት ........ 13
የኦዲት ግኝቶች ........ 13
ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 መሠረት የህግ ማዕቀፎች ........ 13
እንዲወጡ እና ተገባራዊ እንዲሆኑ ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ 13
ኤጀንሲው የዘርፉን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት አፈፃፀሙን ........ 15

መከታተሉን በተመለከተ ........ 15
በፌዴራል እና በከተሞች ዘርፉን በተመለከተ ........ 17
የተናበበ አደረጃጀት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ........ 17
በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩና ሥራ ........ 19
ለሌላቸው ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን በተመለከተ ........ 19
ኤጀንሲው አዳዲስና አዋጭ የሆኑ የሥራ ዕድል ........ 24
አማራጮችን ማጥናቱን በተመለከተ ........ 24
የአንድ ማዕከል አገልግሎት የአሰጣጥ ........ 27
ስርዓትና ስታንዳርድን በተመለከተ ........ 27
የሥራ ፈላጊዎችን ምዘገባን በተመለከተ ........ 31
ለስራ ዕድል ፈጠራ ሥራ የሚውል ........ 33
የመስሪያና የመሸጫ ቦታን በተመለከተ ........ 33
የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች በቀጣይ እድገት ........ 38
ማስመዝገባቸውን ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 38
የገበያ ትስስርን በተመለከተ፣ ........ 41
ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና ኘሮግራም በስትራቴጂዎች እና መርሃ ግብሮች መሠረት መከናወኑንና መከታተሉን በተመለተ፣ ........ 43
በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን መለየትን በተመለከተ ........ 46
በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ........ 50
የሚውል ሀብት ማሰባበስን በተመለከተ ........ 50
ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና ኘሮጀክቶች መገምገሚያ ሠነድ (Project appraisal Document) ስለመዘጋጀቱና በክልሎች ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 52
በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ ስለመሰጠቱ እና ድጋፍና ክትትል ስለመደረጉ በተመለተ ........ 53
ኤጀንሲው በከተሞች የእርስ በእርስ የልምድ ........ 57
ልውወጥ የጋራ መድረክ መፍጠሩን በተመለከተ፣ ........ 57
ኤጄንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር ........ 58
ስላለው ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ ........ 58

ለከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ........ 60
ሥራዎች የሚሆኑ ግብዓቶች ማሟላታቸውን በተመለተ ........ 60
የሥራ ዘርፎች ፓኬጅን መቅረጽን በተመለተ ........ 63
በከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና በምግብ ዋስትና ........ 64
ዙሪያ ግንዛቤ መፈጠሩን በተመለከተ ........ 64
የኤጀንሲው የስልጠና ድጋፍን በተመለከተ ........ 67
የኤጀንሲው የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ ........ 69
የሪፖርት አላላክና የግብረ መልስ ........ 71
አሰጣጥ ሥርዓትን በተመለከተ ........ 71
**ክፍል ሶስት** ........ 74
መደምደሚያ ........ 74
**ክፍል አራት** ........ 83
የማሻሻያ ሃሣቦች ........ 83
<u>አባሪዎች</u>
አባሪ 1 ........ i
የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር ........ i
አባሪ 2 ........ iii
የሥራ ዕድል ፈጠራ ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት የላቀ ስዕላዊ መግለጫ /High level map ........ iii
የአንድ ማዕከል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት የላቀ ስዕላዊ መግለጫ ........ iv
የገበያ ልማትና ግብይት ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ ደረጃ የሥራ ........ v
ፍሰት ማፕ/High Level Mapping/ ........ v
የከተሞች ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስተባበሪያ የስራ ፍሰት ........ vi
የኑሮ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት የላቀ ስዕላዊ መግለጫ ........ vii
አባሪ 3 ........ vii
መመዘኛ መስፈርቶች ........ viii
አባሪ 4 ........ xii
በ5ቱ የስራ ዘርፎች ለመፍጠር የታቀዳው የስራ ዕድል እና የተፈጠረ የሥራ ዕድል ዝርዝር ማስረጃ ሠንጠረዥ 1 ........ xii

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሠንጠረዥ 2........xvi
የደቡብ ክልል የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሠንጠረዥ 2...xvi
የአማራ ክልል የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሠንጠረዥ 3..xvii
የኦሮሚያ ክልል የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት........xviii
የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሠንጠረዥ 4........xviii
አባሪ 5........ix
በአማራ ክልል የ2009 በጀት ዓመት የመሬት አቀርቦትና አጠቃቀም ሠንጠረዥ 1........ix
ሠንጠረዥ 2........x
በአማራ ክልል የ2010 በጀት ዓመት የመሬት አቀርቦትና አጠቃቀም........x
አባሪ 6........xi
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ10 ክፍለ ከተማች ለምግብ ዋስትና ኘሮግራም /በአከባቢ ልማትና በቀጥታ ድጋፍ/ ተመዝግበው ተጠቃሚ የሆኑ ዜጐች........xi

# የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ /ድርሞ/

## /Executive Summery/

### የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደንብ ቁጥር 374/2008 በተሠጠው ሥልጣን መሠረት የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና አፈጻጸም ውጤት በሚያመጣ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንጻር የአሰራር ስርዓቱ አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ የኦዲት የመመዘኛው መስፈርቶች እና በኦዲቱ የተገኙት ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

- ኤጀንሲው የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ ሥራዎችን ለማፋጠን የሚረዱ የህግ ማቀፎችንና ስትራቴጂዎችን ነድፎ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በማፀድቅ ሲጸድቅም በስራ ላይ በማዋል አፈፃፀሙን ሊከታተል እንደሚገባ በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 ሥልጣን የተሰጠው ቢሆንም፡-
    - ✓ የከተማ ግብርና ዘርፍ የሚመራበት የከተማ ግብርና ፖሊሲ አለመኖሩ፣
    - ✓ የከተማ ግብርና ልማት ስትራቴጂ ፀድቆ ስራ ላይ አለመዋሉ፤
    - ✓ ለከተማ ግብርና የሚሆን መሬት ለረጅም ጊዜ ለመጠቀም የሚያስችል የአሰጣጥ መመሪያ አለመኖሩ፣
    - ✓ የጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ በ2005 ዓ.ም የወጣ ሲሆን እስከ አሁን ማሻሻያ ሳይደረግለት እየተሰራበት የሚገኝ መሆኑ፣
  - ✓ ኤጀንሲው የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ የዘርፉን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት አፈፃፀሙን ሊከታተል እንደሚገባ በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከክልል ከተሞችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር በጋራ አቅዶ እየሠራ የሚገኝ ቢሆንም እቅድና አፈጻጸማቸውን ለመገምገም የተያዘውን መደበኛ የግንኙነት ጊዜ ጠብቆ በመገናኘት በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙትን

ችግሮች በፍጥነት ፈቶ አማራጭ መፍትሔ በማሰቀመጥ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ባለመደረጉ በክክልሎች እና በከተማ አሰተዳደሮች በአምስቱም የስራ ዘርፎች ለስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር በየበጀት አመቱ አቅደው እየሰሩ ቢሆንም ባቀዱት ልክ አለመፈጸማቸውና እቅዳቸውን ሙሉ በሙሉ አለማሳካታቸው፣

- ኤጀንሲው በፌደራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ 001/2009 እንዲሁም በከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ላይ በተገለጸው መሰረት በሁሉም ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች የተናበበ ተቋማዊ አደረጃጀት እስከ ታችኛው እርከን እንዲፈጠር በማደረግ ስትራቴጂውንና የስትራቴጂውን ማስፈፃሚያ ስልቶች በየደረጃው መተግበሩን የሚያረጋግጥ የድጋፍና ክትትል ስርዓት ዘርግቶ አለመስራቱ፣
- ኤጀንሲው በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩ ሥራ ለሌላቸው ዜጐች የሥራ ዕድል ፈጥሮ እራሳቸውን ለማስቻል በሚያደርገው እንቅስቃሴ በዘጠኙ ክልሎችና በሁለት ከተማ አስተዳደሮች ከ2009-2010 በጀት ዓመት የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም በታቀደው ልክ ያልተፈፀመ ከመሆኑም በተጨማሪ ከ2009-2010 በጀት ዓመት በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ አፈፃፀምንና ከፌደራል ኤጀንሲ የተገኘው ዕቅድና አፈፃፀም ከክልሎች ከተገኘው ጋር ሲነፃፀር የሚጣረስ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በስትራቴጂክ ዕቅዱ ላይ በተገለጸው መሰረት አዳዲስና አዋጭ የሆኑ የሥራ ዕድል አማራጮችን በጥናት በመለየት በየዘርፎቻቸው የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በማደረግ አፈጻጸሙን በሚፈለገው ደረጃ ድጋፍና ክትትል ባለማደረጉ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ፀጋዎችን በመለየትና የተለዩትን በተደራጀ አግባብ ምን ያህል ሥራ ፈላጊ ሊሰማራባቸው እንደሚችል በሚያሳይ መልኩ ከማመላከትና ወደ ፈጻሚ የማውረድና በተለዩት የአካባቢ ፀጋዎችም ፈጥኖ ሥራ ፈላጊዎችን ከማሰማራት አንፃር ችግሮች መኖራቸው፣
- ኤጀንሲው በስራቴጂክ ዕቅዱ ላይ በተገለጸው መሰረት በሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳሮች የሚገኙ  የአንድ ማዕከል አገልግሎቶችን ለተገልጋዮቻቸው ሁሉን አቀፍ አግልግሎት መስጠት እንዲያስችላቸው የአሠራርና አገልግሎት አሰጣት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅና በስታንዳርዱ መሠረት መተግበሩን ማረጋገጥ ቢኖርበትም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች የሚገኙ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች

በሰው ኃይልና በግብዓት የተሟሉ ባለመሆናቸው በስታንዳርዱ መስረት ለተግልጋዮቻቸው /ስራ ፈላጊዎች/ የተሟላ አገልግሎት እየሰጡ ካለመሆኑም በላይ በሁሉም ከተሞች በሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተደራሽ አለመሆኑ፣

- ኤጀንሲው ከዩኒቨርስቲዎችና ከቴ/ሙ.ያ ምሩቃንና ሌሎች ሥራ ፈላጊ ዜጐችን በትምህርት ደረጃ፣ በጾታና በዕድሜ ለይቶ መመዝገብ እንዲቻል እና ሥራ እንዲፈጠርላቸው የሚያስችል አሰራር በመዘርጋትና ከፈፃሚዎች ጋር በጋራ ሊያቅድና ለፈፃሚዎች ድጋፍና የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ መስራት ያለበት ቢሆንም በክልል ከተሞች የሚገኙ አብዛኞቹ የአንድ ማዕከል ጣቢያዎች የዩኒቨርስቲዎች፣ የቴክኒክና ሙ.ያ ምሩቃንን እና ሌሎች ሥራ ፈላጊዎችን በተዘጋጀው መዝገብ መሠረት በተሟላ መልኩ ከመመዝገብና የስራ እድል የተፈጠረላቸው እና ያልተፈጠረላቸውን ዜጎች ከመለየት አንጻር ክፍተቶች መኖሩን፣
- በሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች የሥራ ዕድል ለተፈጠረላቸው ዜጐች አገልግሎት የሚውሉ አዳዲስ የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ግንባታ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነው የለማ መሬት በወቅቱና በተፈለገው መጠን አለመዘጋጀቱ እንዲሁም ግንባታቸው በተጠናቀቁ የማምረቻና መሸጫ ሕንጻዎችና ሼዶች ለተጠቃሚዎች ከመተላለፋቸው በፊት አስፈላጊው መሠረተ ልማቶች የተሟላላቸው አለመሆኑ ታውቋል፡፡ ኤጀንሲውም ችግሩን ለመቅረፍ በዕቅድ ቢይዝም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የማሰተካከያ እርምጃ አለመውሰዱ፣
- በኤጀንሲው የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጐች በሚያገኙት ገቢ ቆጠበው እና በሚሠጣቸው ብድር ወደ ኢንተርኘራይዞች ልማት የሥራ ሂደት እስከሚተላለፉ ድረስ ቀጣይነታቸውን የማረጋገጥ ድጋፍና ክትትል ማደረግ ቢጠበቅበትም ኢንተርፐራይዞችን ወደ ሚቀጥለው የስራ ሂደት እስኪተላለፉ ደረስ ከክልሎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፋይናስ አቅራቢ ተቋማት ጋር ጠንካራ ግንኙነት ፈጥሮ ወጥነት ባለው መልኩ እና በሚፈለገው ደረጃ ክትትልና ድጋፍ አለማደረጉ፣
- በኤጀንሲው በፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ ሥራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት አደረጃጀት እና የአደራጃጀትና የአሰራር መመሪያ ላይ በተገለፀው መሠረት የጥቃቅን ኢንተርፐራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ ኢንተርፕራይዞችን

በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ፣ በመደገፍ ከሀገር ውስጥ የገበያ ተስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ዘላቂ በሆነ መልኩ እንዲመቻች ባለመደረጉ፡-

- ✓ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሚገነባው የመሥሪያ ሼድ እና የመሸጫ ሼድ ከክልል ከተሞች ውጭና ለግብይት በማይመች ግልጽ ባለሆነ ቦታ በመሆኑ ሥራ የተፈጠረላቸው ዜጎች ያመረቱትን ምርት ሳይሸጡ ለቀው እንደሚሄዱና ከገጠር እስከ ከተማ ያለው የገበያ ትስስር ሰንሰለትም ሥራ የተፈጠረለትን ዜጋ ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ባለመሆኑ በተፈጠረለት ሥራ ላይ ያለመቆየት ችግር እየተፈጠረ መገኘቱ፣
- ✓ በክልል በሚገኙ ከተሞች የገበያ ዕድሎችን የሚያሳድጉ ባዛርና ኢግዚብሽን አለማካሄድ ችግር መኖሩ፣
- ✓ የኢንተርፕራይዞች የምርት ማሳያና መሸጫ ማዕከል አለመኖሩና የግብዓት አቅርቦት ችግር መኖሩ፣
- ✓ በፌደራልና በክልል በጀት በሚሠሩ ኘሮጀክቶች ትስስር ለመፍጠር የአሠራር ወጥነት አለመኖርን፣
- ✓ የሚፈጠረው የገበያ እድልና የተደራጀ ኢንተርኘራይዞች ቁጥር አለመመጣጠን፣
- ✓ የመንግሥት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎችና ሆስፒታሎች የሚፈጠሩትን ሥራዎች ላይ ኢንተርኘራይዞችን በማሳተፍ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር አለማድረግ፣
- ✓ የስራ እድል የተፈጥሮላቸው ወደ ስራ የገቡ ኢንተርፕራይዞች የሲፒዮና የጨረታ ሰነድ በነፃ የመስጠት ድጋፍ እየተሠራ አለመሆኑ፣
- ✓ በሥራ እድል ፈጠራ ዙሪያ የተደራጁትን ከማበረታታት አንፃር ማለትም ገበያ ፈላጊዎችን ከምርቱ ተጠቃሚ አካል ጋር የማስተዋወቅ ክፍተት መኖሩ፣

- ➢ በኤጀንሲው መቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/20089 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ሊነድፍ፣ መርሃ ግብሮችን ሊያዘጋጅ፤ ሲፈቀድም ለትግበራ ሊያወርድና አፈጻጸሙን መከታተል እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው በአስራ አንድ ከተሞች የህግ ማዕቀፎች እስከታችኛው እርከን ደረስ ወርደው በትክክል መተገርበሩን በሚፈለገው ሁኔታ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙት ችግሮችን ለይቶ በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲደረግባቸው እየሠራ አለመሆኑ፣

- በኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ላይ በተገለፀው መሠረት በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ፡-
    - ✓ በአከባቢ ልማት ስራዎች በአተገባበሩ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍቻ ማኑዋል በወቅቱ ፀድቀው ወደ ሥራ ባለመግባታቸው ስትራቴጂውን ተረድቶ በመሥራት ላይ የሥራ ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን፣
    - ✓ በሁሉም ክልሎችና ከተሞች ልዩ ድጋፍ የሚያሰፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ኑሯቸውን በጎዳና ያደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎችን የተሀድሶ አግልግሎት ማግኘት እንዲችሉ የልየታ ረቂቅ ማኑዋል እና የድርጊት መርሃ-ግብር ረቂቁ ሰነዱ ጸድቆ በስራ ላይ ባለመዋሉ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በልየታ ሰነዱና በመርሃ ግብሩ መስረት በፍጥነት የድጋፉ ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣
    - ✓ በምግብ ዋስትና የታቀፉትን የህብረተሰብ ክፍሎችን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ የሚፈለገውን ያህል በአነሰተኛ ሥራ ላይ ያሉትን ህብረተሰብ ማቀፍ አለማቻሉ፣
    - ✓ በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች ቀጣይነት ባለው መልኩ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ለማረጋገጥ እንዲቻል በአከባቢ ልማት ስራዎች ተግባራዊነታቸው ላይ የሚያገጥሙትን የበጀት እጥረት፣ የአቅም ግንባታ ችግሮች፣ ተጠቃሚዎችን የነጻ የህክምና የጤና አግልግሎት አለማግኘት፣ የልማት መሣሪያና የሴፍቲ መሣሪያዎች በወቅቱ አለመሟላቱ፣
- ኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚውል ሀብት ከህብረተሰቡ፣ ከባለድርሻ አካላትና ከልማት አጋሮች እንዲሰበሰብና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማደረግ ቢጠበቅበትም ኦዲቱ እሰከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ የሀብት ማሰባሰብ እና የማሰተላለፊ እየሰራ አለመሆኑ፣
- በኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያሰችሉ ኘሮጀክቶችን የሚገመግምበት የግምገማ ሠነድ (Project appraisal Document) በማዘጋጀት ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች መላክ ቢኖርበትም አለመላኩ፣

- ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 11፣12 በተቀመጠው መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት የተጋለጡ እና ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ዘርግቶ እየስራ ቢሆንም፡-
  - ✓ ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች በቀጥታ ድጋፍና በአከባቢ ልማት ሥራዎች በማሳተፍ የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ የግብዓት ችግሮች መኖራቸው ለምሳሌ፡-
    - በዘርፉ የተሟላና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ድጋፍ መስጠት የሚችል አመራርና ባለሙያ እጥረት መኖሩ፣
    - በየደረጃው ለዘርፉ ልማት በቂ በጀት አለመመደብ፣
    - በአስፈጻሚ ተቋማትና በየደረጃው በሚገኙ ቢሮዎች በሰው ኃይልና በቁሳቁስ እንዲሁም ለመስክ አገልግሎት የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች አለማሟላት፣
  - ✓ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም በ10 ክፍለ ከተሞችና በተመረጡ 35 ወረዳዎች ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ያሉ ቤተሰቦችን በአካባቢ ልማት እና ማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች በማሳተፍ የምግብ ዋስትና ተጋላጭነትን፣ መቀነስ እገዛ የሚያደርግ አደረጃጀት ፈጥሮ በሁሉም ክፍለ ከተሞች በተሰጣቸው የተጠቃሚነት ኮታ መሠረት በሁለቱም ኘሮግራሞች /በአከባቢ ልማትና በቀጥታ ድጋፍ ኘሮግራም/ ምዝገባ ለማካሄድ በታቀደው መሠረት ከተመዘገቡ 123,918 ቤተሰቦችን ውስጥ 19,132(15%) ተጠቃሚ ሲሆኑ ቀሪ 104,786 ዜጐች ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣
    - የምግብ ዋስትና ፐርግራም አሰመልክቶ በክልልም ሆነ በከተማ ደረጃ ያለው አደረጃጀት ወጥነት የሌለው መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በፌደራል የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ላይ በተገለፀው መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትና የጋራ መድረክ በማዘጋጀት ከተሞች የእርስ በእርስ ልምድ ልውውጥ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ መስራት ቢጠበቅበትም በዘርፉ መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በአሰተዳደርና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የአሰራር ምርጥ ተሞክሮችን በመቀመርና

በማስፋፋት በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለው የልምድ ልውውጥና የመወያየት ልምድ በተሟላ ሁኔታ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ ተገልጋዮች የሚሰጠው አገልግሎት ወጥ እና የተሟላ እንዲሆን በሚያስችል መልኩ በቋሚነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ እየተተገበረ አለመሆኑ፣

- ኤጀንሲው በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 በተገለፀው መሠረት ከዘጠኙ ክልሎችና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ጋር የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስት ሥራ ዕቅድን በጋራ ለመተግበር የስምምነት ሠነድ በመፈራረም አፈፃፀሙን ሊከታተል እንደሚገባ ተልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከክልሎች፣ ከከተማ አስተዳደሮች፣ ከባለድርሻ አካላትና የዘርፉ አጋሮችን የትብብር መስኮችን በመለየት፣ በመደበኛ የዕቅድ ዝግጅትና የአፈፃፀም የግምገማ ግንኙነት ጊዜ ጠብቆ በመገምገም እና የተዘጋጀውን ዕቅድ በታቀደው ልክ በመተግበር ላይ ከፌደራል እስከ ክልል ባሉ ፈፃሚዎች የሥራ ክፍተቶች ያሉባቸው ሲሆን፣ የፌደራሉ ኤጀንሲም ወጥነት እና ተከታታይነት ያለው ድጋፍና ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እያደረገ አለመሆኑን፣
- ኤጀንሲው በፌደራል የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና አፈፃፀም ዙሪያ በአገር አቀፍ ደረጃ መፍትሄ የሚሹ የግብዓት ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለመፍታት ሥርዓት ዘርግቶ በሚጠበቀው ደረጃ ባለመሥራቱ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለዜጐች የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ የሥራ ማነቆ ሆኖ ከመገኘቱም በላይ ችግሩ ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት እና የአደረጃጀትና የአሠራር መመሪያ ላይ በተገለፀው መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሥራ ፈላጊዎች እንደየ ፍላጐታቸውና ችሎታቸው የሚሠማሩበት የሥራ ዘርፎችን ፓኬጅ ቀርጾ ለፈጻሚዎች ቢልክም በተላከው ፓኬጅ መሠረት ስለመሠራቱ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ እየሰራ ባለመሆኑ፡-
    - በኤጀንሲው ፓኬጁን ቀርጾ ወደ ከተሞች እና ወደ ከተማ አስተዳደር ሲያወርድ በከተሞች ያለውን ፀጋ ያገናዘበ አለመሆኑ፣

- የሥራ ዘርፍ ፓኬጁ ሲዘጋጅ በከተሞች ያለውን ፀጋ እንዲካተት በጥናት ያላረጋገጠ መሆኑ፣
- ሥራ ፈላጊዎች የሥራ ዕድል የሚፈጠርላቸው በተማሩትና በፍላጐታቸው ባለመሆኑ በተፈጠረላቸው የሥራ መስክ ላይ ያለመሠማራት ችግር መኖሩ፣

➢ ኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ላይ በተመለከተው መሠረት ከሚዲያ ጋር በመቀናጀት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር፣ የሕዝብ መድረኮች በመፍጠርና የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ላይ  ተከታታይነት ያለው ግንዛቤ መፍጠር ቢጠበቅበትም በሚፈለገው ደረጃ እስከ ታችኛው እርከን ወርዶ የተዛባ አመለካከትን ሊቀይር በሚችል መልኩ  ግንዛቤ አለመፍጠሩ፣

➢ ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 7 በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ የሥራ አመለካከት መቀየር የሚያስች የትምህርት፣ የስነ ልቦናና የክህሎት ሥልጠና  እንዲሰጡ ድጋፍ የማደረግ ኃላፊነት ቢኖረውም በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም ተገልጋዮች በወጡት ስትራቴጂዎችና የህግ ማዕቀፎች ላይ ተከታታይነት ባለው መልኩ በስልጠና  ከማብቃት አንጻር ችግሮች መኖራቸው፣

➢ ኤጀንሲው ከፌደራል እስከ ክልል ባሉ ከተሞች የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የዳታ ቤዝ ልማት ሶፍትዌር አልምቶ ተግባራዊ እንዲሆን እየሰራ አይደለም፣

➢ ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ኘሮግራም አፈፃፀምን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላትና የክልል ከተሞች ወጥ የሆነ እና ወቅቱን የጠበቀ ጥራት ያለው ሪፖርት እንዲልኩ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግና የተላኩ ሪፖርቶችን ገምግሞ በወቅቱ ግብረ-መልስ መስጠት ቢጠበቅበትም ኤጀንሲው እና ክልሎች የጋራ ዕቅድ አቅደው በወቅቱ ካለመላካቸውም በዘለለ በየዕሩብ አመቱ እና በየአመቱ የሚላከው የአፈጻጸም ሪፖርቶች  ጥራት የሌለው መሆኑ፣ እንዲሁም በኤጀንሲው የዕቅድ አፈፃፀም ላይ የተገለፀው እና ከክልሎች የመጣው አፈፃፀም እርስ በርስ የሚጣረስ መሆኑን፣

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የሀገራችን ኢኮኖሚ ፖሊሲ የገጠርና የከተማ ልማት አቀናጅቶና አስተሳስሮ ሁሉን አቀፍ ልማት ማፋጠን እና ለህዝቡ ተደራሽ መሆን እንዲያስችል ተደርጐ የተቀረጸ ነው፡፡ በመሆኑም በገጠር የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ በገበያ የሚመራ ክፍለ-ኢኮኖሚ በመፍጠር ላይ ያተኮረ መሆኑ፣ እንዲሁም በከተሞች ሰፊ መሠረት ያለው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ስትራቴጂን ማሳካት ቁልፍ ሚና አድርጐ በመውሰዱ ከተሞችን የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ማዕከላት በማድረግ ላይ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

2. በተጨማሪም መንግሥት በከተሞች የተንሠራፋውን የሥራ አጥነት ችግር ለማስወገድ ካለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ጀምሮ በርካታ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ሲሆን በተለይም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች የሥራ ዕድል በመፍጠር ድህነትን ከማስወገድ፣ ልማታዊ ባለሀብትን ከማፍራትና ለኢንዱስትሪው ሰፊ መሠረት በመጣል አገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን መሣሪያ ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው፡፡

3. በመጀመሪያው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት የተገኙ አበረታች ውጤቶች ቢኖሩም በዘርፉ የሚታዩ የመልካም አስተዳደርና የኪራይ ሰብሳቢነት አዝማሚያዎች፣ የቅንጅታዊ አሰራርና የማስፈጸም አቅም ክፍተቶች እና በዘርፉ አንቀሳቀሾች የሚስተዋሉ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶች ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ ተልዕኮውን እንዳይወጣ እንዳደረጉት ማስተዋል ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በከተሞች የመስራት አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎች በዘርፉ ልማት ተጠቃሚ አለመሆናቸው ሌላኛው ክፍተት ነው::

4. በመሆኑም በሁለተኛው ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በዘርፉ የተገኙ ውጤቶችን አጠናክሮ ለማስቀጠልና የተስተዋሉ ተግዳሮቶችን በመፍታት መልካም አስተዳደርና ፍትሃዊነትን ማስፈን ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ሆኗል፡፡ ዕቅዱም የሚያሳካቸው በዘርፉ ፈጻሚዎችና አንቀሳቃሾች የሚታየውን የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶችን በመቅረፍ በከተሞች ፀጥቃቅን እና ከማኑፋክቸሪንግ ውጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በመፍጠርና ነባሩን በማጠናከር ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠር እና የመስራት አቅም ያላቸው የድሃ ድሃ

የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በአካባቢ ልማት ስራዎች ማለትም በከተማ አረንጓዴ ልማት፣ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት፣ በደረቅ ቆሻሻ ማሰባሰብና ማስወገድ፣ በመሰረተ-ልማት፣ በከተማ ግብርና እና በሌሎችም የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ስራዎች በማሳተፍ የስራ እድል እንዲፈጠርላቸውና ገቢ እንዲያገኙ፣ ከሚያገኙትም ገቢ ቆጥበው ዘላቂነት ያለው የራሳቸውን ስራ እንዲሰሩ ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም የመስራት አቅም የሌላቸውን በቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ በማድረግ የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ለሴቶች፣ ለወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግር ተጋላጮች ልዩ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡

5. እነዚህን ግቦች ለማሳካት ቀድሞ የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የነበረውን አደረጃጀት በመቀየር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 374/2008 የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀነሲ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ በየደረጃው የተናበበ አደረጃጀት ለመፍጠር ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በቅንጅት የሚሰራ ይሆናል፡፡

6. የፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በአሁኑ ሰዓት ተጠሪነቱ ለከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር ሲሆን በአንድ ዋና ዳይሬክተር፣ በአራት ዘርፎች የዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና በ20 ዳይሬክቶሬቶች ተዋቅሮ በመሥራት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡

## ኤጀንሲው የተቋቋመበት ራዕይ፣ ዓላማ እና ተልዕኮ

### የኤጀንሲው ራዕይ

7. ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ሰፊ ሥራ ዕድል የሚፈጥሩ፣ ለኑሮ አመቺና የነዋሪውን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸውን በአስተማማኝ መሠረት ላይ በመገንባት በ"2017" በግልጽ ማየት፡፡

### የኤጀንሲው ዓላማዎች

8. ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡፡

- የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ መሥራት ለማይችሉ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት እየቻሉ ሥራ

ለሌላቸው እና ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ፣

- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ተወዳዳሪ፣ ቀጣይነት ያለው፣ ለኢንዱስትሪው ልማት ጠንካራ መሠረት የሚጥል እንዲሆን ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን መደገፍና ማስተባበር፣
- በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ በከተማ ግብርና፣ በግንባታ፣ በንግድ እና በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍና በማሳደግ ተወዳዳሪ፣ ቀጣይነት ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ የሥራ ዕድል በከተሞች እንዲፈጠር፣ የነዋሪዎች ገቢ እንዲሻሻል እና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ፣
- የዜጎችን የተመጣጠነ የሥርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

## የኤጀንሲው ተልዕኮ

9. ኤጀንሲው ቀጥሎ በዝርዝር የተመለከቱት ተልዕኮዎች አሉት፡፡

- የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከተሞች ያላቸውን ያልለማ ጉልበት፣ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት በማቀናጀት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት በመንደፍ የሥራ ዕድል ፈጠራውን መሠረት ማስፋፋት፣
- የከተሞችን የምግብ ዋስትናና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ስትራቴጂዎችን መሠረት በማድረግ አገራዊ ልማት ዕቅድ በማዘጋጀት፣ በቤተሰብ ደረጃ የደሀ ድሆችን ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና እጦትን የሚቀይር ኘሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊነታቸውን መከታተል፣
- የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና የድጋፍ ማዕቀፎችን በመቅረጽ፣ የድጋፍ ሰጪ ተቋማትን በፍላጐትና በመረጃ ላይ የተመሠረተ የስልጠና፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት እዲያገኙ ማስተባበር፣
- የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኘሮግራም አፈፃፀም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈና የተጠቃሚዎች መረጃ በአግባቡ የተደራጀ

ሆኖ ፍትሃዊ የሀብት ተጠቃሚነት እንዲኖር ሥርዓት በመዘርጋት የምግብ ዋስትና ልማቱን ማገዝ፣

- የክልል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ተቋማትን መደገፍ እና አቅማቸውን መገንባት፣ የሀገር ውስጥ ገበያ ትስስር ሥራዎችን ማከናወን፣
- የዘርፉን የልማት ችግሮች ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ማከናወን፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መቀመርና ለተጠቃሚዎች በማሠራጨት አፈጻጸሙን መከታተል፣ የሚሉት ናቸው፡፡

## የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

10. ኤጀንሲውን ለማቋቋም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 374/2008 የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡፡ እነዚህም፡-

- የከተሞች የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎችን ለማፋጠን የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
- የልማታዊ ሴፍቲኔት፣ የኑሮ ማሻሻያ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የድጋፍ ማዕቀፎች ይቀርፃል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
- ለከተሞች ምግብ ዋስትና መረጋገጥ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ እና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሔ ይሰጣል፣
- የከተሞች ምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራን የሚደግፉና የሚያስተባብሩ ተቋማት የድጋፍ ማዕቀፎችን በማስፈፀም አቅም ይገነባል፣
- የከተሞች ምግብ ዋስትናና የሥራ ዕድል ፈጠራ ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ የዘርፉን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
- የእሴት ሰንሰለትን እና የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ልማት ፍላጐት መሠረት በማድረግ ለጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ

ኢንተርፕራይዞችን ድጋፍ ሰጪ ተቋማት የሚያቀርቡትን የሥልጠና፣ የፋይናንስ እና የቴክኖሎጂ የምክር አገልግሎት ያስተባብራል፣

- በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ የሥራ አመለካከት መቀየር የሚያስችሉ የትምህርትና ሥልጠና ሥራዎችን በስፋት እንዲሠሩ የሚያግዝ የሕዝብ ንቅናቄ በከተሞች እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፣
- የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር በከተሞች የማህበራዊ ኑሮ ችግርና ጠንቅ እንዲሁም ለሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና ፍልሰት ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን የመከላከልና የተሃድሶ ሥራዎች እንዲሠሩ ያደርጋል፣
- ከተሞችን በየፈርጃቸው ለማወዳደር በሚወጡ የልማትና የመልካም አስተዳደር ምዘና እና ማወዳደሪያ መስፈርቶች ውስጥ የከተሞች ምግብ ዋስትና ጉዳይ እንደ አንድ መስፈርት መካተቱን ይከታተላል፣
- ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ በመደገፍ ከሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል ፣
- በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የሥራ ዕድል ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ ሥራ የሌላቸውን፣ መሥራት የሚችሉና የማይችሉ ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን መረጃ በጥናት በመለየት ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ያሠራጫል፣
- ከድህነት ወለል በታች ላሉት ተጠቃሚዎች የተለየ ፓኬጅ ቀርጾ ወደ ሥራ ያሠማራል በጊዜ ገደብ እንዲመረቁም ያደርጋል፣
- ምርጥ ተሞክሮዎችን በማጥናት በመቀመርና በማስፋፋት የከተሞች ምግብ ዋስትናና የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎችን ይተገብራል፣
- ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የግልና የመንግሥት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን ያስተባብራል፣ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

11. በኤጀንሲው ካሉ የሥራ ክፍሎች ውስጥ የሥራ ዕድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ በቀጥታ ከኦዲት ሥራው ጋር ግኙኝነት ያላቸው ሲሆን፣ የሥራ ዘርፎቹ ተግባርና ኃላፊነት ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

## የሥራ ዕድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ

- የዘርፉን የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ሪፖርት ያዘጋጃል
- ከሚመለከታቸው የዘርፍ ኢንስቲትዩቶች እና ኮርፖሬሽኖች ጋር በመሆን የጋራ እቅድ እንዲዘጋጁ በማድረግ ኢንተርፕሪይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣
- ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሆኑ የሥራ እድል አማራጮችን ይለያል፣ የሥራ እድል ፈጠራን ሥራ ያስተባብራል፣
- የድጋፍ ማዕቀፎች እንዲቀረጹ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣
- የሥራ እድል ፈጠራ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ ያደርጋል፣
- ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት የሚውል ሀገር አቀፍ ስታንዳርድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ኢንተርፕራይዞች በስታንዳርዶች እና በጥራት ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፣
- ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ይለያል፣ የመፍትሔ ሃሣብ ያቀርባል፣ ተስማሚ የሆኑ ፕሮጀክት ፕሮፋይሎች ያዘጋጃል አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡

## የምግብ ዋስትና ዘርፍ

- ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር ህብረተሰቡን ያሳተፈ የዘርፉን ዕቅዶች በማዘጋጀት ለተፈፃሚነቱ የስምምነት ሰነድ ይፈራረማል፣ አፈፃፀሞችን ይከታተላል፣
- በማንኛውም የከተሞች የልማትና ሌሎች ማወዳደሪያ መስፈርቶች ላይ የከተሞችን የሴፍቲኔት ጉዳይ እንደ አንድ መስፈርት መካተቱን ይከታተላል፣
- ከፌደራል እስከ ከተሞች የተናበበ አደረጃጀትና አሠራር ሥርዓቶችን በማዘጋጀት እና አጋርነት በመፍጠር የስትራቴጂው ማስፈጸሚያ ስልቶች እንዲፈፀሙ ያደርጋል፣
- ከሚዲያ ጋር በመቀናጀት፣ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የተለያዩ የሕዝብ መድረኮች፣ ዶክመንተሪ ፊልሞች፣ የህትመት ውጤቶችን በማዘጋጀት በአመጋገብ ባህል መሻሻል፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ በአረንጓዴነት ልማት፣ በከተማ ግብርና የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በታታሪነት የሥራ ባህል ላይ የተለያዩ የሕዝብ

አደረጃጀቶችን በመጠቀም የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ የሕዝብ ንቅናቄዎች እንዲፈጠሩ ይሠራል፣

- ስትራቴጂ፣ የህግ እና የድጋፍ ማዕቀፎች፣ የስልጠና ማንዋሎች ያዘጋጃል፣ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች የስነ ልቦናና የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ተከታታይ የሆነ የአቅም ግንባታ ሥራ እንዲከናወን ያደርጋል፣
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ የሥራ አመለካከት መቀየር የሚያስችሉ የትምህርትና ስልጠና ሥራዎችን በስፋት እንዲሠሩ የሚያግዝ የሕዝብ ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፣

## የኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

12. የፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ አንድ ዋና ዳይሬክተር ያለው ሲሆን በስሩ አራት ዘርፎች አሉት፡፡ እነርሱም የሥራ ዕድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት፣ የምግብ ዋስትና ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት፣ የኮርፖሬት ሀብት ሥራ አመራር ማስተባበሪያ ዘርፍ ጽ/ቤት ሲሆኑ በጠቅላላው 20 ዳይሬክቶሬቶች አሏቸው፡፡ዝርዝሩ በአባሪ 1 ተመልክቷል፡፡

13. ለኤጀንሲው በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ብዛት 358 ሲሆን፣ እስከ ታህሳስ 30/2011 ዓ.ም. በጠቅላላው በሰው ኃይል የተሟላው 248 (69%) ነው፡፡ ቀሪው 110 ወይም 31% በሰው ሀይል ያልተሟላ ወይም ያልተያዘ የስራ መደብ እንደሆነ ከከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የሰው ኃይል ዳይሬክቶሬት ከተሰበሰበ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 3 ተመልክቷል፡፡

## የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ

14. የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና በዕቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን ገቢ የሚያገኘው መንግሥት በሚመድብለት መደበኛ በጀት ሲሆን በ2009፣ በ2010 እና በ2011 እስከ ታህሳስ 30 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 104,504,528.15፣ ብር 64,961,013.70፣ ብር 65,016,285.00 የተመደበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በ2009 ዓ.ም ብር

101,054,625.54(97%)፣ በ2010 ዓ.ም ብር 57,263,198.52 (88%)፣ እና በ2011 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ብር 29,035,999.34(45%) ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ በድምሩ ብር 187,353,823.40 በስራ ላይ አውሏል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

15. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ ኤጀንሲው ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር፣ የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ መደረጉን ለመገምገም ሲሆን፣ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ በማውጣት ግድፈቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አፈጻጸም ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና የመመዘኛ መስፈርቶች

17. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር አምስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱርም፡-

1. የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ አፈፃፀምን መገምገም፣
2. የከተሞች የምግብ ዋስትና ኘሮግራም አፈፃፀምን መገምገም፣
3. የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣
4. በከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም አፈፃፀም ዙሪያ የትምህርት፣ የስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣ እና

5. በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አፈፃፀም የመረጃ አያያዝና ልውውጥ፣ የሪፖርት አቀራረብና የግብረ መልስ አሰጣጥ ሥርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉት ናቸው፡፡

18. ከላይ የተገለፁትን የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 27 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) የተዘጋጁ ሲሆን፣ በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይም የኤጀንሲው ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

19. ኦዲቱ የተከናወነው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ኦዲቱ የተከናወነው በፌዴራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ከ2008 በጀት ዓመት እስከ 2010 በጀት ዓመት ድረስ ባለው ጊዜ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ዙሪያ የተሠሩ ሥራዎችን በተመለከተ ነው፡፡

20. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በፌዴራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ሲሆን፣ በናሙና ከተመረጡ ከ3 ክልሎች (ከአማራ፣ ከኦሮሚያና ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት) እና ከአንድ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በ7 የዞን ከተሞች እና በየደረጃው ከሚገኙ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ተቋማት በአካል ተገኝቶ የመስክ ምልከታ በማድረግ እንዲሁም ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስ እና በመተንተን መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

21. በዚህም መሠረት በናሙና በተመረጡ የአማራ ክልል የቴክኒክ ሙያና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፣ የኦሮሚያ ክልል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፣ የደቡብ ክልል የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፣ በኦሮሚያ ክልል የአዳማ ከተማ አስተዳደር የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት፣ በደቡብ ክልል በሀዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሥር ለሚገኝ

የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት፣ በደቡብ ክልል ለጋሞጐፋ ዞን የከተማ ልማትና ቤቶች መምሪያ የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ጽ/ቤት፣ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን ደብረ ማርቆስ በቴክኒክ ሙያ ኢንተርፕራይዝ ልማት መምሪያ፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን ለፍኖተሰላም ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት መምሪያ፣ በደቡብ ጎንደር ዞን ደበረ ታቦር ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይች ልማት መምሪያ፣ በደቡብ ወሎ ዞን በደሴ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት መምሪያ የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት፣ በሰሜን ወሎ ዞን ለወልዲያ ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት መምሪያ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልደታ ክፍለ ከተማ ጥቃቀንና አነሰተኛና ኢንተርፕራዝ ልማት ጽ/ቤት እና የካ ክፍለ ከተማ ጥቃቀንና አነስተኛና ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በአካል ተገኝቶ የመስክ ምልከታ በማድረግ እንዲሁም ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በመከለስና የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን የኦዲት ማስረጃዎች ተሰብስቧል፡፡

## የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም የአሰራር ሥርዓትመግለጫ /Process description/

22. በኤጀንሲው ካሉ የሥራ ክፍሎች ውስጥ የሥራ ዕድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ሥር በቀጥታ ከኦዲት አካባቢው ጋር ተያያዥ የሆኑ 5 ዳይሬክቶሬቶች ያሉ ሲሆን፣ የሚያከናውኗቸው ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### የሥራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ

- አዋጪ የሆኑ የሥራ እድል አማራጮችን በጥናት መለየት
- የሥራ ባህል እንዲጐለብት እና እንዲዳብር ቅስቀሳ ማካሄድ ሀገር አቀፍ የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ማካሄድ
- ድጋፍ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እና ስልጠና መስጠት
- የማደራጀት እና የሥራ ትብብር አገልግሎት መስጠት
- የተፈጠሩ የሥራ እድሎችና ትስስሮች ላይ ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ማካሄድ

### የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በተመለከተ

- የማደራጀት እና የሥራ ትብብር አገልግሎት መስጠት
- የተፈጠሩ የሥራ እድሎችና ትስስሮች ላይ ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ማካሄድ
- የግብይት ሂደቱን የማስተካከል ፍላጐት/አቅጣጫ/ መለየት
- ክፍተቶችን ለመለየት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ
- በጥናቱ የተለዩ ችግሮችን ሊሞላ የሚያስችል የመፍትሄ ሃሣብ ማቅረብ
- በሚመለከታቸው አካላት እንዲተገበር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

### የገበያ ልማትና ግብይትን በተመለከተ

- አፈጻጸሙን መገምገምና ግብረ መልስ መስጠት
- በጥናቱ የተለዩ ችግሮችን ሊሞላ የሚያስችል የአሠራር ስርዓት መዘርጋት
- በሚመከታቸው አካላት ማስተቸትና ማስጸደቅ
- ግንዛቤ መፍጠር
- በሚመለከታቸው አካላት እንዲተገበር ክትትልና ድገፍ ማድረግ

**የከተሞች ሴፍቲኔትን በተመለከተ**

- ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የድጋፍ ተጠቃማዎችን መለየት
- በየደረጃው የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች አገልግሎት አሰጣጥን ለማጠናከር የሚየስችሉ ተቋማዊ አደረጃጀትና አሠራር መፍጠር
- የስምምነት ሰነድ መፈራረም
- ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ማድረግ
- ኑሮ የሚሻሻልባቸው /ለኑሮ ማሻሻያ የማልሚያ አማራጮችን በጥናት መለየት የድጋፍ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት
- በየደረጃው የኑሮ ማሻሻያ አገልግሎት አሰጣጥን ለማጠናከር የሚያስችሉ ተቋማዊ አደረጃጀትና አሠራር መፍጠር ነው፡፡ የሥራ ፍሰት ስዕላዊ መግለጫ በአባሪ 2 ተመላክቷል፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

**ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 መሠረት የህግ ማዕቀፎች እንዲወጡ እና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረጉን በተመለከተ፤**

23. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ ሥራዎችን ለማፋጠን የሚረዱ የህግ ማዕቀፎችን /ፖሊሲዎች፣ ስታንደርዶች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች፣ ጋይድ ላይኖች፣ የግምገማ ሰነዶች እና ስትራቴጂዎችን/ እንዲወጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

24. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት የከተሞች የሥራ እድል ለሚፈጠርባቸው አምስት ዘርፎች/ ማለትም የጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ የንግድ ዘርፍ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ እና የከተማ ግብርና ዘርፍ/ ማስፈፀሚያነት ከሚያስፈልጉት የህግ ማዕቀፎች ውስጥ የሚከተሉት ማለትም የከተሞች የምግብ ዋስትና ሰትራቴጂ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል መመሪያ ቁጥር 001/2010፣ የመሥሪያና መሸጫ ሼድና የገበያ ማዕከላት የቦታ ዘግጅት ዲዛይን፣ ግንባታ እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 002/210 የፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት እና አደረጃጀት የአሠራር መመሪያ የወጡ ቢሆኑም የከተማ ግብርና ዘርፍ የሚመራበት የከተማ ግብርና ፖሊሲ ያልተዘጋጀ መሆኑንና፣ የከተማ ግብርና ልማት ስትራቴጂ ቢዘጋጅም ፀድቆ ስራ ላይ እንዲውል ባለመደረጉ ምክንያት በከተማ ግብርና ሥራዎች በአነስተኛ ቦታ ዘመናዊ አሠራርና ቴክኖሎጂን በመጠቀም በግልና በተደራጀ መንገድ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠሪያና ገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዳይሰራ ማድረጉን፣

እንዲሁም ለከተማ ግብርና የሚሆን መሬት ለረጅም ጊዜ ለመጠቀም የሚያስችል የአሰጣጥ መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑን፣ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

25. ከዚህ በተጨማሪ የወጡት የህግ ማዕቀፎች ማለትም ፖሊሲዎች፣ ስታንዳርዶች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች፣ ጋይድ ላይኖች እና የግምገማ ሰነዶች በከተሞችና በክልሎች ወጥ በሆነ መልኩ ተግባራዊ አለመደረጋቸውንና ኤጀንሲውም የነዚህን የህግ ማእቀፎች ወጥነት እንዲኖራቸው የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ እንዳላደረገ እንዲሁም የዘርፉ የህግ ማዕቀፎችን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ወቅታዊ በማድረጉ ላይ ኤጀንሲው የሚጠበቅበትን ሥራዎች አለመስራቱ ለምሳሌ የጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ በ2005 ዓ.ም የወጣ ቢሆንም በአፈፃፀም የታዩ ክፍተቶችን በመገምገም እስከ አሁን ማሻሻያ ያልተደረገበት መሆኑን፣ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. ጉዳዩን አስመልክቶ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ መሰረት የህግ ማዕቀፎችም ፀድቀው ወደ ክልል ቢወርዱም በአተገባበር ላይ ክፍተቶች መታየታቸውን፤ ለምሳሌ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት የመሸጫ ሼድ ለሌላ ኢንተርፕራይዝ ከማስተላለፍ አንፃር የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል መመሪያ 001/2010 ዓ.ም መሰረት በማምረቻና መሸጫ ቦታዎች የመቆያ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ኢንተርፕራይዞች በወቅቱ መልቀቅ እንዳለባቸውና ቦታውም ለሚመለከተው ተጠቃሚ መተላለፍ እንዳለበት ቢገልጽም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች መመሪያው በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን ያለመሥራት ችግር መኖሩን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ስላላወጣቸው የህግ ማዕቀፎችና ስላልተሸሻሉት የህግ ማእቀፎች አስመልክቶ ለቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ምላሽ አለመስጠታቸውን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. በመሆኑም ኤጀንሲው በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ያሉትን የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራን አስመልክቶ የሚያስፈልጉ የህግ ማእቀፎች በተሟላ መልኩ አለማውጣቱ እና የወጡ የህግ ማዕቀፎችም እንዲሻሻሉ ተገቢውን ሥራ ባለመሰራቱ እንዲሁም በወጡ የህግ ማእቀፎች ላይ በየጊዜው አፈጻጸማውን በመገምገም፣ ችግሮችን በወቅቱ እንዲሻሻሉ በተሟላ መልኩ ባለመደገፉ እና ባለመከታተሉ በከተሞች የሚፈለገው የሥራ እድል በሚፈለገው ደረጃ እንዳይፈጠር አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## ኤጀንሲው የዘርፉን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ  በማዘጋጀት አፈፃፀሙን መከታተሉን በተመለከተ

28. ለኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ ስራዎችን በተመለከተ የዘርፉን ሀገራዊ የልማት እቅድን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመተባበር ሊያዘጋጅ እና አፈፃፀሙንም ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡

29. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት ኤጀንሲው  ከክልል ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች ጋር የጋራ ዕቅድ አቅዶ እየሠራ ቢሆንም በመደበኛ የግንኙነት ጊዜን መሰረት በማድረግ የዕቅዱን አፈፃፀም በጋራ የማይገመግሙ መሆኑን እና በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙትን ችግሮች በፍጥነት እየፈቱ እና አማራጭ መፍትሔ እያስቀመጡ ከመሄድ አንጻር ክፍተቶች መኖራቸውን እንዲሁም በኤጀንሲው አቅም የማይፈቱትን ችግሮች ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ ላይ ውስንነቶች መኖራቸውን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

30. እንዲሁም በክልሎች ለዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሮ ወደ ሥራ ለማሠማራት ፌደራልና ክልሎች የጋራ ዕቅድ አቅደው ወደ ሥራ ቢገቡም ሥራ አጥ ዜጎችን ከሥራ ዕድል ይፈጠርልኝ ጥያቄ ፍላጎት አኳያ እየተፈጠረ ያለው የሥራ ዕድል ፈጠራ በአምስቱም ዘርፎች /በጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ በንግድ ዘርፍ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ እና ከተማ ግብርና ዘርፍ/ በየበጀት ዓመቱ የሚታየው አፈፃፀም በአብዛኛው ዝቅተኛ በመሆኑ የሥራ ፈላጊውን ፍላጎት የማያሟላ መሆኑን እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራው የብዙ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ሥራ በመሆኑና በሁሉም ባለድርሻ አካላት የእኔ ሥራ ነው ብሎ ያለመሥራት ችግር መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

31. በተጨማሪ ኤጀንሲው  ከክልል ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች ጋር የጋራ ዕቅድ አቅዶ እየሠራ ቢሆንም መደበኛ የግንኙነት ጊዜን መሰረት በማድረግ የዕቅዱን አፈፃፀም በጋራ የማይገመግሙ መሆኑን እና በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙትን ችግሮች በፍጥነት እየፈቱ እና አማራጭ መፍትሔ እያስቀመጡ ከመሄድ አንጻር ክፍተቶቸ መኖራቸውን እንዲሁም በኤጀንሲው አቅም የማይፈቱትን ችግሮች ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ ላይ ውስንነቶች መኖራቸውን ከተከለሰ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለፌደራል ከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች ላቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ በፌደራል ደረጃ ካሉና በሥራ ዕድል ፈጠራ ውስጥ ጉልህ ድርሻ የሚያበረክቱ ተቋማትን በመለየት፣ በጋራ በማቀድና ክንውኑንም በጋራ በመገምገም የሥራ እድል ፈጠራውን ለማሳካት ሥራዎች የተሰሩ ቢሆንም እንዲሁም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የማስተባበር ሥራ ተመሳሳይነት ባለው መልኩ እየተሠራ የሚገኝ ቢሆንም ሁሉም ለሥራ እድል ፈጠራው እኩል ተነሳሽነት አዳብሯል ለማለት እንደማያስብል ገልፀዋል፡፡

33. የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ኤጄንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ቢያቅድም ነገር ግን ከነዚህ አካላት ጋር መደበኛ የግንኙነት ጊዜን በመወሰንና ይሄን መሰረት በማድረግ የዕቅዱን አፈፃፀም በጋራ የማይገመግሙ መሆኑን እና በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙትን ችግሮች በፍጥነት እየፈቱ እና አማራጭ መፍትሔ እያስቀመጡ ከመሄድ አንጻር ክፍተቶቸ መኖራቸውን በኦዲቱ የተረጋገጠ በመሆኑ በኤጄንሲው የሥራ ኃላፊዎች የተሰጠው መልስ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

34. በመሆኑም ኤጄንሲው የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ ሥራዎችን በተመለከተ የዘርፉን ሀገራዊ የልማት እቅድን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመተባበር ያቀደ ቢሆንም ነገር ግን አፈፃፀሙን ከነዚህ አካላት ጋር መደበኛ የግንኙነት ጊዜን በመወሰንና ይሄን መሰረት በማድረግ የዕቅዱን አፈፃፀም በጋራ የማይገመግሙ በመሆኑ እና በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙትን ችግሮች በፍጥነት መፍትሄ ባላመስጠቱ በዘርፉ የሚታቀዱ እቅዶች ውጢታማ እንዳይሆን አድርጓል፡፡

## በፌዴራል እና በከተሞች ዘርፉን በተመለከተ

## የተናበበ አደረጃጀት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

35. ኤጀንሲው ከፌደራል እስከ ከተሞች የተናበበ አደረጃጀትና አሠራር ሥርዓቶችን በማዘጋጀት እና አጋርነት በመፍጠር በኤጀንሲው የፌደራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ 001/2009 ላይ በተጠቀሰው መሰረት እንዲፈጸም ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

36. በኦዲቱ ወቅት የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ከፌደራል እስከ ከተሞች የተናበበ አደረጃጀትና አሰራር ሥርዓቶችን በማዘጋጀት እና አጋርነትን በመፍጠር የስትራቴጂው ማስፈጸሚያ ስልቶች እንዲፈጸሙ መስራት እንዳለበት ይታወቃል፡፡

37. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

- ኤጀንሲው የሥራ ዕድል ፈጠራን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር በሁሉም የክልል ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች የተናበበ ተቋማዊ አደረጃጀት እስከ ታችኛው መዋቅር እንዲፈጠር ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑን
- እንዲሁም ስትራቴጂውንና የስትራቴጂውን ማስፈፃሚያ ስልቶች በየደረጃው መተግበሩን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ዘርግቶ የክትትል ሥራ በመሥራት፣ የማያሠሩ ማነቆዎችን ለይቶ በማውጣት ችግሮች እንዲፈቱ እና ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮችን ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት በማድረግ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ በበቂ መልኩ የማይከታተል መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- እንዲሁም ከፌደራል እስከ ክልል ከተሞች ያሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፈጻሚ አካላት በእኔነት ስሜት ከመሥራት ይልቅ የሥራ እድል ፈጠራ ሥራን እንደ ትርፍ የሥራ ዓይነት የመመልከት ችግር መኖሩ፣
- ኤጀንሲው ወደ ታችኛው መዋቅር ወርዶ በተሟላ ሁኔታ ድጋፍና ክትትል የማያደርግ መሆኑ፣
- በክልል ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች የዘርፉ አደረጃጀት ወጥነት የሌለውና የተበታተነ መሆኑን፣ ይኸውም የዘርፉ አደረጃጀት ራሱን ችሎ ተዋቅሮ መሥራት ሲኖርበት ከሌላ ዘርፍ ጋር ተለጣፊ ሆኖ መደራጀቱ፣ ለምሳሌ የሀዋሣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ከንግድና ኢንዱስትሪ ጋር ተለጣፊ ሆኖ በመደራጀቱና የራሱ በጀት ባለመመደቡ በሥራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ያላስቻላቸው መሆኑና ይህንንም ለፌደራሉ ኤጀንሲና ለክልሉ ኤጀንሲ ማስተካከያ እንዲደረግ በሚፈጠረው መድረክ ሁሉ ቢገልፁም ችግሩ ያልተቀረፈ መሆኑን፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በየደረጃው የተቋቋመው የሥራ ዕድል ፈጠራ ግብረ ኃይል እና ምክር ቤት ተጠናክሮ ተግባሩን ያለመወጣት ችግር መኖሩን፣
- በክልሎች የስራ ዕድል ፈጠራ ሥራ በአንድ ተቋም ተጀምሮ የማይጠናቀቅ በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አጋር አካላትን የሚያስተሳስር የአሰራር ስርዓት በአስገዳጅነት አለመኖሩ፣
- በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ላይ ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እየተሰጠ አለመሆኑና፣ ከአሰራር አንጻር በዘርፉ ላይ ያለመናበብ ችግር መኖሩ…ወዘተ ናቸው፡፡

38. ስለጉዳዩ የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በፌደራል ደረጃ የተቋቋመው ኤጀንሲ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የዘርፉ መዋቅር እንዲናበብ ለማድረግ በኤንጀሲው ድርጅታዊ መዋቅርና የተሰጠው ተልዕኮ ሲሆን፣ የሰው ኃይልን በተመለከተ በክልሎች ከማስተዋወቅ ጀምሮ ለክልል ከፍተኛ

አመራሮች ደብዳቤ በመጻፍ ጭምር (የአማራ ክልል፣ አፋር ክልል እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር) የአደረጃጀት ችግር ስለነበረባቸው እንዲያስተካክሉ ማስደረጋቸውን ገልጸው፤ ነገር ግን ክልሎች በራሳቸው ያስኬደናል ያሉትን የዘርፍ አደረጃጀት የፈጠሩ መሆኑና ከክልል ክልል ልዩነት ያለው ቢሆንም ስራውን ለመስራት እንቅፋት የሆነ አደረጃጀት እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

39. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው ከፌደራል እስከ ከተሞች የተናበበ አደረጃጀትና አሰራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት እና አጋርነት በመፍጠር ስትራቴጂውን እና የስትራቴጂውን ማስፈጸሚያ ስልቶች በተሟላ መልኩ እንዲተገበሩ ለማድረግ በአምስት አመቱ ስትራቴጂክ እቅድ እና በፌደራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ 001/2009 መረት የተጠቀሰ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ በተጨባጭ ባገኛቸው ማስረጃወች መሰረት ኤጄንሲው ከፌዴራል እስከ ከከተሞች የተናበበ አደረጃጀትና አሰራር የሌለው በመሆኑ በኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

40. በመሆኑም ኤጀንሲው ከፌደራል እስከ ከተሞች የተናበበ አደረጃጀትና አሠራር ሥርዓቶችን በማዘጋጀት እና አጋርነት በመፍጠር በኤጀንሲው  የፌደራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ 001/209 ላይ በተጠቀሰው መሰረት እንዲፈጸም ድጋፍና ክትትል ባለማድረጉ ከፌዴራል እስከ ክልል የተናበበ አደረጃጀትና አሰራር እንዳይኖር በማድረግ ዘርፉ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩና ሥራ ለሌላቸው ዜጐች የሥራ ዕድል መፈጠሩን በተመለከተ

41. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ኃላፊነት በተሰጠው መሠረት በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩና ሥራ ለሌላቸው ዜጐች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡

42. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩና ሥራ ለሌላቸው ዜጐች የሥራ ዕድል ፈጥሮ እራሳቸውን ለማስቻል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከክልሎች ጋር በየበጀት ዓመቱ የጋራ እቅድ በማቀድ እየሠራ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. በዘጠኙ ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ከ2009-2010 በጀት ዓመት በአምስቱ የሥራ ዘርፎች ለመፍጠር የታቃደ እና የተፈጠረ የሥራ ዕድልን በተመለከተ በ04/04/2011 ዓ.ም ዝርዝር ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ በቀረበው መሠረት ጥቅል አፈፃፀማቸው ከፍተኛ እንደሆነ ቢያሳይም በየዘርፎቻቸው ሲታይ ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላቸው የሥራ ዘርፎች ያሉ መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ***(በአምስቱ የሥራ ዘርፎች ለመፍጠር የታቃደ የሥራ እድል እና የተፈጠረ የሥራ ዕድል ዝርዝሩ በአባሪ 4 በሠንጠረዥ 1 ላይ ተመልክቷል፡፡)***

44. ይሁን እንጂ ከኤጀንሲው የተሰበሰበው ማስረጃና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች /አማራ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ/ የእቅድና አፈፃፀማቸው ሲነፃፀር ልዩነት የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል፤- ለአብነት፡-

- **በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**
    - ከዚህ ጋር ተያይዞ ከክልልሉ የተገኘው ማስረጃ ከኤጀንሲው ከተሰበሰበው ማስረጃ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ይኸውም ከኤጀንሲው በተሰበሰበው መረጃ ከተማ አስተዳደሩ በ2009 በጀት ዓመት ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ለ206,400 ዕቅድ ይዞ የነበረ ሲሆን፣ ከከተማ አስተዳደሩ የተገኘው መረጃ ግን ለ64,394 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ እንደነበረ ይህም የ142,006 ልዩነት ያለው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የ2010 በጀት ዓመት ሲነፃፀር ከኤጀንሲው የተሰበሰበው ማስረጃ ዕቅድ እና አፈፃፀም ለ161,106 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ አፈፃፀሙ 117,574 ማለትም 72.98% ዜጎች የስራ ዕድል እንደተፈጠረ የሚገልፅ ቢሆንም ከከተማ አስተዳደሩ የተገኘው መረጃ ግን እቅድና አፈፃፀም ደግሞ ለ161,124 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ አፈፃፀሙ ለ117,574 ዜጎች ማለትም 73% የስራ ዕድል እንደተፈጠረ፣

ይኸውም የከተማ አስተዳደሩ መረጃ (ዕቅዱ የ18 በብልጫ ልዩነት ሲያሳይ አፈፃፀሙ እኩል መሆኑን) ማስረጃው ያሳያል፡፡

➢ **የአማራ ክልል**

- ከክልልሉ የተገኘው ማስረጃ ከኤጀንሲው ከተሰበሰበው ማስረጃ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ይኸውም ከኤጀንሲው በተሰበሰበው መረጃ ክልሉ በ2009 በጀት ዓመት ለ250,111 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ የነበረ ሲሆን፣ ከክልሉ የተገኘው መረጃ ግን ለ188,887 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ እንደነበረ መሆኑንና ይህም የ61,224 ልዩነት ያለው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የ2010 በጀት ዓመት ሲነፃፀር ከኤጀንሲው የተሰበሰበው ማስረጃ ዕቅድ እና አፈፃፀም ለ23,545 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ አፈፃፀሙ ለ22,440 ዜጎች ማለትም 95.3.98% የስራ ዕድል እንደተፈጠረ የሚገልፅ ቢሆንም ከክልሉ የተገኘው መረጃ ግን እቅድና አፈፃፀም ደግሞ ለ161,763 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ አፈፃፀሙ ለ115,970 ዜጎች ማለትም 72% የስራ ዕድል እንደተፈጠረ፣ ይኸውም የክልሉ መረጃ (ዕቅዱ የ657 እና አፈፃፀሙ የ93,530) በመብለጥ ልዩነት የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ **የደቡብ ክልል**

- ከክልሉ የተገኘው ማስረጃ ከኤጀንሲው ከተሰበሰበው ማስረጃ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ይኸውም ከኤጀንሲው በተሰበሰበው መረጃ ክልሉ በ2009 በጀት ዓመት ለ237,010 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ የነበረ ሲሆን፣ ከክልሉ የተገኘው መረጃ ግን ለ233,010 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ እንደነበረ መሆኑንና ይህም የ4,000 ልዩነት ያለው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የ2010 በጀት ዓመት ሲነፃፀር ከኤጀንሲው የተሰበሰበው ማስረጃ ዕቅድ እና አፈፃፀም ለ252,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ አፈፃፀሙ ለ182,530 ዜጎች ማለትም 72.43% የስራ ዕድል እንደተፈጠረ የሚገልፅ ቢሆንም ከክልሉ የተገኘው መረጃ ግን እቅድና አፈፃፀም ደግሞ ለ730,400 ዜጎች

የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ አፈፃፀሙ ለ189,743 ዜጎች ማለትም 25.98% የስራ ዕድል እንደተፈጠረ፣ ይኸውም የክልሉ መረጃ (ዕቅዱ የ478,400 እና አፈፃፀሙ የ7,213) በብልጫ ልዩነት የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ **የኦሮሚያ ክልል**

- ከክልልሉ የተገኘው ማስረጃ ከኤጀንሲው ከተሰበሰበው ማስረጃ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ይኸውም ከኤጀንሲው በተሰበሰበው መረጃ ክልሉ በ2009 በጀት ዓመት ለ474,592 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ የነበረ ሲሆን፣ ከክልሉ የተገኘው መረጃ ግን ለ291,799 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ እንደነበረ መሆኑንና ይህም የ182,793 ልዩነት ያለው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የ2010 በጀት ዓመት ሲነፃፀር ከኤጀንሲው የተሰበሰበው ማስረጃ ዕቅድ እና አፈፃፀም ለ362,967 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ አፈፃፀሙ ለ368,171 ዜጎች ማለትም 101.4% የስራ ዕድል እንደተፈጠረ የሚገልፅ ቢሆንም ከክልሉ የተገኘው መረጃ ግን እቅድና አፈፃፀም ደግሞ ለ349,279 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዞ አፈፃፀሙ ለ415,764 ዜጎች ማለትም 119% የስራ ዕድል እንደተፈጠረ፣ ይኸውም የክልሉ መረጃ (ዕቅዱ የ13,688 እና አፈፃፀሙ የ47,593) በብልጫ ልዩነት የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ( ዝርዝሩ በአባሪ 5 ሠንጠረዥ 4 ያይዟል፡፡)

45. በተጨማሪም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ለዜጎች የሥራ እድል ፈጥሮ ወደ ሥራ ለማስገባት በሚደረገው ጥረት የሥራ መስክ በመለየትና ከሚያሠሩ ድርጅቶች ጋር ሥራ ፈላጊዎችን በማገናኘት እየተሠራ ቢሆንም የአሠራር ስርዓቱን ተከትሎ የመሥራት ችግሮች መኖራቸውንና በዚህ ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት የሥራ እድል ፈጠራ ሥራን በስትራቴጂው መሰረት ሁሉም ትኩረት ሰጥተው በቁርጠኝነት እየሠሩ አለመሆኑን፣ የፌደራሉ ኤጀንሲም ይህንን ችግር ለመቅረፍ አልፎ አልፎ በሚያደርገው የሱፐርቪዥን ሥራ እየሠራ ቢሆንም ወጥነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር ለሚደረገው ሱፐርቪዥን የሚሰጠው ግብረ መልስ ወቅታዊነት የሌለው መሆኑን፣ የከተማ አስተዳደሩ የስራ

ኃለፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስና ከተከለሰው በማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. እንዲሁም ሥራ ለሌላቸው ዜጎች በክልሉ በሚገኙ ሰባት ከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና በኢንተርፕራይዞች ልማት ሥራ በየደረጃው የሚገኙ ዘርፉን እንዲመሩና እንዲያስፈፀሙ ኃላፊነት የተሰጣቸው አመራሮችና ፈጻሚዎች ለስትራቴጂው ትኩረት ሰጥቶ በወጥነት ከመተግበር አኳያ ውስንነቶች መኖራቸውን የሥራ ኃላፊዎቹ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስና ከክልሉ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

47. በተመሳሳይ በአማራ ክልል የቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በአምስቱ የእድገት ተኮር ዘርፎች መሠረት ኢንተርፕራይዞች አቋቁሞ የሥራ እድል ለመፍጠር በየበጀት ዓመቱ በእቅድ ይዞ የመሥራት ሁኔታ ቢኖርም በታቀደው ልክ ለመተግበር ቀጥሎ ባሉ የአሠራር ማነቆዎች ግብን ማሳካት አለመቻሉን ከመልሳቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ኃላፊዎቹም ለሥራዎች ማነቆ ናቸው ያሏቸው፡-

- በፌደራል የወጡትን ስትራቴጂዎችና መመሪዎች በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በትክክል መተግበራቸውን የፌደራሉም ሆነ የክልሉ ኤጀንሲው የክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ በሚፈለገው መጠን ድጋፍና ክትትል እየተደረገ ባለመሆኑ፣
- በፌደራልና በክልል የሚወጡ የአሠራር መመሪያዎች ላይ በከተሞች ደረጃ ለሚገኙ ፈፃሚዎች የሚፈለገውን ሥልጠና ስለማይሰጥ ህጉን ተረድቶ በመፈፀም ላይ ክፍተቶች መኖራቸው፣
- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ሠራተኞች ሲቀጠሩ ሥልጠና ሳይሰጥ ቀጥታ ወደ ሥራ የሚሠማሩ መሆኑ፣
- በፌደራል የሚወጡ ህጎች ወቅታዊ አድርጎ ወደ ፈፃሚ በማውረድ ላይ የሚዘገይ መሆኑ፣
- በ5ቱም በዕድገት ተኮር ዘርፎች ላይ ኢንተርፕራይዞች ለመቋቋም የመሠረተ ልማት አቅርቦት አለመሟላት፣ የሼድ አቅርቦት ችግሮች መኖራቸው፣
- የንግድ ፈቃድ፣ የቲን ነበር፣ የብድር አገልግሎቶች አሰጣቶችን በአንድ መስኮት እንዲያልቁ ስታንዳርዱ ቢያዝም በተለያዩ ተቋማት በመሰጠታቸው ለሥራ ፈላጊዎች ምቹ አለመሆኑ፣

- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በሰው ኃይልና በማቴሪያል ባለመሟላቱ፣...ወዘተ የሚስተዋሉ የሥራ ማነቆዎች መሆናቸውን የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስና ከተሰበሰበ ማስረጃወች ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. ስለጉዳዩ የፌደራል ከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለስራ ፈላጊዎች በአምስቱም ዘርፎች የስራ እድል የመፍጠር ሥራ ቢሠራም በሁሉም ዘርፎች፣ ለምሳሌ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እየተፈጠረ ያለው የሥራ ዕድል አመርቂ አለመሆኑን ገልፀው በዚህ ዙሪያ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ መስጠት ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለማረም የወጡ ስትራቴጂ እና የድጋፍ ማዕቀፎች ጸድቀው እየተተገበሩ የሚገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ፡፡

49. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በተጨማሪ ሌሎች ዘርፎችም ለምሳሌ የከተማ ግብርና ዘርፍ፣ የጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ አፈፃፀም የሚታይበት ሁኔታ ያለ ሲሆን፣ የወጡ ስትራቴጂ እና የድጋፍ ማዕቀፎችም ጸድቀው የመተግበር ሁኔታ ቢኖርም የአተገባበር ክፍተቶች ያሉባቸው በመሆኑ መልሳቸውን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

50. በመሆኑም ኤጀንሲው በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩና ሥራ ለሌላቸው ዜጐች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ወጥነት ባለውና ውጤት በሚያመጣ መልኩ የክትትል ሥራ እሰከታችኛው መዋቅር ድረስ ባለመሠራቱ የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው በማደረግ ስራ አጥነትንና ደህነትን በመቅረፍ የሥራ አጥ ዜጐችን ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ለማረጋገጥ የሚደረገውን እንቅስቃሴ የሚፈለገውን ውጤት እንዳያስገኝ አሰተዋጽኦ ሊያደረግ ይቻላል፡፡

## ኤጀንሲው አዳዲስና አዋጭ የሆኑ የሥራ ዕድል አማራጮችን ማጥናቱን በተመለከተ

51. በኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅዱ ላይ በተገለጸው መሰረት አዳዲስና አዋጭ የሆኑ የሥራ ዕድል አማራጮችን በጥናት በመለየት በየዘርፎቻቸው የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በማድረግ አፈጻጸሙን ክትትልና ድጋፍ ሊያደረግ ይገባል፡፡

52. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት ኤጀንሲው አዳዲስና አዋጭ የሆኑ የሥራ ዕድል አማራጮችን በጥናት በመለየት በየዘርፎቻቸው የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ወደ ክልሎች በማውረድ ስርዓት ዘርግቶ እየሰራ ቢሆንም በአፈፃፀም ላይ ግን በርካታ ውስንነቶች እንደነበሩ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡በኦዲቱ የተለዩት ዝርዝር ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- በሀረሪ ክልል በ2010 በጀት ዓመት የዘርፉ ዕቅድ በከተማው ያለውን ዕምቅ አቅም በመለየት እና ለዜጎች የሥራ ዕድል አማራጮችን በጥናት በመለየት በክልሉ ያሉ የስራ ፈላጊዎችን ብዛት ታሳቢ ባደረገ መልኩ በማዘጋጀት የሥራ ፈጠራው ሥራ በሚፈለገው ልክ ለዜጎች ሥራ እድል ከመፍጠር አንጻር ውስንነት ያለበት መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ክልል በሆሎታና በአዳማ ከተሞች በ2010 በጀት ዓመት ለዜጎች የሥራ ዕድል አማራጮችን በጥናት በመለየት በየዘርፎቻቸው የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ለማዘጋጀት ጥረት ቢደረግም በአስፈጻሚና በባለድርሻ አካላት መካከል በነበረው ቅንጅታዊ አሠራር ውስንነት ምክንያት አለመታቀዱን፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 113,000 የአካባቢ ጸጋ የስራ አማራጮችን በጥናት የተለየ መሆኑ እና በከተማ አሰተዳደር ደረጃ 103,000 የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ዕድል ሊፈጥሩባቸው የሚችሉ መደቦች በጥናት የተለየ ቢሆንም በተለዩት ጸጋዎችንና ክፍት የስራ መደቦችን ጥናቱን ወደታች አውርዶ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻርና ሥራ ፈላጊውን ፈጥኖ ወደስራ ከማሰማራት አንጻር ክፍተት መኖሩን፣
- በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ውስጥ በተለያዩ የሥራ መደቦች ለ55,000 ስራ ፈላጊዎች የሚሆኑ ክፍት የስራ መደቦች ሰለመኖራቸው በጥናት የተለየ መሆኑን በማስረጃው ቢጠቀስም

በተለዩት ጺጋዎችንና ክፍት የስራ መደቦች መሰረት ጥናቱን ወደታች ከማወረድና ሥራ ፈላጊውን ፈጥኖ ወደ ስራ ለማሰማራት ክፍተቶች መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

- የደቡብ ክልል በጥናት የተለዩ መስኮችን መሬት ላይ ወርዶ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የሥራ ክፍተቶች መኖራቸውን፤

53. የፌደራል የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ህጐችንና አማራጭ የሥራ ዕድሎችን ወደ ክልል ቢያወርድም በተሟላ መልኩ መተግበራቸውን የክትትል ሥራ የማይሰሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

54. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለዜጐች የሥራ እድል ፈጥሮ ወደ ሥራ ለማስገባት በሚደረገው ጥረት የሥራ መስክ በመለየትና ከሚያሠሩ ድርጅቶች ጋር ሥራ ፈላጊዎችን በማገናኘት እየተሠራ ቢሆንም የአሠራር ስርዓቱን ተከትሎ የመሥራት ችግሮች መኖራቸውንና የፌደራሉ ኤጀንሲ ይህንን ችግር ለመቅረፍም አልፎ አልፎ በሚያደርገው የሱፐርቪዥን ሥራ እየሠራ ቢሆንም ወጥነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር ለሚደረገው ሱፐርቪዥን የሚሰጠው ግብረ መልስ ወቅታዊነት የሌለው መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

55. በአማራ ክልል የደቡብ ጎንደር ዞን ቴክኒክ ሙያ ኢንተርፕራይዝ ልማት መመሪያ ኃላፊዎች ሰለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጺጋዎችን ለመለየትም ሆነ ወደ ሥራ ሲገባ ከስራ ፈላጊ ቁጥርና ፍላጎት ጋር የማይጣጣም መሆኑን አስረድተው ለዚህም ምክንያት የሆነው የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ እና የክልሉ ቢሮ በክልሉ በሚገኙ ዞኖች ምን ያህል ጺጋ ተለይቶ ምን ያህሉ ሥራ ፈላጊ ወደ ተለየለት የስራ መስክ ተሰማርቷል የሚል የድጋፍና ክትትል ሥራዎች እንደማይሠሩ ገልፀዋል፡፡

56. ስለጉዳዩ የፌደራል ከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ላቀረበላቸው ቃለመይቅ እና በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች ለስራ ፈላጊዎች የስራ እድል ሊፈጥሩባቸው የሚችሉትን መስኮች አጥንቶ ሰነዱን በማዘጋጀትና ስልጠና በመስጠት ለትግበራ ማሰራጨቱን ጠቅሰው፣ አዋጭ የስራ ዕድሎችን ጥናት በአስፈጻሚ አካላት እና የስራ

ዕድል በሚፈጠርለት ሥራ ፈላጊም ጭምር የማጥናት ኃላፊነት እንዳለባቸው፣ ይሁን እንጂ በዘርፉ የሥራ ዕድል መፍጠሪያ አማራጮችን ከመለየትና ከማሳወቅ ባለፈ የታዩትን ክፍተቶች በመለየት መፈጠር የሚገባውን ያህል የሥራ እድል አለመፈጠሩን ገልፀዋል፡፡

57. በመሆኑም ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አጋርነትን በመፍጠር አዳዲስና አዋጭ የሆኑ የሥራ ዕድል አማራጮችን በጥናት በመለየት ጥናቱን ወደ ታችኛው መዋቅር እንዲወርድ በማደረግ በተጠናው አማራጭ የሥራ ዘርፎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን በተሟላ መልኩ ድጋፍና ክትትል ባለመደረጉ የስራ ፈላጊወችን ተጠቃሚነት በሚፈለገው ደረጃ እንዳያድግ አሰተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የአንድ ማዕከል አገልግሎት የአሰጣጥ ስርዓትና ስታንዳርድን በተመለከተ

58. በኤጀንሲው በስራቴጂክ ዕቅዱ ላይ በተገለጸው መሰረት በሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳሮች የሚገኙ የአንድ ማዕክል አገልግሎቶችን ለተገልጋዮቻቸው ሁሉን አቀፍ አግልግሎት መስጠት እንዲያስችላቸው የአሠራርና አገልግሎት አሰጣት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅና በስታንዳርዱ መሠረት መተግበሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

59. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት ኤጄንሲው በ2003 ዓ.ም ይሠራበት የነበረውን የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ መመሪያ ቁጥር 001/2003 ዓ.ም በአንድ ማዕክል አገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል መመሪያ 001/2010 ተሻሽሎ እንዲሁም በሚያዚያ 2010 ዓ.ም የአንድ ማዕከል አግልግሎት መስጫ ጣቢያ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ፀድቆ ለክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች ለሚገኙ የአንድ ማዕክል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ለትግበራ እንዲወርድ ቢደረግም ነገር ግን ማዕከላቱ በስታንዳርዱ መሠረት መሥራት የሚያስችላቸውን ተከታተይነት ያለው ድጋፍና ክትትል ኤጄንሲው በሚጠበቅበት

ደረጃ ባለማካሄዱ በአንድ ማዕከል የአገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ በኦዲቱ የተለዩት ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- በትግራይ ክልል እስከ 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ያሉት 108 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ያሉ ሲሆን 40 ማዕከላት በሰው ሀይል ያልተሟላላቸው መሆኑ፣ አምስት ጣቢያዎች ምንም ወንበር፣ ጠረጴዛና ተሽከርካሪ ያልተሟላላቸው መሆኑ፣ 76 ማዕከላት የመስመር ስልክ የሌላቸው መሆኑ፣ 100 ማዕከላት የፎቶ ኮፒ ማሽን የሌላቸው መሆኑ፣ 99 ማዕከላት ፋክስ ተጠቃሚዎች አለመሆናቸው፣

- በኦሮሚያ ክልል እስከ 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ያሉት 650 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ያሉ ሲሆን ከተፈቀደው የሰው ኃይል የተሟላው 30% ብቻ መሆኑ፣ 20 ማዕከል ምንም ዓይነት ግብዓትም ሆነ የሰው ኃይል ያልተሟላላቸው መሆኑ፣ 41 ማዕከላት አንድ የሰው ኃይል ብቻ ያላቸው መሆኑ፣ 71 ማዕከላት በሁለት የሰው ኃይል አገልግሎት አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑ፣ 525 ማዕከላት የመስመር ስልክ ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣ ሁሉም ጣቢያዎች ፋክስ የሌላቸው መሆኑ፣ 413 ማዕከላት ኮምፒዩተር የሌላቸው መሆኑ፣ 556 ማዕከላት የፎቶ ኮፒ ማሽን የማይጠቀሙ መሆኑ፣ 75 ማዕከላት ወንበር፣ 107 ማዕከላት ጠረጴዛ የሌላቸው መሆኑ፣ 620 ማዕከከላት ተሽከርካሪ የሌላቸው መሆኑ፣

- በደቡብ ክልል እስከ 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ 347 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተቋቁመው በሥራ ያሉ ሲሆን፡- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት የሰው ኃይል ማሟላት 75% ለማድረስ ቢታቀድም 49% እና 43% እንደቅደም ተከተላቸው መሆኑ፣ 18 ማዕከላት በአንድ አንድ የሰው ኃይል፣ 22 ማዕከላት በሁለት ሁለት የሰው ኃይል አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉ፣ 301 ማዕከላት መስመር ስልክ ተጠቃሚዎች አለመሆናቸው፣ 239 ማዕከላት የኮምፒዩተር የማይጠቀሙ መሆኑ፣

- የአማራ ክልል፡-287 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተቋቁመው በሥራ ላይ የሚገኙ ሲሆን 73% የሰው ኃይል ያልተሟላላቸ መሆኑ፣ 4 የማዕከል አገልግሎት መስጫ ጠቢያች ምንም ዓይነት ግብዓትና የሰው ኃይል

ያልተሟላቸው በመሆኑ አገልግሎት መስጠት አለመጀመራቸው፣ በክልሉ ከሚገኙ 116 ማዕከላት ኮምፒዩተር ያልተሟላላቸው መሆኑ፣ 185 ማዕከላት ስልክ የሌላቸው መሆኑ፣ 273 ማዕከላት ፋክስ የሌላቸው መሆኑ፣ 37 ማዕከላት ምንም ዓይነት ተሽከርካሪ የሌላቸው መሆኑ፣

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ2008 በጀት መጨረሻ ድረስ 117 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተቋቁመው በሥራ ላይ የሚገኙ ሲሆን ለተገልጋዮች አገልግሎት ለመስጠት የሰው ኃይልና የግብዓት መሟላትን በተመለከተ፡-
  - የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም ካስፈለገባቸው ዓላማዎች አንዱ ተገልዮች አገልግሎቱን ፍለጋ ረጅም ርቀት ሳይጓዙ በአቅራቢያቸው ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ ቢሆንም በአስተዳደሩ የተቋቋሙት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በወረዳ ደረጃ ብቻ መደረጉ ከተደራሽነት አንፃር በቂ አለመሆኑ፣ የማዕከላቱ ባለሙያዎች ለመስክ ሥራ የትራንስፖርት አቅርቦት አለመኖሩ፣ 41 ማዕከላት የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች አለመሆናቸው፣ 38 ማዕከላት የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ አለመሆናቸው፤
  - ከሰው ኃይል አቅርቦት አንፃር በ2 ማዕከላት አንድ የሰው ኃይል ብቻ መኖሩ፣ በ9 ማዕከላት ሁለት የሰው ኃይል እና በ9 ማዕከላት ሶስት የሰው ኃይል ብቻ በመሆኑ፤

60. በተመሳሳይ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ በ3 ክልሎች፣ በ7 ከተሞችና በአንድ ከተማ አስተዳደር ጉዳዩን አስመልክቶ ለሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከተሰበሰበ ማስረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለው፡-
    - የፌደራሉ ኤጀንሲ የአንድ ማዕከላት አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የአገልግሎት ማስፈጸሚያ ስታንዳርድ ለትግበራ ወደ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ቢላክም ተገልጋዮች በስታንዳርዱ መሠረት የአንድ መስኮት አገልግሎት ተደራሽነት ያለውና በተሟላ ሁኔታ እያገኙ አለመሆናቸው፣ ለምሳሌ የንግድ ፍቃድ እና ቲን ነምበር ማውጣት፣ የብድር አግለግሎቶች ማግኘት…ወዘተ/ እንዲሁም ማዕከላቱ የሚፈለገውን አገልግሎት

ለተገልጋዮቻቸው ለመስጠት የሚያስችላቸው የሰው ኃይልና የግብዓት አለማሟላት ችግር እንደነበረባቸው ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

61. በተጨማሪ የስታንዳርዱን ተደራሽነት በተመለከተ በአማራ ክልል ከ2008 ዓ.ም በፊት ይሠራበት የነበረውን የአንድ ማዕከላት አገልግሎት መስጫ ስታንዳርድ ሚያዝያ 2010 ዓ.ም. ማሻሻያ ተደርጐለት በ2011 ዓ.ም. ለትግበራ ወደ ክልሉ 150 ስታንዳርድ ቢላክም በክልሉ ለሚገኙ 271 የአንድ ማዕከላት ተደራሽ ባለመሆኑ ክልሉ አባዝቶ ላልደረሳቸው ማዕከላት ለመላክ የፌደራል ኤጀንሲውን ቢጠይቅም መልስ አለመሰጠቱን ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ መልስ ሰጥተዋል፡፡

62. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡዱኑ ለፌደራሉ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ መሰረት ሰነዱ ለክልሎቹ ታትሞ በኮታ ሲላክላቸው በሶፍት ኮፒ እና በኢሜል ጭምር እንደሚላክና ክልሎች በራሳቸው የሥራ ቋንቋ አባዝተው ለማዕከላቱ መላክ እንደሚገባቸው ገልፀዋል፡፡

63. በተጨማሪም ማዕከላቱ በስታንዳርዱ መሠረት እየሠሩ አለመሆኑን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ላቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የችግሩ ምክንያት በሁሉም ክልል ከተሞችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን አቅም በማሳደግ ከሰው ኃይል ማሟላት ጀምሮ እስከ መሥሪያ የቢሮ ቁሳቁሶች ጉድለቶች ያሉባቸው መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ላይ ገልፀዋል፡፡

64. የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የወጣው ስታንዳርድ በሁሉም ክልሎች በሚገኙ ማዕከላት ደርሶ ተገልጋዮች ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎት እንዲያገኙ እስከ ማዕከላት ወርዶ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግበት የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ መሥራት እንዳለበት መሆኑን በድርጅታዊ መዋቅር ጥናቱ ላይ የተገለፀ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ መልሳቸውን አልተቀበለውም፡፡

65. በመሆኑም ኤጀንሲው ሰነዱን በ2010 ዓ.ም. አሻሽሎ በማፀደቅ ወደ ክልልና ከተማ አስተዳደር ቢያወርድም ተደራሽነቱን እስከ የአንድ ማዕከላት አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች መድረሱን የክትትል ሥራ ባለመሠራቱ ቀድሞ ይሠራበት በነበረው መመሪያ ቁጥር 001/2003 እየሠሩ የሚገኙ መሆኑንና እንዲሁም ኤጀንሲው

የሚጠበቅበትን የድጋፍ ስራ በሚጠበቀው ደረጃ ባለመስራቱ ሁሉም አገልግሎቶች በአንድ መስኮት ለመስጠት የታሰበው አሰራር በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ ባለመሆኑ ተገልጋዮች ለአንግልት፣ ለምልልስ፣ ለተጨማሪ አላስፈላጊ ወጪ ከመዳረጋቸውም በተጨማሪ የስራ ዕድል ፈጠራ ስራ ተጠቃሚ የሚሆኑት ዜጎች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዳያገኙና በፍጥነት ወደ ስራ እንዳይሰማሩ ሊያደረግ ይችላል፡፡

## የሥራ ፈላጊዎችን ምዝገባን በተመለከተ

66. ኤጀንሲው ከዩኒቨርስቲዎችና ከቴ/ሙ.ያ ምሩቃንና ሌሎች ሥራ ፈላጊ ዜጐችን በትምህርት ደረጃ፣ በጾታና በዕድሜ ለይቶ መመዝገብ እንዲቻል እና ሥራ እንዲፈጠርላቸው የሚያስችል አሰራር በመዘርጋትና ከፈፃሚዎች ጋር በጋራ ሊያቅድና ለፈፃሚዎች ድጋፍና የክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃወች መሰረት ኤጀንሲው ከዩኒቨርስቲዎች ከቴ/ሙ.ያ ምሩቃንና ሌሎች ሥራ ፈላጊዎችን በትምህርት ደረጃ፣ በጾታና በዕድሜ ለይቶ በትክክል መመዝገብ እንዲቻል የአሠራር ስርዓት ዘርግቶ እንደሚሠራ በድርጅታዊ መዋቅር ሰነዱ ላይ የተገለፀና ከ9 ክልሎችና ከ2 ከተማ አስተዳደሮች ጋር የጋራ ዕቅድ በማቀድ ወደስራ ቢገባም ነገር ግን በክልል ከተሞች የሚገኙ አብዛኞቹ የአንድ ማዕከል ጣቢያዎች የዩኒቨርስቲዎች፣ የቴክኒክና ሙ.ያ ምሩቃንን እና ሌሎች ሥራ ፈላጊዎችን በተዘጋጀው መዝገብ መሠረት በተሟላ መልኩ ከመመዝገብ አንጻር ኤጄንሲው የሚጠበቅበትን ድጋፍና ክትትል ባለማካሄዱ በአሰራር ላይ ክፍተቶች እንደነበሩ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡በኦዲቱ የተለዩት ዝርዝር ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- በትግራይ ሙኸኒ አንድ ማዕከል በጥናት ለይቷል የተባለው የሥራ ፈላጊ ቁጥር ከተመዘገበው ጋር የማይጣጣም መሆኑ ማለትም በጥናት የተለዩት ሥራ ፈላጊዎች 1772 ሲሆኑ የስም ዝርዝር መመዝገቢያው ላይ የሚያሳየው የ832 ብቻ መሆኑ፣

- በአማራ ደብረ ታቦር፣ በኦሮሚያ ሆለታ፣ በደቡብ ሃዋሣ እና አርባ ምንጭ ከተሞች በታዩ አንድ ማዕከላት በሥራ አጥ መዝገብ ላልተመዘገቡ ሥራ ፈላጊዎች የሥራ ዕድል ተፈጥሮ የተገኘበት ሁኔታ መኖሩን፣

- በክልል ከተሞች የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን እና ያልተፈጠረላቸውን ሥራ ፈላጊ ዜጐች ከስራ አጥ መመዝገቢያ ከመዝገብ ላይ በማቀናነስ በኩል በሁሉም ክልሎችና ከተሞች በሚገኙ የአንድ ማዕከላት ውስንነት የሚታይባቸው መሆኑ፣ ለማሳያ ያህል፡-

  - በሀረሪ ክልል ይኖራል ተብሎ ከሚገመተው የሥራ ፈላጊዎች ብዛት ባነሰ መልኩ የሚመዘግቡ መሆኑን፣
  - አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሩብ ዓመት ለመመዝገብ ከታቀደው 24,166 ሥራ ፈላጊዎች 11,974 (49.5%) መመዝገቡ፣
  - በሀዋሣ ከተማ በምሥራቅ ክፍለ ከተማ አንድ ማዕከል በ2010 በጀት ዓመት ለመመዝገብ ከታቀደው 5,000 ሥራ ፈላጊዎች 847 (17%) ብቻ የተመዘገቡ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም በሥራ ፈላጊ ልየታ እና ምዝገባ ሥራው ላይ ኃላፊነት የተጣለባቸው የወጣቶችና ስፖርት እንዲሁም ሴቶችና ህፃናት አደረጃጀቶች ሥራ ፈላጊው ዜጋ በሥራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ የስነ ልቦና አመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ግንዛቤ የመፍጠር ሚናቸውን ከመወጣት አንጻር ክፍተት ያለበት መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የማስረጃ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. ስለጉዳዩ ለኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ መሰረት የልየታ እና ምዝገባ ጋይድ ላይን አዘጋጅቶ ስራ ፈላጊዎችን የተሟላ መረጃ አመዘጋገብና አደረጃጀትን እንዴት እንደሚፈጸም በተደጋጋሚ በስራ አጥ መዝገብ በመመዝግብ የተጀመረው በማኑዋል (Manual) ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደ ክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ ጉደለቶች የሚታይበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

69. ከዚህ በተጨማሪም የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ መግለጫ በሰጡት መልስ መሰረት በ2010 በጀት ዓመት በበመጀመሪያ ሩብ ዓመት ላይ (በደበረ ታቦር፣ በሆሎታ፣ በሐዋሳ፣ በአርባ ምንጭ) በድጋፍና ክትትል ወቅት በተገኘው መረጃ

መሰረት ለለያቸው ክልሎችና ከተሞች እንዲያሰተካከሉ ግብረ መልስ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

70. የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ይህን አሰመለክቶ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ግብረ መልስ መሰጠቱን ቢገልጹም በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት የማሰተካከያ አርምጃ ሰለመወሰዱ የሚገልጽ ማሰረጃ ባለመቅረቡ በኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

71. በመሆኑም ኤጀንሲው ከዩኒቨርስቲዎችና ከቴ/ሙ/ያ ምሩቃንና ሌሎች ሥራ ፈላጊ ዜጐችን በትምህርት ደረጃ፣ በጾታና በዕድሜ ለይቶ መመዝገብ እንዲቻል እና ሥራ እንዲፈጠርላቸው የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ከፈፃሚወች ጋር በጋራ ቢያቅድም ነገርግን የተዘረጋውን አሰራር አስመልክቶ የሚጠበቅበትን ድጋፍና ክትትል ባለማካሄዱ ምሩቃንን እና ሌሎች ሥራ ፈላጊ ዜጐችን በትክክል እንዳይለዩና እንዳይመዘገቡ በመሆኑ የስራ ፈጠራው እቅድ በተጨባጭ መረጃ እንዳይመሰረት በማድረግ ስራ ፈላጊዎችን ወደ ስራ የማሰገባት ሂደት ውጤታማ እንዳይሆን አድርጐታል፡፡

**ለስራ ዕድል ፈጠራ ሥራ የሚውል**

**የመስሪያና የመሸጫ ቦታን በተመለከተ**

72. ኤጀንሲው በ2009 በጀት ዓመት ዕቅዱ መሠረት የሥራ ዕድል ለተፈጠረላቸው ዜጐች አገልግሎት የሚውሉ አዳዲስ የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ግንባታ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነው የለማ መሬት በወቅቱና በተፈለገው መጠን የተዘጋጀላቸው መሆኑን፤ እንዲሁም ግንባታቸው በተጠናቀቁ የማምረቻና መሸጫ ሕንጻዎችና ሼዶች ለተጠቃሚዎች ከመተላለፋቸው በፊት አስፈላጊው መሠረተ ልማቶች የተሟላላቸው መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡

73. በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ባደረገው የማስረጃ ክለሳ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች ለኢንተርፕራይዞች የሚገነባው የመስሪያና የመሸጫ ሼዶች ግንባታ፣ የለማ መሬት በወቅቱ፣ በተፈለገውና መጠን መዘጋጀቱን እና ግንባታቸው በተጠናቀቁ የማምረቻና መሸጫ ሕንጻዎችና ሼዶች ለተጠቃሚዎች ከመተላለፋቸው በፊት

አስፈላጊውን መሠረተ ልማቶች የተሟላላቸው መሆኑን በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ስታንዳርድ ላይ ተገልጿል፡፡

74. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

- በአንዳንድ ክልሎች (አማራ፣ ደቡብ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ ድሬዳዋና ሀረሪ) የሚገነባው የመሥሪያና የመሸጫ ሼዶች ከፌደራል ኤጀንሲ በወረደው የስታንዳርድ ዲዛይን መሰረት አድርገው ባለመገንባታቸው የመሠረተ ልማት ችግር ያለባቸው መሆኑ፣ እንዲሁም ለአገልግሎት ምቹ ባለመሆናቸው ለአገልግሎት ሳይውሉ በመፍረስ ላይ መሆናቸው፣
- ኢንተርፕራይዞች እንዲገለገሉባቸው የተገነቡ የመሥሪያ ቦታዎችና መሸጫ ሼዶች ለስራ ምቹ በሆነ ቦታ ላይ ባለመገንባታቸውና መሠረተ ልማት ያልተሟላላቸው በመሆኑ ኢንተርፕራይዞች ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ያለሥራ የተቀመጡና የወንጀለኛ መሸሸጊያ በመሆን ወንጀል የሚፈፀምባቸውና በመኖሪያ ቤትነት እየተጠቀሙባቸው መገኘታቸው፣ ክልሎች የመሥሪያ ቦታና ሼድ ለመገንባት የፋይናንስ ችግር ያለባቸው መሆኑ፣…ወዘተ የተስተዋሉ ችግሮች ሲሆኑ በኤጀንሲውም ከክልሎች ጋር በጋራ ችግሩን ለመቅረፍ የተሠራ ሥራ ባለመኖሩ አሁንም እየተስተዋለ ይገኛል፡፡

75. በተጨማሪም ይህንን አስመልክቶ የፌደራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት በ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀሙ ላይ በተገለፀው መሠረት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች እና ለኢንተርፕራይዞች የመሥሪያና መሸጫ ቦታዎች በግንባታ፣ በአቅርቦትና በአጠቃቀም የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ለመፍታት የክትትል ሥራ ቢሠራም አሁንም ችግሮቹ አለመፈታታቸውን ማሰረጃው ያሳያል፡፡ ለአብነት ያህል፡-

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኤሌክትሪክ አቅርቦትን በተመለከተ፡-**

- በከተማ አስተዳደሩ በአጠቃላይ መብራት እንዲገባላቸው ከሚያስፈልጋቸው 527 የመሥሪያና መሸጫ ቦታዎች 4(0.008) ብቻ በመሆኑ የኤሌክትሪክ አቅርቦት የላቸውም በሚያስብል ደረጃ ላይ መሆናቸው፣

**የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

- በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ በአጠቃላይ ውሃ እንዲገባላቸው ከሚያስፈልጋቸው 392 የመሥሪያና መሸጫ ቦታዎች ውስጥ አንድ ብቻ የገባ ቢሆንም በቀሪዎቹ የውሃ አቅርቦት የላቸውም በሚያስብል ደረጃ ላይ መሆናቸውን ማስረጃው ያሳያል፡፡

**በድሬድዋ ከተማ የከተሞች**

- የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በጋራ በቅንጅት መሥራት ባለመቻሉ ለወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠሪያ መሆን የሚችሉ ማዕከላት ቢገነቡም አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ፣

**በአማራ ክልል**

- ለኢንተርፕራይዞች 1,005 ሼዶች የተዘጋጁ ቢሆንም ሁሉም ሼዶች በመብራት ባለመሟላት ምክንያት ወደ ሥራ ያልገቡ መሆኑ፣

**በኦሮሚያ ክልል**

- በ2009 በጀት ዓመት ተጀምረው በ2010 ሩብ ዓመት የተጠናቀቁ ሼዶች 845 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 87 ሼዶች መሠረተ ልማት ያልተሟላላቸው ሲሆን ወደ ሥራ ለማስገባት በዋናነት የመሠረተ ልማት ችግር መኖሩ፣ ኤጀንሲውም እነዚህንም ችግሮች ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ለፈቺ አካል በማሳወቅ እንዲፈቱ በጋራ እየሠራ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

- የመሥሪያ ቦታዎች በማዘጋጃ ቤት አቅም ተገንብተው የሚቀርቡ በመሆናቸውና ከተሞቹም ሲሰሩ በፕላናቸው ውስጥ ለዚህ ተግባር የሚሆኑ ቦታዎችን በማስተር ፕላን ያለማካተት ችግር መኖሩ፣

- በክልል ከተሞች እና ከተማ አሰተዳደሮች የሚገኙ ነባር ኢንተርፕራይዞች የቆይታ ጊዜያቸውን የጨረሱ ኢንተርፕራይዞችን ያለማስወጣትና ለአዲስ

ለሚመሠረቱት ኢንተርፕራይዞች ያለማስተላለፍ ችግር በመኖሩ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውም አመራሮች በዚህ ዙሪያ በታማኝነት አለመሥራት….ወዘተ በማለት መልሰዋል፡፡

76. ከዚሁ ጋር ተያይዞ በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎችና ከተሞች ለኢንተርፕራይዞች የለማ መሬት አዘጋጅቶ ለመገንባት በሚያደርጉት እንቅስቃሴያቸው አፈፃፀማቸው ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑን ከአፈፃፀማቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-

- የደቡብ ክልል በ2009 በጀት ዓመት 56 አዲስ የአንድ ማዕከላትን ለመገንባት አቅዶ በወላይታ በጠቅላላው 10 አንድ ማዕከላትን የገነባ ሲሆን፣ ክንውኑ 17.85% አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑና ቀሪ ማዕከላት 46ቱ ያልተገነባ መሆኑ፣ በ2010 በጀት ዓመት 56 አዲስ የአንድ ማዕከላትን ለመገንባት አቅዶ በጠቅላላው 2 ማዕከላት ብቻ የተገነባ በመሆኑ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑና፣ በበጀት አመቱ 54ቱ ቀሪ ማዕከላት ያልተገነቡ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በ2010 በጀት ዓመት በዚሁ ክልል በኮንስትራክሽን፣ በአገልግሎት፣ ከተማ ግብርና እና በንግድ ዘርፎች ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ቦታ በማዘጋጀትና በማቅረብ በሙሉ አቅማቸው መሥራት እንዲችሉ ድጋፍ ከማድረግ አንፃር በእቅድ ይዞ ቢሠራም አጠቃላይ በአራቱም ዘርፎች ለተሠማሩ ሥራ ፈላጊዎች 5,911,022 ካሬ ሜትር ለማዘጋጀት አቅዶ 3,698,687 ካሬ ሜትር ቦታ በማዘጋጀት ክንውኑ 63% በመሆኑ የዓመቱ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በአማራ ክልል በ2009 በጀት ዓመት ለሼድ ግንባታ የሚሆን 1,141,752 ካ.ሜ የለማ መሬት የተዘጋጀ ቢሆንም ከተዘጋጀው መሬት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው 750,838 (66%) ብቻ መሆኑ፣ ለክላስተር ግንባታ የተዘጋጀ የለማ መሬት 58,096 ካ.ሜ ሲሆን ከተዘጋጀው መሬት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው 18,478 (32%) መሆኑ፣ ለከተማ ግብርና የሚውል የተዘጋጀ የለማ መሬት 4,405,885 ካ.ሜ ሲሆን ከተዘጋጀው መሬት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው 3,114,985 (71%) መሆኑን በአጠቃለይ ከተዘጋጀው የሼድ፣ ለክላስተር እና ለከተማግብርና

5,605,733 የከተማ መሬት ውስጥ 3,884,301 (69%) በመሆኑ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑ፣

- በተጨማሪም በ2009 በጀት ዓመት የሥራ እድል ለተፈጠረላቸው ኢንተርፕራይዞች አገልግሎት የሚውል የተዘጋጀ 17,416 ኮንቴይነሮች መካከል 13,456 ኮንቴይነሮች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን 1,296 ጥቅም ላይ ያልዋልና 2,664 ኮንቴነሮች በህገወጥ የተያዙ መሆናቸውን ከእቅድ አፈፃፀሙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በክልሉ ለሼድ ግንባታ ተፈቅዶ የተዘጋጀ የለማ መሬት 3,064,745 ካ.ሜ ሲሆን ከተዘጋጀው የከተማ መሬት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው 1,211,105 (40%) በመሆኑ ዝቅተኛ አፈፃፀም ማስመዝገቡ፣ ለከተማ ግብርና ተፈቅዶ የዘጋጀ የለማ መሬት 17,277,901 ካ.ሜ ሲሆን ከተዘጋጀው የከተማ መሬት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው 12,700,355 (74%) ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለሼድና ለከተማ ግብርና ከተዘጋጀው 20,342,646 መሬት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው 13,911,460 (68%) በመሆኑ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑን ማስረጃው ሲያሳይ በ2010 በጀት ዓመት ለክላስተር ግንባታ የተዘጋጀ መሬት አለመኖሩ ታውቋል፡፡/የመሬት አቅርቦትና የመሠረተ ልማት መሟላትን በተመለከተ ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ 5 ከሠንጠረዥ 1-2 ተመልክቷል/፡፡

77. ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአማራ ክልል በወልደያ፣ ከተማ ለአንድ ማዕከል ጣቢያዎች የሚያገለግሉ የመሥሪያና የመሸጫ ሼድ ግንባታ የሚካሄድባቸው የለማ መሬት በከተማ አገልግሎት ወይም ማዘጋጃ ቤት ሙሉ በሙሉ ያለማቅረብ ችግር መኖሩ፣ የመስሪያ ቦታዎች ከከተማ የራቁ መሆኑ፣ ለዚሁ ጉዳይ የተገነባው ህንፃ ለታለመለት ዓላማ ሳይውል ለሌላ አገልግሎት እንዲውል መደረጉ፣ ለምሳሌ ከከተማው ወጣ ብሎ የተገነባ የመስሪያ ቦታውን ለመከላከያ አድማ በታኝ ልዩ ኃይል አገልግሎት እንዲውል መደረጉ ታውቋል፡፡

78. ስለጉዳዩ ለኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ እና በነባራዊ መግለጫ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአማራ ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል፣ በድሬደዋ ከተማ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው የመስሪያ ቦታዎችን በተለይም የመብራት ኃይል ችግር ያለባቸው

ሼዶችን ለይቶ በማሳወቅ የዕቅድ አካል እንዲያደረጉ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መሰጠታቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪ ስራው የአንድ ተቋም ስራ ብቻ ሳይሆን የብዙ ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራርን የሚጠይቅና አሰራሩ የላላ በመሆኑ አሁን ላይ ችግሮቹ ጎልቶ እንዲወጡ አደርጎታል በማለት ገልጸዋል፡፡

79. በተጨማሪም የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ መግለጫ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአማራ ክልል በወልዲያ ብቻ ሳይሆን በደባርቅ፣ በእንጅባራ በባህርዳር እና ጎንደር ጨምሮ የአንድ ማዕከል አግልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ከከተማው ውጪ መስራቱንና ለታለመለት ዓላማ ሳይውል ለአድማ በታኝ ልዩ ሀይል አግልግሎት መዋሉን ኤጀንሲው በደሰሳ ጥናት የለያቸውን ክፍተቶች በክትትልና ድጋፍ ወቅት ትክክልና አግባብ አለመሆኑ ለከተማውና ለክልሉ የቢሮ ኃላፊዎች መሰተካከል እንዳለበት በተከታታይ እንዲያውቋቸው ማደረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

80. የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች እንዲቀረፉ ግብረ መልስ መስጠታቸውን ቢገልጹም በተሰጠው ግበረ መልስ መሰረት የማሰተካከያ እርምጃ ሰለመወሰዱ ለኦዲት ቡድኑ ማሰረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

81. በመሆኑም ኤጀንሲው ከላይ የተዘረዘሩ ለስራ እድል ፈጠራ ስራ የሚውሉ የመስሪያና የመሸጫ ቦታዎች ችግር ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ችግር ፈቺ በሆነ መልኩ ቅንጅት ፈጥሮ በሚፈለገው ደረጃ ድጋፍና ክትትል ባለማደረጉ የስራ ዕድል ለሚፈጠረላቸው ዜጎች ወደ ስራ ለማሰማራት እንዳይቻል እና የመስሪያ ቦታ ፍላጎትና አቅርቦት ጥያቄ እንዳይመለስ፣ እንዲሁም የሚገነቡት የመሸጫ እና የመስሪያ ሼዶች ብዙዎቹ ከከተማ ውጭ በመሆናቸው ለገበያ ትስስር ምቹ ባለመሆኑ ኢንተርፕራይዞች ምርቶቻቸውን ሸጠው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አሰተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች በቀጣይ እድገት ማስመዝገባቸውን ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፣

82. በኤጀንሲው የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጐች በሚያገኙት ገቢ ቆጠበው እና በሚሠጣቸው ብድር ወደ ኢንተርኘራይዞች ልማት የሥራ ሂደት እስከሚተላለፉ ድረስ ቀጣይነታቸውን የሚያረጋግጥ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

83. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራሃላፊወች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት ኤጀንሲው የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ኢንተርፕራይዞች የሚያገኙትን ገቢ መቆጠብ ባለባቸው ሁኔታ የማስቆጠብ እንቅስቃሴ ቢያካሂድም ኢንተርፕራይዞችን ወደ ሚቀጥለው የስራ ሂደት እስኪተላለፉ ደረስ ከክልሎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፋይናስ አቅራቢ ተቋማት ጋር ጠንካራ ግንኙነት ፈጥሮ ወጥነት ባለው መልኩ እና በሚፈለገው ደረጃ ክትትልና ድጋፍ እንዳላደረገ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡ ፡በኦዲቱ የተለዩት ዝርዝር ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- አንቀሳቃሾች በውዴታ የቆጠቡትን ገንዘብ በፈለጉበት ጊዜና ወቅት ማውጣት ያለመቻላቸው ለቁጠባው መደበኛ ባንኮችን የሚመርጡ መሆናቸውና ግዴታ ካልሆነ በቀር በአነሰተኛ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለመቆጠብ ፍላጎት አለመኖር፣

- የብድር ዋስትና ፈንድ ስርዓት ቢኖርም የኢንተርፕራይዞች  የቁጠባ ሰርዓቱ የተረጋጋ አለመሆኑ፣

- ለኢንተርኘራይዞች የሚሠራጨው ብድር በታቀደው ልክ አለመፈፀሙና የተሰራጨውን ብድር ወቅቱን ጠብቆ ያለማሰመለስ ችግሮች በመኖራቸው መልሶ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ አዳዲስ  ኢንተርፕራዞች  ለማበደር ማነቆ መሆኑን፣

- ተጠቃሚዎች መደበኛ ብድር ቁጠባ የማይወስዱበትን ዋናው ምክንያት 20 በመቶ የቅድመ ብድር ቁጠባ የሚጠየቅበት ዋስትና ከአቅም በላይ በመሆኑ፣ ለምሳሌ የቤት ካርታ እና የመኪና ሊብሬ  ያለው ሀብት ዋስ  የሚጠየቁ መሆኑ፣

- ኢንተርኘራይዞች ብድር ለማግኘት ሲጠይቁ እስከ ሶስት ወር የሚቆዩበት ሁኔታ መኖሩ…ወዘተ ማነቆዎች  መኖራቸው፤

- ለተበደሩት ገንዘብ የወለድ ምጣኔው መብዛት አቅማቸውን ያላገናዘበ መሆኑ፣

- ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት በቂ የአመለካከት ግንባታ ባለመሠራቱ፣
- የፋይናንስ ተቋሞች ቀልጣፋና ዘመናዊ  አገልግሎት አለመስጠታቸው፣
- ወደ ስራ የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች ሥራቸውን ለመጀመር ወይንም ለማስፋፋት የብድር አቅርቦት የማመቻቸት ሁኔታ ቢኖርም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በታቀደው ልክ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ዜጎች የብድሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየሠሩ አለመሆናቸው፣
- የብድሩ ተጠቃሚ የሆኑት ኢንተርፕራይዞች የሚሰጣቸውን ብድር ለታለመለት ዓላማ ያለማዋል ችግር ከመኖሩም ባሻገር የክልል ፈፃሚዎች ብድሩን ለማስመለስ በሚሠሩ ሥራዎች ላይ የሥራ ክፍተቶች ያሉባቸው መሆኑን ከስራ ኃላፊዎቹ መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. ስለጉዳዩ ለፌደራል ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ መሰረት የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ሞዳሊቲ ያመጣውን ወለድ ዝቅተኛ ከመሆን አንፃር ኢንተርፕራይዞች ለመጠቀም ቢፈልጉም የፋይናንስ የብድር የፍላጎትና የአቅርቦት አለመመጣጠን ችግሮች የሚታዩ መሆኑን፣ እንዲሁም የመደበኛ ብድር የወለድ ምጣኔ ከ12-17 በመቶ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሥራ ፈላጊዮች በተለይም ወጣቱ የብድር ተጠቃሚዎች ያለመሆን ችግር እንደሚስተዋል የገልጹ ሲሆን የተዘዋዋሪ  ብድር ፈንድን በተመለከተ ኃላፊነቱ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር የተሰጠ ቢሆንም የስራ ዕድል ፈጠራ ስራ ሰለሚመለከት  እየስሩ በመሆኑ ኃላፊነቱ በህግ  እንዲሰጣቸው መጠየቃቸውን ገልጸዋል፡፡

85. በመሆኑም ኤጀንሲው የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸው ኢንተርፕራይዝ ለማቋቋም እና ስራ ለማሰጀመር ለስራ ማሰፋፊያ የሚሆን ብደር ሰርጭት የስራ ፈላጊውን ፍላጎትን ሊሞላ በሚያስችል መልኩ ከፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት፣ በየደረጃው ከሚገኙ አሰፈጻሚዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በሚፈለገው ደረጃ ክትትልና ድጋፍ አለማድረጉ የተጠቃሚወችን አቅም ያገናዘበ የብድር አቅርቦት ለኢንተርፕራይዞቹ በበቂ ሁኔታ ብድር እንዲመቻችላቸውና ብድሩን ለተፈለገው ዓላማ እንዲያውሉና የወሰዱትን ብድር በወቅቱ እንዲመልሱ በማስደረግ በአዲስ መልክ  ወደ ዘርፉ ለሚመጡ ስራ ፈላጊዎች ወደ ስራ እንዲሰማሩ የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠር ባለመሠራቱ ምክንያት ኤጀንሲው በስተራቴጂው ያሰቀመጣቸውን ግቦች

እንዳይሳኩ፣ ኢንተርኘራይዞችም ቆጠበው እራሳቸውን እንዳይችሉና ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

## የገበያ ትስስርን በተመለከተ፣

86. በኤጀንሲው በፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ ሥራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት አደረጃጀት እና የአደራጃጀትና የአሰራር መመሪያ ላይ በተገለፀው መሠረት የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ ኢንተርፕራይዞችን በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ፣ በመደገፍ ከሀገር ውስጥ የገበያ ተስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ዘላቂ በሆነ መልኩ ሊያመቻች ይገባል፡፡

87. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት ኤጀንሲው በአዋጁ የተሰጠውን ሃላፊነት በሚጠበቅበት ደረጃ ባለመፈፀሙ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ ኢንተርፕራይዞችን በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ፣ በመደገፍ ከሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ዘላቂ በሆነ መልኩ ከማስቻል አንፃር ጉልህ ችግሮች እንደነበሩ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡በኦዲቱ የተለዩት ዝርዝር ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሚገነባው የመሥሪያ ሼድ እና የመሸጫ ሼድ ከክልል ከተሞች ውጭና ለግብይት በማይመች ግልጽ ባለሆነ ቦታ በመሆኑ ሥራ የተፈጠረላቸው ዜጎች ያመረቱትን ምርት ሳይሸጡ ለቀው እንደሚሄዱና ከገጠር እስከ ከተማ ያለው የገበያ ትስስር ሰንሰለትም ሥራ የተፈጠረለትን ዜጋ ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ባለመሆኑ በተፈጠረለት ሥራ ላይ ያለመቆየት ችግር እየተፈጠረ መገኘቱ፣
- በክልል በሚገኙ ከተሞች የገበያ ዕድሎችን የሚያሳድጉ ባዛርና ኢግዚብሽን አለማካሄድ ችግር መኖሩ፣

- የኢንተርፕራይዞች የምርት ማሳያና መሸጫ ማዕከል አለመኖሩና የግብዓት አቅርቦት ችግር መኖሩ፣
- በፌደራልና በክልል በጀት በሚሠሩ ፕሮጀክቶች ትስስር ለመፍጠር የአሠራር ወጥነት አለመኖርን፣
- የሚፈጠረው የገበያ እድልና የተደራጀ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር አለመመጣጠን፣
- የመንግሥት ተቋማት ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር አለመፍጠር፣
- የመንግሥት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎችና ሆስፒታሎች የሚፈጠሩትን ሥራዎች ላይ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር አለማድረግ፣
- የስራ እድል የተፈጥሮላቸው ወደ ስራ የገቡ ኢንተርፕራይዞች የሲፒዮና የጨረታ ሰነድ በነፃ የመስጠት ድጋፍ እየተሠራ አለመሆኑ፣
- የገበያ ትስስር ባለመኖሩ ወደ ሥራ ገብቶ የስራቸውን ምርቶች በመሸጥ ተጠቃሚ መሆን አለመቻል፣ ለምሳሌ የወልደያ ከተማ ወጣቶች የተፈጠረላቸውን የስራ እድል ተጠቅመው አፓል ለማምረት በማህበር ተደራጅተው ቢያመርቱም የገበያ ትስስር ባለመኖሩ ያመረቱትን የአፓል ምርት በመሸጥ ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣
- በሥራ እድል ፈጠራ ዙሪያ የተደራጁትን ከማበረታታት አንፃር ማለትም ገበያ ፈላጊዎችን ከምርቱ ተጠቃሚ አካል ጋር የማስተዋወቅ ክፍተት መኖሩ፣...ወዘተ ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

88. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ መልስ ኢንተርፕራይዞች በየዘርፋቸው እንዲደራጁ ድጋፍ እንደሚያደረጉ ገልጸው በክልሎችም በንግድና በዘርፍ ማህበራት እና በየራሳቸው ንዑስ ዘርፎችም ለማደራጀት ጥረት የሚደረግ ቢሆንም በመንግስት ድጋፍ የሚሰጣቸው ጥቃቅንና አነስተኛ እና ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በየዘርፍ ተለይተው እንዲደራጁ ለማደረግ የሚታዩ ክፍተቶች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡

89. የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ኢንተርፕራይዞች በህጋዊ መንገድ ተደራጅተው በመሥራት እራሳቸውን ከሥራ አጥነት ማላቀቅ እንዲችሉ የሚያስችል በሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር ማመቻቸት እንዳለበት በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 መሠረት ሥራ አጥ ዜጎች በተፈጠረላቸው የሥራ ዕድል በማህበር እንዲደራጁ እና የገበያ ትስስሩን በማመቻቸት በምርታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ከህግ ውጭ ሆነው የተገኙትን ማህበራትን ከክልሎችና ከተማ አሰተዳሮች ግንዛቤ ፈጥሮ እንዲያስተካክሉ በማድረግና አምርቶ የመጠቀም እንቅስቃሴያቸውን እንዲቀጥሉ የማድረግ ሥራ መሥራት ያለበት በመሆኑ በኤጄንሲው የስራ ሃላፊዎች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

90. በመሆኑም ኤጀንሲው የጥቃቅን ኢንተርፐራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነሰተኛ ኢንተርፐራይዞችን በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ፣ በመደገፍ ዘላቂነት ባለው መልኩ በሀገር ውስጥ የገቢያ እድል ከሚፈጥሩ ተቋማት ጋር ጠንካራ የሆነ ግንኙነት ፈጥሮ በሁሉም ክልሎች እና ከተሞች በሀገር ውስጥ ሚዛናዊና የተደራሽነት ሽፋን ያለው የገቢያ የስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚፈለገው ደረጃ ባለማመቻቸቱ እንዲሁም ኢንተርፕራይችን እርስ በራሳቸው በምርት ውጤቶቻቸው የገቢያ ትስስር ዕድል እንዲፈጠሩና በሀገር ውስጥ ተወዳደሪ እንዲሆኑ የማመቻቸት ስራ በሚፈለገው መልኩ ባለመስራቱ ኢንትርፕራይዞች የኢኮኖሚ የዕድገት ለውጥ እንዳያመጡ ከማደረጉ በላይ ለኢንደስትሪው ልማት ቀጣይነት ጠንካራ መሰረት እንዳይጥሉ ሊያደረግ እና የስራ እድል የተፈጠረላቸው ማህበራት መልስው ለመፈረስ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጠር አሰተዋጾ ሊያደረግ ይችላል፡፡

## ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በስትራቴጂዎች እና መርሃ ግብሮች መሠረት መከናወኑንና መከታተሉን በተመለተ፣

91. በኤጀንሲው መቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/20089 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ሊነድፍ፣ መርሃ ግብሮችን ሊያዘጋጅ፤ ሲፈቀድም ለትግበራ ሊያወርድ፣ እንዲሁም ስትራቴጂው መተግበሩን የሚለኩ የአፈጻጸም መለኪያዎችን አዘጋጅቶ ለከተሞች በማሳወቅ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

92. በኦዲቱ ወቅት የፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ነድፎ መርሃ ግብሮችን በማዘጋጀትና በማፀደቅ ለትግበራ  የምግብ ዋስትና ኘሮግራም ወደ ሚተገበርባቸው አስራ አንድ ከተሞች መላኩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

93. ይሁን እንጂ የተላከው የህግ ማዕቀፎች እስከታችኛው እርከን ደረስ በወረደው መሠረት በትክክል መተገርበሩን ድጋፍና ክትትል በማድረግ በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙት ችግሮችን ለይቶ በማውጣት በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲደረግባቸው እየሠራ አለመሆኑን የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. በተጨማሪም ኤጀንሲው በ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖረት መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ቀድሞ ከተመረጡ 11 ከተሞች  በተጨማሪ በአዲስ መልክ የከተሞች የምግብ ዋስትና ኘሮግራም የሚተገበርባቸውን 44 ከተሞች በፌደራል ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ከተሞችን የመለየት ስራ መስራታቸውን በ2010 በጀት አመት ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ቢጠቀስም ኘሮግራሙ በአዲስ መልክ የሚተገበርባቸው ከተሞች ላይ በኘሮግራሙ አተገባበር ዙሪያ የሚያስፈልገውን የበጀት ምንጭ በመንግሥት ደረጃ ለምን ያህል ከተሞች ማስተግበሪያ እንደሚያስፈልግ ተወስኖ ባለመጽደቁ የልየታ ሥራው ብቻ መፈጽሙን የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ  ለማረጋገጥ ተችሏል፡

95. በተመሳሳይ የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ ባያቸው ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስና ጉዳዩን አስመልክቶ ተሰብስበው ከተከለሱ ማስረጃወች ለማወቅ እንደተቻለው በፌደራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በተመረጡ 11 ከተሞች የምግብ ዋስትና ኘሮግራምን ለመተግበር የወጡ ስትራቴጂዎች እና ማስተግበሪያ ማኑዋሎችን ኘሮግራሙ በሙከራ ወደ ሚተገበርባቸው ከተሞች በላከው መሠረት ተግባራዊ እየተደረገ ቢሆንም ፈፃሚዎች ስትራቴጂዎችንና ማስተግበሪያ ማንዋሎችን

ተጠቅመው በመፈፀም ላይ የሥራ ውስንነቶች እንዳሉ ገልጸው፣ ለዚህም የሥራ ክፍተቶች ምክንያት ናቸው ያሏቸውን ቀጥሎ ተመልክተዋል፡፡

- ኘሮግራሙ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የአመራርና የፈፃሚ የብቃት፣ የክህሎት፣ የአመለካከት ውስንነቶች እንዳይኖሩ በሚፈለገው ደረጃ ለፈፃሚዎች በፌደራልና በክልል ስልጠና አለመሰጠቱ፣
- ኤጀንሲው በምግብ ዋስትና ስትራቴጂና መርሃ ግብሮች መሰረት የምግብ ዋሰትናን አስመልክቶ የሚሰጡ አገልግሎቶች እና ድጋፎች የምግብ ዋስትና ተግባራዊ በሚሆንባቸው ከተሞቹ የፕሮግራሙ ከድህነት ወለል በታች ላሉ ተጠቃሚ በሆኑት ላይ የመጣውን ለውጥ በጥናት አለማረጋገጡ፣
- ኤጀንሲው በስትራቴጂው መሠረት ሥራዎችን መሠራታቸውን ለማረጋገጥ በክልል ደረጃ ከማሳወቅና በጋራ ተናቦ ከመሥራት ይልቅ አልፎ ቀጥታ ወደታች ከሚገኙ ከክልል ከተሞች ቢሮዎችና ፈፃሚ አካላት ጋር አሰራሮችን የመከታተል ሁኔታ በመኖሩ በክልል ደረጃ ያሉ የሥራ ኃላፊዎች ወደ ፈፃሚዎች ወርዶ ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፣ …ወዘተ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

96. ስለሁኔታው የፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የምግብ ዋሰትና ስትራቴጂ ፀድቆ ወደ ስራ ሲገባ የማስተግበሪያ ማኑዋሎች ተዘጋጅተው በ2009 በጀት አመት መጀመሪያ ላይ ፕሮግራሙ የሚተገበርባቸው አስራ አንድ ከተሞች ለአሰፈጻሚና ለባለድርሻ አካላት በስራቴጂ፣ በፕሮጀክት ማበለጸጊያ ሰነድ፣ በፕሮጀክት ትግበራ ሰነድ ላይ ለአመራርና ባለሙያዎች ግንዛቤ የተፈጠረላቸው እንደሆነና ወደ ትግበራም ከተገባ በኃላም የአፈጻጸም ማኑዋሎችና መመሪያዎች ላይ መደረኮችን በመፍጠር ለክልሎች አሰፈጻሚ አካላት ስልጠናዎች መስጠታቸውን የስራ ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡

97. የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በስትራቴጂው መሰረት የሚሰጡ ድጋፎችን ውጤታማና ቀልጣፋ ሰለመሆናቸው እንዲሁም የህግ ማቀፎችን መሰረት አድርጎ በየደረጃው የሚገኙ አሰፈጻሚዎች ያለባቸውን የአፈጻጸም ክፍተት በመለየት በሁሉም ክልሎች በወጥነት እንዲፈጸም ድጋፍና ከትትል በማደረግ ያለባቸውን የአፈጻጸም ክፍተቶች በመለየት የማሰተካኪያ እርምጃ ሰለመወሰዱ የሚያሳይ ማሰረጃ

በለማቅረቡ በኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

98. በመሆኑም ኤጀንሲው የላከውን የህግ ማዕቀፎች እስከታችኛው እርከን ድረስ በወረደው መሠረት በትክክል መተግርበሩን ድጋፍና ክትትል በማድረግ በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙት ችግሮችን ለይቶ በማውጣት በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲደረግባቸው ባለማድረጉና የፕሮግራሙን ውጤታማነት አስመልክቶም አስፈላጊውን ጥናት ባለማጠናቱ ፕሮግራሙ የሚተገበርባቸው አስራ አንድ ከተሞች በየደረጃው የሚገኙ አሰፈጻሚና ፈጻሚ ባለሙያዎች፣ የከተሞች የምግብ ዋስትና ሰትራቴጂን ለማሰፈጸም የተቋቋሙት ኮሚቴዎች ውጤት በሚያመጣና ወጥነት ባለው መልኩ ተናበው እንዳይሰሩ እንዲሁም የህግ ማዕቀፎችን በተሟላ ሁኔታ ተፈጻሚ እንዳይሆን በማድረግ ፕሮግራሙ ውጤታማ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን መለየትን በተመለከተ

99. በኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ላይ በተገለፀው መሠረት በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

100. በኦዲቱ ወቅት በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመለየትና በመፍታት የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች ወደ ዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ እንዲታቀፉ የቅድመ ዝግጅት እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችል ማኑዋሎችን በማዘጋጀት የክህሎት ስልጠናዎች የመሰጠት እና የተገልጋዮች እርካታ ለማወቅ የሚስችል ዳሰሳ ጥናት በእቅድ ይዞ መሠራት እንደሚኖርበት ተገልጻል፡፡

101. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ

መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

- ኤጀንሲው ዜጐችን የምግብ ዋስትናቸውን እንዲረጋገጥላቸው ለሚደረገው እንቅስቃሴ የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂው ፀድቆ ወደ ትግበራ ቢላክም በስትራቴጂው መሰረት ውጤት በሚያመጣ መልኩ እንዲተገበር ለማስቻል የሚረዱ የህግ ማዕቀፎች ለምሳሌ የከተማ ግብርና ስትራቴጂ፣ ፓኬጆች፣ የአከባቢ ልማት ስራዎች ማሰተግበሪያ ማኑዋሎች ሳይጸድቅ በ11 ከተሞች ተስራጭተው እየተጠቀሙበት መሆኑ፣
- በአከባቢ ልማት ስራዎች በአተገባበሩ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍቻ ማኑዋል በወቅቱ ፀድቀው ወደ ሥራ ባለመግባታቸው ስትራቴጂውን ተረድቶ በመሥራት ላይ የሥራ ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን፣
- በሁሉም ክልሎችና ከተሞች ልዩ ድጋፍ የሚያሰፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ኑሯቸውን በጎዳና ያደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎችን የተሃድሶ አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ የልየታ ረቂቅ ማኑዋል እና የድርጊት መርሃ-ግብር ረቂቁ ሰነዱ ጸድቆ በስራ ላይ ባለመዋሉ ልዩ ድጋፍ የሚያሰፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በልየታ ሰነዱና በመርሃ ግብሩ መስረት በፍጥነት የድጋፉ ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣
- ከአለም ባንክ እና ከመንግስት የሚደረገው ድጋፍ አሁን ካለው የኑሮ ውድነት አንጻር በቂ አለመሆኑ፣
- ከፌደራል እስከ ክልል ታችኛው መዋቅር ድረስ ወጥ የሆነ የፕሮግራም ማስፈፀሚያ አሠራርና አደረጃጀት አለመዘርጋቱ፣
- ህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር እንዲላቀቅ የተቀመጡ አማራጮች ላይ በየደረጃው ለሚገኙ ፈፃሚዎች ተከታታይነት ያለው እና ሊያሠራ የሚችል ስልጠና በየእርከኑ አለመሰጠቱ፣
- በክልልም ሆነ በፌደራል የሚፈለገውን ድጋፍና ክትትል አለመደረጉ፣

- በምግብ ዋስትና የታቀፉትን የህብረተሰብ ክፍሎችን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ የሚፈለገውን ያህል በአነሰተኛ ሥራ ላይ ያሉትን ህብረተሰብ ማቀፍ አለማቻሉ፣
- በቤተሰብ አንድ ሰው እንዲታቀፍ በማድረግ እና ቆጥበው ጊዘያቸውን ሲጭረሱ በቆጠቡት ገንዘብ ወደ ስራ ለማሰማራት የመስሪያ ቦታ አቅርቦት እጥረት ማነቆ መሆኑ፣
- በክፍለ ከተሞች በሚገኙ የልየታ ከሚቴዎች በምዝገባ ወቅት የተሰጡ ፎርማቶችን በአግባቡ ያለመሙላት እና የተሞላቸውን በግድየለሽነት የመያዝ ችግር፣
- መመዝገብ የሚገባቸውን ቤተሰቦችን ሳይመዘግቡ የማለፍ ችግር መኖሩ፣
- በልየታ ወቅት አንዳንድ ቀጠናዎች የማይገባቸውን ቤተሰቦችን እንዲጠቀሙ የማደረግ ችግር ሲኖር መጠቀም ያለባቸው እንዳይካተቱ የማደረግ ችግር መኖሩ፣
- የልየታ ኮሚቴው በልየታ ሥራ ወቅት ተሟልቶ ለመገኘትና እያንዳንዱን ከልየታ ጋር የተያያዘ ተግባር በቃለ ጉባኤ እያሰፈሩ የመሄድ ችግሮች መኖራቸውን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በአከባቢ ልማት ስራዎች ለሚሳተፉ ዜጎች በአረንጓዴ ልማት፣ በተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት፣ በውብት፣ በመናፈሻ እና ዘላቂ ማሪፌያ ልማት አሰተዳደር፣ በጽዳት አሰተዳደር፣ የአከባቢ ጥበቃና ሌሎች በተቀናጀ መልኩ ለምግብ ዋስትና ትግበራ በተመረጡ በሁሉም ከተሞች ህበረተሰቡን በማሳተፍ በሚፈለገው መልኩ እየተስራ አለመሆኑ፣
- እንዲሁም በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች ቀጣይነት ባለው መልኩ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ለማረጋገጥ እንዲቻል በአከባቢ ልማት ስራዎች ተግባራዊነታቸው ላይ የሚያገጥሙትን የበጀት እጥረት፣ የአቅም ግንባታ ችግሮች፣ ተጠቃሚዎችን የነጻ የህክምና የጤና አግልግሎት አለማግኘት፣ የልማት መሣሪያና የሴፍቲ መሣሪያዎች በወቅቱ አለመሟላቱ፣

102. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በፕሮጀክት ማበልጸጊያ ሰነዱ ላይ እንደተመለከተው የዘላቂ የኑሮ ዋስትና ትግበራ የሚጀምረው ተጠቃሚዎች ድጋፍን ማግኘት ከጀመሩበት ከአንድ አመት በኃላ በመሆኑ በከተሞች ደረጃ በአሁን ወቅት በዘላቂ ኑሮ ዋስትና የሚታቀፈውን የቤተሰብ አባል በመለየት ስልጠና እንዲያገኙ መደረጉን ገልጸው በቀጣይም በ2ኛ እና በ3ኛ ዙር የሚሰማሩበትን የስራ ዓይነት እንዲመርጡ በማደረግ የንግድ ሥራና የስራ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ድጋፍ በመስጠት ወደ መደበኛ ሥራ እድል ፈጠራ ስራ ፕሮግራም እንዲሸጋገሩ ማድረግና ይህንን የሚመራ ጋይድ ላይን በፌደራል ደረጃ በአማካሪ ደርጅት ተዘጋጅቶ ለክልልና ለከተማ አሰፈጻሚ አካላት ሰልጠና በመስጠት ወደ ትግበራ እንዲገባ መደረጉን ሆኖም ተጠቃሚዎች ሙሉ ለሙሉ ከፕሮጄክቱ ተመርቀው ወደ ዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ የሚገቡት በ3ኛ ዙር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

103. የኤጀንሲው የስራ ኃለላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከላይ ለማሳይነት በተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ እና በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎችን ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት እንዲቻል ቀጣይነት ያለው የአሰራር ስራዓትን ተግባራዊነቱን በሚመለከት ኤጀንሲው ከስልጠኛ እና ከስራ ልየታ ከመስራት ባለፈ በረቂቅ ደረጃ የሚገኘውን የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ መመሪያ ለስራ ዝግጁ ያላደረገ በመሆኑና፣ ከሌሎች አካላት ጋር የቅደመ ዝግጅትን የሚመለከቱ የተጀመሩና እየተሰሩ ያሉትን ስራዎችና በአሁኑ ሰዓት በኑሮ ማሻሻያ የታቀፉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ድጋፉ ከመጠቅም ባለፈ በድጋፉ በኑሯቸውና በህይወታቸው እንዲሁም በኢኮኖሚው ያመጡትን ለውጥ በጥናት የተደገፍ ስራ ስለመስራቱ የሚያመላከት መልስ እና ማሰረጃ ለኦዲት ቡዱኑ ባለመቅረቡ በኤጄንሲው የስራ ኃላፊዎች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

104. በመሆኑም ኤጀንሲው በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎችን ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት በሚጠበቀው ደረጃ ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማደረጉ የኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ አተገባበር ውጤታማና ቀልጣፋ ካለማደረጉም በላይ በኑሮ

ማሻሻይ የሚታቀፉትን የህበረተሰብ ክፍሎችን በኑሯቸው እንዳይሻሻሉና ህይወታቸው እንዳይለወጥና ዳግም ወደ ደህነት እንዲመልሱ አስተዋጾ ሊያደረግ ይችላል፡፡

## በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ

## የሚውል ሀብት ማሰባበስን በተመለከተ

105. ኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚውል ሀብት ከህብረተሰቡ፣ ከባለድርሻ አካላትና ከልማት አጋሮች እንዲሰበሰብና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

106. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና አፈጻጸም ለማረጋገጥ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ከግልና ከመንግስት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን እንዲሁም በከተሞች የምግብ ዋስትና የሚውል ሀብት ከህበረተሰቡ፣ ከባለደርሻ አካላትና ከልማት አጋሮችን በማስተባበርና በማሰባበሰብ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ የማደረግ ስራ ለመሥራት በድርጅታዊ ጥናት ሠነዱ እና በማቋቋሚያ ደንብ 374/2008 ላይ ተገልጿል፡፡

107. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት ኤጀንሲው የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና አፈጻጸም ለማረጋገጥ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ከግልና ከመንግስት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን እንዲሁም በከተሞች የምግብ ዋስትና የሚውል ሀብት ከህበረተሰቡ፣ ከባለደርሻ አካላትና የልማት አጋሮችን በማሰተባበር የሚፈለገውን ሀብት በአገር ውስጥ በማሰባበሰብ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ የማደረግ ስራ በሚጠበቀው ደረጃ እንዳልሰራ ታውቋል፡፡

108. በተመሳሳይ መልኩ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የዘርፉ የስራ ሃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ እንደገለፁት ከድህነት ወለል በታች ላሉት የህብረተሰብ  ክፍሎች ከለጋሽ ድርጅቶችና ከግል ተቋማት ሀብትን

የማሰባሰብና ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየሰሩ  እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም በዘረፉ ድህነትና የስራ አጥነትን በመቅርፍ የህዝቡን ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ከማረጋገጥ አኳያ የሚፈለገውን ያህል ውጤት አለማስገኘቱን  በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

109. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የፌደራል ኤጀንሲው የፕሮጀክቱን ዓላማ ለህብረተሰብ እንዲያውቁት ከማደረግ አንጻር የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራታቸውን እና በቀጣይ  የምግብ ዋስትና ፕሮግራሙን  በባለቤትነት እንደመራው ለማደረግ የምግብ ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለኤጀንሲው ማኔጅመንት አባላት አሰተያየት እንዲሰጡበት የመበተን ስራ መስራታቸውን እና በአሁኑ ወቅት ሀብት የማሰባሰቡን ሥራ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጽ/ቤት ተጠሪ ሆኖ ለተቋቋመው የስራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

110. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በኤጀንሲው ድርጅታዊ ጥናት ሰነዱ እና በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 ዓ.ም ላይ በተገለጸው መሰረት ሀብት የማሰባሰብና የማሰተላለፍ ስራ የመስራት ሃላፊነት እንዳለበት የተገለፀ ሲሆን ይህ ህጋዊ ኃላፊነት በህግ ስለመነሳቱ ማስረጃ ባላቀረቡበትና ስራው ከኤጀንሲው ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጽ/ቤት ተጠሪ ሆኖ ለተቋቋመው የስራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን ስለመተላለፉ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ባለመቅረቡ በኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

111. በመሆኑም ኤጀንሲው የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና አፈጻጸም ለማረጋገጥ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ከግልና ከመንግስት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን እንዲሁም በከተሞች  የምግብ ዋስትና ስራ የሚውል ሀብት ከህበረተሰቡ፣ ከባለደርሻ አካላትና ከልማት አጋሮችን በማሰተባበርና በማሰባበሰብ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የማስተላለፍ ስራ ባለመስራቱ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎች ቁጥር እንዲጨምር ከማድረጉም በላይ በከተሞች በስራ ዕድል ፈጠራ እና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ስትራቴጂ የተያዘውን ግብ በሚፈለገው ደረጃ እንዳይሳካ አሰተዋጾ አድርጓል፡፡

**ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮጀክቶች መገምገሚያ ሠነድ (Project appraisal Document) ስለመዘጋጀቱና በክልሎች ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

112. በኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን የሚገመግምበት የግምገማ ሠነድ (Project appraisal Document) በማዘጋጀት ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሊልክና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

113. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን የሚገመግምበት የግምገማ ሠነድ (Project appraisal Document) በማዘጋጀት ወደ ክልል አውርዶ አፈፃፀሙን መከታተል እንዳለበት በድርጅታዊ መዋቅር ጥናቱ ላይ ተገልጿል፡፡

114. ይሁን እንጂ የግምገማ ሰነዱን እንዲወጣ በማድረግ ለትግበራ ወደ ለክልል እና ከተማ አስተዳደሮች አለመላኩን ከተሰበሰበ ማስረጃ እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በሰባት ከተሞች ለሥራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

115. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ መሰረት የግምገማ ሰነዱ መዘጋጀቱን ገልፀው በዓመት አራት ጊዜ በኤጀንሲው ደረጃ ክትትል የሚደረግ ሲሆን ከአለም ባንክ ቡድን ጋር በጋራ በዓመት ሁለት ጊዜ የፌደራልና የክልል አሰፈጻሚና ባለድርሻ አካላት በተኙበት የክትትልና ድጋፍ መደረክ በማዘጋጀት ክትትል እንደሚያደርጉ በመልሳቸው ገልጸዋል፡፡

116. የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የግምገማ ሰነዱ ተዘጋጅቶ ለትግበራው ወደ ክልሎች ሰለመላኩና በሰነዱ መሠረት ገምግሞ ድጋፍና ክትትል ስለማደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ባለመቅረቡ መልሳቸውን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

117. በመሆኑም የፌደራል ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን የሚገመግምበት የግምገማ ሠነድ (Project appraisal Document) በሀገር አቀፍ ደረጃ የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የፕሮጀክቶችን አተገባበርና አፈጻጸም በሰነዱ መሰረት በዕቅድ ይዞ በቋሚነት

በመከታተል የሚገመግምበት ሁኔታ ባለመኖሩ የፕሮጀክቱን ውጤታማነትና በአፈጻጸሙ ወቅት ያጋጠሙትን ክፍተቶች ለማረም እንዳይቻል ከመሆኑም በላይ የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ወደ ሌሎች ከተሞች በፍጥነት እንዳይሰፋና በወጥነት እንዳይተገበር አስተዋጾኦ ሊያደረግ ይችላል፡፡

## በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ ስለመሰጠቱ እና ድጋፍና ክትትል ስለመደረጉ በተመለተ

118. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 11፣12 በተቀመጠው መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት የተጋለጡ እና ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ዘርግቶ ሊሠራ ይገባል፡፡

119. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት የተጋለጡ እና ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ኤጄንሲው በድርጅታዊ ጠናቱ በተገለፀው መሰረት የድጋፍና ክትትል ስርአት በመዘረጋት እየሰራ ቢሆንም ነገርግን በዚህ ጉዳይ ላይ በሚሰሩ ስራዎች አፈፃፀም ላይ በኦዲቱ የተለዩት ዝርዝር ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- በፌደራሉና ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተከታታይነትና ዘላቂ የሆነ የግንዛቤ አፈጣጠር ሥራ በወጥነት እስከ ታችኛው እርከን ያለመሥራት፣

- ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች በቀጥታ ድጋፍና በአከባቢ ልማት ሥራዎች በማሳተፍ የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ የግብዓት ችግሮች መኖራቸው ለምሳሌ፡-
  - በዘርፉ የተሟላና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ድጋፍ መስጠት የሚችል አመራርና ባለሙያ እጥረት መኖሩ፣
  - በየደረጃው ለዘርፉ ልማት በቂ በጀት አለመመደብ፣
  - በአስፈጻሚ ተቋማትና በየደረጃው በሚገኙ ቢሮዎች በሰው ኃይልና በቁሳቁስ እንዲሁም ለመስክ አገልግሎት የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች አለማሟላት፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር የልማት መሣሪያና የሴፍቲ መሣሪያዎች በወቅቱ አለመሟላት፣ ይህም ህጉን ያልተከተለ አሠራር ችግር /በቀጥታ ግዥ/ የሚፈጸምበት ሁኔታ መኖሩ፣ በድጋፉ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች ክፍያ አነሰኝ የሚል ጥያቄዎች የሚነሱ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በ10 ክፍለ ከተሞችና በተመረጡ 35 ወረዳዎች ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ያሉ ቤተሰቦችን በአካባቢ ልማት እና ማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች በማሳተፍ የምግብ ዋስትና ተጋላጭነትን፣ መቀነስ እገዛ የሚያደርግ አደረጃጀት ፈጥሮ በሁሉም ክፍለ ከተሞች በተሰጣቸው የተጠቃሚነት ኮታ መሠረት በሁለቱም ፕሮግራሞች /በአከባቢ ልማትና በቀጥታ ድጋፍ ፕሮግራም/ ምዝገባ ለማካሄድ በታቀደው መሠረት በቀጥታ ድጋፍ ፕሮግራም እና በአካባቢ ልማት ፕሮግራም ከተመዘገቡ 123,918 ውስጥ 19,132(15%) ተጠቃሚ ሲሆኑ 104,786 ዜጐች ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ማስረጃው ያሳያል፡፡ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ 6 በሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡
- በደቡብ ክልል በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት የተጋለጡ እና ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት የተደረገ ቢሆንም የቀጥታ ድጋፉ ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ የተቀመጠው ቁጥርና

መጠቀም የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር ያለመጣጣም እንዲሁም በልየታ ወቅትም ከነበረው የጥራት መጓደል ጋር ተያይዞ የሥራ ጉድለቶች መኖራቸው፣

- በአማራ ክልል በደሴ ከተማ በ2009 በጀት ዓመት የተጀመረ ሲሆን ሥራውን በተቀላጠፈ አግባብ ለመምራት የሚያስችል የአሠራር ስርዓት የልተዘረጋለትና በአግባቡ የተጠና አደረጃጀት ያልተፈጠረለት በመሆኑ ቀጥሎ የተመለከቱት የአሠራር ችግሮች መስተዋላቸው፣
    - በክልልም ሆነ በከተማ ደረጃ ያለው አደረጃጀት ወጥነት የሌለው በመሆኑ በደሴ ከተማ አሠራርን ተከትሎ ለሚፈጠሩ አደረጃጀቶች ማለትም በክልል የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ምክር ቤት፣ ስትሪንግ ኮሚቴ እንዲሁም ከዚሁ ጋር የተያያዙ ንኡሳን ኮሚቴዎችን ማቋቋም አለመቻል፣
    - የበጀት ዓመቱን ተግባራት በተቀመጠው መርሃ ግብር መሠረት ለማከናወን በፌዴራል የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በኩል በጀት ጸድቆ ለአማራ ክልል መላክ ባለመቻሉ ለሥራዎች መዘግየት ምክንያት መሆኑ፣
    - የምግብ ዋስትና ሥራ እንዲከናወን ከአማራ ክልል የደሴ ከተማ የተመረጠ ቢሆንም በጽ/ቤቱ ያለው ባለሙያ የተሟላ ባለመሆኑ ያሉት ሠራተኞች ተረጋግተው እንዳይሠሩ አስተዋጽኦ መፍጠሩ፣
    - በደሴ ከተማ ለጽ/ቤቱ ሥራ መሳለጥ አስፈላጊ ናቸው የተባሉ የቢሮ ግብዓቶች /ጠረንጴዛ፣ ሸልፍ፣ ወንበር፣ ከምፒዩተር፣ ወረቀት …ወዘተ/ ባለመሟላታቸው የምግብ ዋስትና ሥራውን በሚፈለገው አግባብ እየተሠራ አለመሆኑ፣
    - የከተማው ጽ/ቤት ለድጋፍና ክትትል የሚያገለግል ተሽከርካሪ የሌለው መሆኑ….ወዘተ ችግሮች ያሉበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ከተማ መስራት ለማይችሉ፣ የመስራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት ለተጋለጡ ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች

ተጠቃሚ ለማደረግ እየሰሩ እንደሆነ ገልጸው ነገር ግን ቀጥታ ድጋፍ ለማድረግ የሚከፈለው ብር 225 በመሆኑ ካለው ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ኑሮአቸውን ያሻሽላል ተብሎ የሚታሰብ አለመሆኑ፤ እንዲሁም በአከባቢ ልማት ስራ ለምሳሌ፡ በደረቅ ቆሻሻ ማንሳት፣ በአረንጓዴ ልማት ላይ ሰርተው እራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ ረገድ እየሰሩ ቢሆንም የስራ ላይ የሴፍቲ ወይም የደህንነት መሳሪያዎች፣ የመስሪያ እቃዎችን ለመግዛት በጀት ባለመለቀቁ የመዝግየት ሁኔታዎች መኖራቸውን፣ የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲም ሆነ ክልሉ ኤጀንሲዎች ለአስፈጻሚዎች ሥልጠናዎችን በመስጠት የመደገፍ ስራ ቢሰራም ሰልጠና ለመስጠት ሲያቅድ የክልሉን የስልጠና ፍላጎት ጥናት ወይም (ኒድ አሰስመንት ጥናት) ሳይሰራ እና ሳይጠይቅ የሚሰጥ ሥልጠና የተሟላ ነው ለማለት የማያስችል መሆኑ፣ እና በተሰጠው ስልጠና ላይ ተመስረቶ በስራ ላይ ምን ውጤት እንዳመጣ ወይም አሰገኝ የሚለውን አጥንቶ ለክልሉ በማሳወቅ ሥራዎችን በውጤት እንዲከናወኑ እያደረገ አለመሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

120. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ የከተሞች የምግብ ዋሰትና ፕሮጀክት በ2009 ዓ.ም ተጀምሮ በ11 ከተሞች ላይ በሙከራ ትግበራ ደረጃ ኘሮግራሙ እየተካሄደ ሲሆን በኮታ አሰጣጡ ወቅት ለተፈጠረው ችግር ከከተማው አሰተዳደር ጋር በመነጋገር የማሰተካኪያ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

121. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ለማሳያነት በቀረበው ከኮታ በላይ እና ከኮታ በታች የተመዘገቡትን በሚመለከት ምን አይነት ማሰተካኪያ እንደተወሰደ እና ችግሩን ስለመቀረፉ እንዲሁም ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች አስመልክቶ ስለተወሰደው እርምጃ የሚያሳይ ዝርዝር ማሳረጃ ለኦዲት ቡዱኑ ያላቀረቡ በመሆኑ በኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

122. በመሆኑም ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት የተጋለጡ እና

ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ውጢታማ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት ከፌደራል ከተሞች ጀምሮ እስከ ታችኛው እርከን ድረስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አደረጃጀት እንዲፈጠር እና በከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራሙ አፈጻጸም በወጥነት እንዲተገበር የሚጠበቀውን ያህል ክትትል እና ድጋፍ ባለማደረጉ የከተሞችን የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በወጣው ስትራቴጂና ይህንን ተከትሎ የወጣውን የ10 አመት የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም መርሃ ግብር መሰረት በፍጥነትና በተደራሽነት ለመተግበርና በአጭር ጊዜ ውስጥ በከተሞች ያለውን የምግብ ዋስትና እጦት ለማቃለልና በዘላቂነት ለማሰወገድ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዳይሆን አሰተዋጸኦ ያደርጋል፡፡

## ኤጀንሲው በከተሞች የእርስ በእርስ የልምድ ልውወጥ የጋራ መድረክ መፍጠሩን በተመለከተ፣

123. ኤጀንሲው በፌደራል የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ላይ በተገለፀው መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትና የጋራ መድረክ በማዘጋጀት ከተሞች የእርስ በእርስ ልምድ ልውወጥ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ሊሠራ ይገባል፡፡

124. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው በአምስት አመት በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ላይ በተገለፀው መሠረት ቀጣይና ተከታታይ የሆነ የከተሞች የምግብ ዋስትና የጋራ መድረክ እና የእርስ በእርስ ልምድ ልውውጥ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ መሥራት እንዳለበት ተገልፃል፡፡

125. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት ኤጀንሲው በከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችለውን የጋራ መድረክ እና የእርስ በእርስ ልምድ

ልወውጥ ሥርዓት በመዘርጋት የክልልና የከተማ አስተዳደሮች በዘርፉ መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የግብዓት አቅርቦት፣ በአስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የአሰራር ምርጥ ተሞክሮችን በመቀመርና በማስፋፋት በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለው የልምድ ልውውጥና የመወያየት ልምድ በተሟላ ሁኔታ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ ተገልጋዮች የሚሰጠው አገልግሎት ወጥ እና የተሟላ እንዲሆን በሚያስችል መልኩ በቋሚነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ እየተተገበረ አለመሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

126. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ፕሮግራሙ ከተጀመረበት ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ስልጠናዎችና የጋራ ግምገማዎችን በተለያዩ ተሞክሮ ባላቸው ከተሞች ለአመራርና ባለሙያዎች ስልጠና በማዘጋጀት ከተሞች የራሳቸው የልምድ ልውውጥ እንዲኖራቸው መደረጉን ገልጸው፣ ነገር ግን ከሚሰራው ስራ አንጻር በሚፈለገው ደረጃ እንዳልሆነ እና ወደፊትም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የልምድ ልውውጥ መደረኮችን መፍጠር እንደሚያሰፈልግ ገልፀዋል፡፡

127. በመሆኑም የፌደራል ኤጀንሲው የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና በሚመለከት የጋራ መድረክ በማዘጋጀት ከተሞች የእርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ በቋሚነት ክልሎችና የከተማ አሰተዳደሮች ባለመስራቱ በክልል አመራሩ እና በባለሙያዎች መካከል በእቅድ አፈጻጸም ወቅት እና ስትራቴጂውን ተከትሎ የሚታዩ የአጻጸም ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል አቅም እንዳይፈጠር በማድረግ ኤጀንሲው በስትራቴጂው የተቀመጡትን ግቦች እና የተሰጠውን ኃላፊነት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳያሳካ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር

## ስላለው ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ

128. ኤጀንሲው በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 በተገለፀው መሠረት ከዘጠኙ ክልሎችና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ጋር የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስት ሥራ ዕቅድን በጋራ ለመተግበር የስምምነት ሠነድ በመፈራረም አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

129. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው በከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና አፈፃፀም ዙሪያ ከዘጠኙ ክልሎችና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ጋር የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስት ሥራ ዕቅድን በጋራ ለመተግበር የስምምነት ሠነድ ተፈራርሞ እየሠራ ይገኛል፡፡

130. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የማስረጃዎች ክለሳ ለማወቅ እንደተቻለው በታቀደው የጋራ ዕቅድ መሠረት ከክልሎች፣ ከከተማ አስተዳደሮች፣ ከባለድርሻ አካላትና የዘርፉ አጋሮችን የትብብር መስኮችን በመለየት፣ በመደበኛ የዕቅድ ዝግጅትና የአፈፃፀም የግምገማ ግንኙነት ጊዜ ጠብቆ በመገምገም እና የተዘጋጀውን ዕቅድ በታቀደው ልክ በመተግበር ላይ ከፌደራል እስከ ክልል ባሉ ፈፃሚዎች የሥራ ክፍተቶች ያሉባቸው ሲሆን፣ የፌደራሉ ኤጀንሲም ወጥነት እና ተከታታይነት ያለው ድጋፍና ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እያደረገ አለመሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

131. እንዲሁም ለዜጐች የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥላቸው እና የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው በአስፈፃሚና በባለድርሻ አካላት የሚሰጠው ክትትልና ድጋፍ ዘላቂነት እንዲኖረው በሥራ ዕድል ፈጠራና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ዙሪያ የሚሠሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት ስራዎች በተቀናጀና በተናበበ ሁኔታ በማስፈጸም እና በመፈፀም ውጤቱን ቀጣይነት ያለው ከማደረግና ሁሉም የድርሻቸውን ከመወጣት አንጻር የድጋፍና የክትትል ሥራው ክፍተት ያለበት መሆኑ፣ ይህንንም ክፍተት ኤጀንሲው በሚፈለገው ደረጃ ክትትል በማድረግ ችግሩ እንዲቀረፍ አለማድረጉን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃወች ለማወቅ ተችሏል፡፡

132. በተጨማሪም በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች በኦዲት ቡድኑ ለሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ መሠረት ሥራ ለሌላቸው ዜጐች የሥራ እድል እንደሚፈጠርላቸውና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ውስጥ ያሉ ዜጐች የምግብ ዋስትና ሊያረጋግጥላቸው የሚያስችል ሥራ መሠራቱን በየደረጃው ያሉ ፈፃሚ አካላት የድጋፍና የክትትል ሥርዓት ዘርግተው በሚፈለገው ደረጃ እና ወጥነት ባለው መልኩ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እየተወጡ አለመሆኑን፤ ኤጀንሲውም በዚህ ዙሪያ የሚሠሩ ሥራዎች ስለመሠራታቸው የሚመለከታቸው አካላት እስከ ታችኛው

መዋቅር ወርደው የቁጥጥር ሥራ መሥራታቸውን ስለመከታተላቸው በክትትል እያረጋገጠ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

133. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከፌደራል እስከ ሚተገበርባቸው ከተሞች ድረስ የተለያዩ አደረጃጀቶች ተፈጠረው ወደ ትግበራ በገቡት መሠረት ከአስፈጻሚ እና ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተዋቅሮ ሥራዎችን የሚገመገሙበትና ድጋፍ የሚደረግበት የአሰራር ሥርዓት ቢዘረጋም ኮሚቴዎቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተገናኝኘተው ድጋፍና ክትትል የሚያደርጉት አግባብ ክፍተት ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

134. በመሆኑም ኤጀንሲው በከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና አፈፃፀም ዙሪያ ከዘጠኙ ክልሎችና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ጋር የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስት ሥራ ዕቅድን በጋራ ለመተግበር የስምምነት ሠነድ በመፈራረም አፈፃፀሙን ክትትል ማድረግ እንዳለበት በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 ኃላፊነት የተሰጠው ቢሆንም ይህን ሃላፊነቱን በሚጠበቀው ደረጃ ባለመወጣቱ በሥራ እድል ፈጠራና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ሥራዎች አተገባበር ላይ ተጽዕኖ እንዲፈጥር በማድረግ በዘርፉ ለደረስበት የታሰበው ግብ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## ለከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ሥራዎች የሚሆኑ ግብዓቶች ማሟላታቸውን በተመለከተ

135. ኤጀንሲው በፌደራል የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና አፈፃፀም ዙሪያ በአገር አቀፍ ደረጃ መፍትሄ የሚሹ የግብዓት ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሊፈታ ይገባል፡፡

136. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና አፈፃፀም ዙሪያ በአገር አቀፍ ደረጃ መፍትሄ የሚሹ የግብዓት ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መፍታት እንዳለበት ተመላክቷል፡፡

137. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር (በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ) እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የቢሮ ሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከእነዚህ ተቋማት ተሰብስበው በተተነተኑ ማስረጃዎች መሰረት ኤጀንሲው በድርጅታዊ መዋቅር ጥናት ሰነዱ እና በአምስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ ላይ በተገለፀው መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸምን ውጤታማ ለማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ መፍትሄ የሚሹ የግብዓት ችግሮችን (ትራንስፖርት፣ ውሃ, መብራት፣ የመስሪያ ቦታ፣ የመሸጫ ቦታ፣ ጥሬ እቃ….) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ችግሩን ለመፍታት ሥርዓት ዘርግቶ በሚጠበቀው ደረጃ ባለመሥራቱ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለዜጐች የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ የሥራ ማነቆ ሆኖ ከመገኘቱም በላይ ችግሩ ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ እንደመጣ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

138. ከዚሁ ጋር በተያያዘ በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና አንድ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች የኦዲት ቡድኑ ለሥራ ኃላፊዎች ባደረገው ቃለ-መጠይቅ ከሰጡት መልስና ከተከለሰው ማስረጃ ለማወቅ እንደተቻለው ለሥራ ፈላጊ ዜጐች የሥራ እድል ፈጥሮ ራሳቸውን ከማስቻልና በምግብ ዋስትና ኘሮግራም ለታቀፉ ዜጐች የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥላቸው የሚሠራው ሥራ በታችኛው መዋቅር የሚከናወን ቢሆንም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት መሟላት ያለበትን ግብዓት /ለአንድ ማዕከላት መሟላት ያለበት የሰው ኃይል፣ የቢሮ ቁሳቁሶች፣ ለድጋፍና ክትትል ሥራ የሚሆን ተሽከርካሪ፣ ለኢንተርኘራይዞች መሠረተ ልማት የተሟላለት የመሥሪያና የመሸጫ ቦታ አቀርቦት፣… ወዘተ/ እንዲሁም ኑሮአቸውን ለማሻሻል በአከባቢ ልማት ላይ ተሰማርተው እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለሚረዱ ዜጐች የመሥሪያ መሳሪያዎች እና ከአደጋ መጠበቂያ የደህንነት ቁሳቁሶች /የእጅ ጓንት፣ ቱታ፣ አካፋ፣ ዶማ…ወዘተ/ በወቅቱ የማይሟላላቸው መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

139. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ መሠረተ ልማት ያልተሟላላቸው ሼዶች ለማሟላት በተለይም የመብራት ኃይል ችግር ያለባቸው ሼዶችን ክልሎች ለይተው የእቅዱ አካል እንዲያደርጉ ማደረጋቸውና በተጠየቀው መሠረት ችግሮቻቸው እንዲፈታ ለኢትየጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት በማሳወቅ ክትትል እያደረጉ መሆኑን ገልጸው፣ ነገር ግን የኤሌክትሪክ ችግር አሁንም ማነቆ እንደመሆኑ መጠን የፌደራል መንግሥት እና በክልልና ከተማ አስተዳደሮች የበላይ አመራር ደረጃ ታውቆ የማይፈታ ችግር በመሆኑ እንደ ሀገርም ትልቅ ማነቆ እየሆነ የመጣ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

140. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኤጀንሲው በእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ /2008-2012/ እና በድርጅታዊ መዋቅር ጥናት ሰነድ ላይ በተገለጸው መሠረት በዘጠኙ ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ለሥራ አጥ ዜጐች የሥራ እድል ለመፍጠር በታቀደው ልክ ለመተግበር እና በምግብ ዋስትና ለሚታቀፉ ዜጐች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት በማሻሻል የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ የሚፈጠሩ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሩ እስኪሚፈታ ድረስ መስራት የሚገባው በመሆኑ ችግሩ በፌደራል መንግሥት እና በክልልና ከተማ አስተዳደሮች የበላይ አመራር ደረጃ ታውቆ የማይፈታ ችግር በመሆኑ ነው ተብሎ መገለፁ ኤጄንሲው የማይፈታችግር መሆኑን እያወቀ እንዴት እቅድ ማቀድ እንዳስፈለገው ያልገለፁ በመሆኑ በኤጄንሲው የስራ ኃላፊዎች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

141. በመሆኑም በአገር አቀፍ ደረጃ መፍትሄ የሚሹ የግብዓት ችግሮች ሳይፈቱ ከዓመት ዓመት ተሸጋጋሪ በመሆናቸው ለዜጐች የሚፈጠረው የሥራ እድል ፈጠራ እንዲሁም የምግብ ዋስትና ኘሮግራም አፈፃፀሙ ውጤታማ እንዳይሆኑ በማድረግ እና ፕሮግራሙ ከአስራ አንድ ከተሞች በተጨማሪ ወደ ሌሎች አዳዲስ ከተሞች ላይ በተያዘለት ዕቅድ መሰረት እንዳይተገበርና በሀገር ደረጃ የሥራ አጥነትን እና ድህነትን ለመቀነስ የተቀመጠው ግብ በሚጠበቀው ፍጥነት እንዳይሳካ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የሥራ ዘርፎች ፓኬጅን መቅረጽንና አፈጻጸሙን በተመለከተ

142. ኤጀንሲው የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት እና የአደረጃጀትና የአሠራር መመሪያ ላይ በተገለፀው መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሥራ ፈላጊዎች እንደየ ፍላጐታቸውና ችሎታቸው የሚሠማሩበት የሥራ ዘርፎችን ፓኬጅ ቀርጾ ለፈጻሚዎች በመላክ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

143. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት እና የአደረጃጀትና የአሠራር መመሪያ መሠረት ለሥራ ፈላጊዎች እንደየ ፍላጐታቸውና ችሎታቸው የሚሠማሩበት የሥራ ዘርፎችን ፓኬጅ ቀርጾ ለፈጻሚዎች ማውረዱ ታውቋል፡፡

144. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሂዳቸው የማስረጃዎች ክለሳ እና ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ መጠይቆች ከሰጡት መልስ ማረጋገጥ እንደተቻለው ኤጀንሲው ሥራ ፈላጊዎች እንደየ ፍላጐታቸውና ችሎታቸው የሚሠማሩበት የሥራ ዘርፎችን ፓኬጅ ቀርጾ ወደ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ቢልክም በተላከው ፓኬጅ መሠረት ስለመሠራቱ በአፈጻጸሙ ላይ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ በሚፈለገው ደረጃ ድጋፍና ክትትል እያደረገ አይደለም፡፡

145. በተመሳሳይ በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በሰባት ክልል ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለመጠይቅ ከሰጡት መልስ ለመገንዘብ እንደተቻለው በፓኬጁ ላይ የተዘረዘሩትን የሥራ ዘርፎች ለመተግበር በማነቆነት የጠቀሷቸውን ቀጥሎ ተመልክተዋል፡፡

- በኤጀንሲው ፓኬጁን ቀርጾ ወደ ከተሞች እና ወደ ከተማ አስተዳደር ሲያወርድ በከተሞች ያለውን ፀጋ ያገናዘበ አለመሆኑ፣
- ለኢንተርፕራይዝ የመሥሪያና የመሸጫ ቦታ ለማዘጋጀት የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ውስንነቶች መኖር፣
- ለኢንተርፕራይዞች አገልግሎት የሚገነቡት ሼዶች ከከተማ ወጣ ብሎ የሚሰሩ በመሆኑ አገልግሎት ላይ የማይውሉ ሲሆኑ ክልሉም ሆነ ፌደራሉ ይህን ችግር ለመፍታት እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም ችግሩ እስኪቀረፍ ድረስ ያለመሥራት ችግር መኖሩ፣

- የሥራ ዘርፍ ፓኬጁ ሲዘጋጅ በከተሞች ያለውን ፀጋ እንዲካተት በጥናት ያላረጋገጠ መሆኑ፣
- ሥራ ፈላጊዎች የሥራ ዕድል የሚፈጠርላቸው በተማሩትና በፍላጎታቸው ባለመሆኑ በተፈጠረላቸው የሥራ መስክ ላይ ያለመሠማራት ችግር መኖሩ፣

ማነቆዎች ናቸው፡፡

146. ስለጉዳዩ ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ መሠረት በአምስቱ ስራ ዘርፎች ሥር ባሉ ንዑስ ዘርፎች ላይ በርካታ ስራ ፈላጊዎች እንደየ አከባቢ ተጨባጭ ሁኔታ አዋጭነቱን በመገምገም ወደ ስራ የሚገባበት ሂደት ቢኖርም በአከባቢው የስራ ዕድል ሊፈጠር የማይቻልበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ሁሉም ተግባራዊ ማደረግ የማይቻል ሲሆን፣ ለከተማ ግብርና እና ለማኑፋክችሪንግ ዘርፍ የሚውሉ ቦታ ዝግጅት ያለማቀረብና ፓኬጆቹን ለማስፈጸም ቅንጅታዊ አሰራሩ ክፍተት ያለበት መሆኑን በድጋፍ ለማወቅ ተችሏል፡፡

147. በመሆኑም ፓኬጆቹ እንደየ ክልል ከተሞች ተጨባጭ ሁኔታ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በማገናዘብና ወቅታዊነታቸው እና ባለው የአከባቢ ፀጋ ልክ በጥናት ተረጋግጠው ባለመወረዳቸው በወጥነት ለመተግበር እንዳይቻል እንዲሁም ስራ ፈላጊዎችን እና ኢንተርፕራዞች እንደየፍላጎታቸው በተሰማሩበትና በመረጡት የስራ ዘርፍ እንዳይሰሩ ምቹ ሁኔታ ባለመፍጠሩ ምክንያት ሥራ ፈላጊ ዜጐች ለመሥራት ያለመፈለግ ዝንባሌ እንዲታይባቸው አድርጓል፡፡

## በከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና በምግብ ዋስትና ዙሪያ ግንዛቤ መፈጠሩን በተመለከተ

148. ኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ላይ በተመለከተው መሠረት ከሚዲያ ጋር በመቀናጀት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር፣ የሕዝብ መድረኮች በመፍጠርና የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ላይ ተከታታይነት ያለው ግንዛቤ ሊሰጥ ይገባል፡፡

149. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ በተገለፀው መሠረት ከሚዲያ ጋር በመቀናጀት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር፣ የሕዝብ

መድረኮች በመፍጠርና የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ተከታታይ ግንዛቤ አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

150. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የማስረጃዎች ክለሳ እና ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በቀረቡ ቃለ መጠይቆች ከሰጡት መልስ መረዳት እንደተቻለው ኤጀንሲው በዘረጋው ሥርዓት መሠረት ከሚዲያ ጋር በመቀናጀት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር፣ የሕዝብ መድረኮች በመፍጠርና የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም በከተሞች የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የሥራ ዕድል አፈጣጠር ላይ ተከታታይነት ያለው እና በሚፈለገው ደረጃ እስከ ታችኛው እርከን ወርዶ ለተገልጋዮች፣ ለማህበረሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ አለመፍጠሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

151. እንዲሁም በአብዛኛው ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች ለምሳሌ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ፣ በአማራ እና በሀረሪ፣ በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ለሥራ ፈላጊዎች ግንዛቤ መፍጠርን በተመለከተ ከተመዘገቡ ሥራ ፈላጊዎች ብዛት ጋር ሲነፃፀር ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ወጣቶች ቁጥር ውስን መሆናቸውን፣ በተመሳሳይም ለዩኒቨርስቲና ኮሌጅ ምሩቃን ልዩ ትኩረት በመስጠት በዘርፉ ሥራ አዋጭነት ላይ የሚፈለገው ግንዛቤ በመፍጠርና በማሳመን ወደ ሥራ ከማስገባት አንጻር እንዲሁም በየአካባቢው ያሉ የሥራ አማራጮችን በሚገባ በማመላከት የሥራ መስክ እንዲመርጡ በማድረግ ላይ ክፍተት መኖሩን የኦዲት ቡድኑ ባከሄደው የማስረጃ ክለሳ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

152. በተጨማሪም በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች በክልል ደረጃ የግንዛቤ ዘዴዎችን በመጠቀም የተሠሩ ሥራዎች ቢኖሩም በየወቅቱ ከሚኖሩ መደበኛ ሥራዎች ጋር አስተሳስሮ ግንዛቤ እንዲሰጥ ከማድረግ በዘለለ ቋሚ የቴሌቪዥን የአየር ሥርጭት እንዲኖር ውል ገብቶ ከመሥራት አንፃር ጉድለት በመኖሩ የግንዛቤ ሥራ በሚፈለገው ደረጃ አለመሠራቱ፣ እንዲሁም በክልል ከተሞች ሥራ ፈላጊው ዜጋ ስለሚፈጠርለት የሥራ ዘርፍ አውቆ ወደ ሥራ እንዲሠማራ፣ በምግብ ዋስትና ፕሮግራም የታቀፉት ዜጎች እና በፕሮግራሙ ያልተካተቱ እንዲካተቱና የምግብ

ዋስትናቸው እንዲረጋገጥ የሚያስችል የግንዛቤ ሥራ ውጤት በሚያስገኝ መልኩ እየተሠራ አለመሆኑ፣ የፌደራል ኤጀንሲም ክልሎች በግንዛቤ አፈጣጠር ዙሪያ የአሠራር ሥርዓት ዘርግተው በሚፈለገው ደረጃ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ በዕቅዱ አካቶ ተከታታይ ድጋፍና ክትትል አለማድረጉን የኦዲት ቡድኑ ለሥራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስና ጉዳዩን አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ችሏል፡፡

153. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ላቀበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በፌደራል የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋሰትና ኤጀንሲ በኩል የዘርፉ ምክር ቤት አደረጃጀት መመሪያ መሠረት ለሥራ ዕድል ፈጠራው አስተዋጽኦ ያላቸውን 22 ሚኒስቴር መ/ቤትን በማንቀሳቀስና በማስተባበር የሥራ እድል ፈጠራው ማነቆ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቅጣጫ እየሰጠ እንዲፈቱ ቢደረግም አብዛኞቹ ተቋማት በቅንጅት የግንዛቤ አፈጣጠር ሥራ እየሠሩ አለመሆኑን እና በፌደራል ደረጃ ያለው የግንዛቤ አፈጣጠር ሥራ ሰፊ ክፍተት እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

154. በመሆኑም በጥቃቅንና አነሰተኛ አንቀሳቃሾች፣ በስራ ፈላጊ ወላጆችና በህበረሰቡ ላይ የሚታየውን የአመለካከትና የክህሎት ችግሮች ለመፍታት ወጣቱ ሥራ ፈጥሮ ከመሥራት ይልቅ ተቀጣሪነትን እንዲጠብቅ፣ ሥራ ፈላጊው ዜጋ በተለይም ምሩቃን የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው በጠየቁት መሠረት ተመዝግበው ከምዝገባ በኋላ ያሉትን የሥራ ሂደቶች ሳያልፉ፤ ለምሳሌ የአጭርና የረዥም ሥልጠና ሳይወስዱ እና ስለተፈጠረላቸው ሥራ ይዘትና ጥቅም ግንዛቤ ሳይሰጣቸው ወዲያው ወደ ሥራ እንዲገቡ ካላቸው ፍላጐት ባለመታገስ ከተመዘገቡ በኋላ በሥራ እድል ፈጠራው ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣ ወላጆች ልጆቻቸው በመንግሥት ሥራ ተቀጥረው እንዲሠሩ እንጂ በራሳቸው ሥራ ፈጥሮ መሥራት እንደሚችሉ ባለመገንዘብ በሥራ እድል ፈጠራ ተሠማርቶ መሥራት ዘላቂነት የሌለውና የተቀጣሪውን ህይወት ሊለውጥ አይችልም ብሎ ማሰብ፣ ዜጐች በልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ሥራዎች ላይ ተሰማርተው በሚከፈላቸው ክፍያ ኑሮአቸውን እንዳያሻሽሉ እና ጥሪት እንዲያፈሩ በሚደረገው ቤት ለቤት ምዝገባ እራሳቸውን እንዲደብቁ መሞከር

…ወዘተ የመሳሰሉ አመለካከቶች በሥራ ዕድል ፈጠራና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ በሚሆኑ ዜጎችና በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲፀባረቁ አድርጓል፡፡

## የኤጀንሲው የስልጠና ድጋፍን እንዲሰጡ ማደረጉን በተመለከተ

155. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 7 በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ የሥራ አመለካከት መቀየር የሚያስች የትምህርት፣ የስነ ልቦናና የክህሎት ሥልጠና እንዲሰጡ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

156. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት በከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ዙሪያ ማኑዋሎችን በማዘጋጀት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላት፣ ለተገልጋዮች፣ ለባለድርሻ አካላትና ለማህበረሰቡ የትምህርት፣ የስነ ልቦናና የክህሎት ሥልጠና እንዲሰጡ ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

157. ይሁን እንጂ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም ተገልጋዮች በወጡት ስትራቴጂዎችና የህግ ማዕቀፎች ላይ ተከታታይነት ባለው መልኩ እስከ ታችኛው የእርከን ደረጃ ወርዶ በስልጠና ከማብቃት አንጻር ክፍተት መኖራቸው፣ ለምሳሌ በአንዳንድ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች /በደቡብ ክልል፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በሀረሪ ክልል---ወዘተ/ ፈፃሚዎች በስትራቴጂዎች፣ በመመሪያዎች እና በማንዋሎች ላይ ማግኘት ያለባቸውን ሥልጠና በሚመለከተው አካል ባለመሠጠቱ ህጎቹን ተረድቶ የመሥራት ክፍተቶች መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

158. እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕርይዞች ልማት ቢሮ በሥራ ፈላጊነት የተመዘገቡ ዜጎች እንደ የቴክኒክና ክህሎት ስልጠና ፍላጐታቸው በ5ቱ ዘርፎች በድምሩ 90,000 ሥራ ፈላጊዎች የቴክኒክ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በድምሩ 23,689 ሥራ ፈላጊዎች ልጠና መስጠት ቢቻልም አፈፃፀሙ የእቅዱ 26.3% በመከናወኑ ዝቅተኛ መሆኑን አፈፃፀሙ ያሳያል፡፡ ይህም በዘርፎቹ ሲተነተን ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

- በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በድምሩ ለ23,400 ሥራ ፈላጊዎች የቴክኒክ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በድምሩ ለ6,756 ሥራ ፈላጊዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ የእቅዱ 28.9% መሆኑ፣
- በኮንስትራክሽን ዘርፍ በድምሩ ለ37,800 ሥራ ፈላጊዎች የቴክኒክ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በድምሩ ለ4,650 ሥራ ፈላጊዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ የእቅዱ 12.3% መሆኑ፣
- በከተማ ግብርና ዘርፍ በድምሩ ለ4,500 ሥራ ፈላጊዎች የቴክኒክ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በድምሩ ለ2,841 ሥራ ፈላጊዎች የቴክኒክ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ የእቅዱ 63.1% መሆኑ፣
- በአገልግሎት ዘርፍ በድምሩ ለ18,000 ሥራ ፈላጊዎች የቴክኒክ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በድምሩ ለ3,040 ሥራ ፈላጊዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ የእቅዱ 16.9% መሆኑ፣
- በንግድ ዘርፍ በድምሩ ለ6,300 ሥራ ፈላጊዎች የቴክኒክ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በድምሩ ለ6,402 ሥራ ፈላጊዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ የእቅዱ 101.6% መሆኑ፣

159. ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኦዲት ቡድኑ በናሙና ተመጥረው በታዩ 3 ክልሎችና 7 ከተሞች ባካሄዳቸው የማስረጃ ክለሳና ለሥራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠየቅ ከሰጡት መልስ የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ማንዋሎችን በማዘጋጀት እና እነርሱን መነሻ በማድግ ስልጠናዎች እየተሰጡ ሲሆን ከምግብ ዋስትና ጋር ተያይዞ ፕሮግራሙ በሙከራ ደረጃ እየተከናወነ ያለ በመሆኑ ለሚመለከታቸው አካላት መድረክ ተፈጥሮ ማንዋሎችን ግልጽ ለማድረግ የሚሠራው ሥራ በተፈለገውና ቀጣይነትን ጠብቆ በመሥራት ላይ የአፈፃፀም ክፍተቶች መኖራቸውና በፌደራሉም ተጠናክሮ ያልተሠራ ሥራ መሆኑ፣ በተጨማሪም ከሥራ ኃላፊዎች ከሰጡት መልስ ለማረጋገጥ እንደተቻለው፡-

- በከተሞች ለሥራ ፈላጊ ዜጋ የቁጠባ ጠቀሜታን፣ የብርድ አጠቃቀምና አመላለስ አስመልክቶ ተከታታይነት ያለው ሥልጠና የማይሰጥ መሆኑ፣

- በከተሞች በአንድ ማዕከል የአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ለሚቀጠሩ አዳዲስ ፈጻሚዎች ስለሥራውና የሥራው ማስተግበሪያ የህግ ማዕቀፎች ስልጠና ሳይወስዱ ወደ ሥራ እንደሚገቡ መደረጉ፣
- በክልልም ሆነ በፌደራል የተሰጡትም ስልጠናዎች ፈፃሚው በሠለጠነው መሠረት ውጤት ሊያመጣ የሚችል ሥራ መሠራቱን ተከታተይነት ያለው ክትትል አለመደረጉ፣

160. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የዘርፉ ልማት ስትራቴጂ /ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ እና የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ/ ከማስተግበሪያ ማኑዋሎቻቸው ጭምር ለክልል አመራሮች ፈፃሚያዎች እና ባለድርሻ አካላት ስልጠና በፊት ለፊት ገለፃ እና በኘላዝማ የተሰጠ ሲሆን የዘርፉ አስፈፃሚዎችና በተለይ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ላይ ያለው የሰው ኃይል በርካታ በመሆኑ አንፃር የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት የሥራ ማኑዋሎች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ጥረት ቢደረግም በየጊዜው እና በየደረጃው ሥልጠና የወሰዱ አመራሮችና ባለሙያዎች ዘርፉን ለቆ የመሄድና በዘርፉ ያሉትም ባለሙያዎች የወሰዷቸውን ሥልጠናዎች በአግባቡ ወደ ፈፃሚ ያለማውረድና ያለማስፋት ክፍተቶች መኖራቸውን መልስ ሰጥተዋል፡፡

161. በመሆኑም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ፈፃሚዎች እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚ እና አሰፈጻሚ አካላት በስትራቴጂዎች እና በህግ ማህቀፎች መሰረት በጥናት በተደገፈ መልኩ ሳይሰለጥኑ ቀጥታ ወደ ሥራ በመግባታቸው ለሥራ ፈላጊ ዜጐች የሥራ እድል ለመፍጠር ከክልል የወረደላቸውን ዕቅድ በታቀደው ልክ ባለመፈፀማቸው ምክንያት በክልሎች የሥራ አጥ ቁጥር እንዲጨምር አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የኤጀንሲው የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ

162. ኤጀንሲው ከፌደራል እስከ ክልል ባሉ ከተሞች የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የዳታ ቤዝ ልማት ሶፍትዌር በማልማት መረጃዎችን ሊሰበስብ፣ ሊይዝና ሊያሠራጭ ይገባል፡፡

163. በኦዲቱ ወቅት የፌደራል የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የዳታ ቤዝ ልማት ሶፍትዌር እንዲልማ በማድረግ መረጃዎችን መሰበስብ፣ መያዝና ማሠራጭ አለበት፡፡

164. ይሁን እንጂ የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትናን አፈፃፀም ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የሚያስችለውን ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት ከፌደራል እስከ ክልል ዘርግቶ ለመሥራት የዳታ ቤዝ ልማት ሶፍትዌር እንዲለማ በማደረግ ተግባራዊ አላደረገም፡፡

165. በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በሰባት የክልል ከተሞች ለሥራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስና ከተከለሰ ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ውጤት በሚያመጣ መልኩ ለመተግበር የሚያስችል በፌደራል ደረጃ የለማ የመረጃ ቋት ዝርጋታ ሥርዓት ባለመኖሩ መረጃዎችን እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች በኢተርኔትና በጽሑፍ የሚለዋወጡ ሲሆን የድግግሞሽ፣ የመጣረስና የመዘግየት ችግሮች የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡

166. ይህን አስመልክቶ ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ዳታ ቤዝ ልማት ሶፍትዌር ለምቶ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ቢደርግም በበጀት እጥረት ምክንያት ተፈጻሚ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

167. በመሆኑም በአብዛኞቹ ከተሞች ለምሳሌ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ፣ በአማራ እና በሀረሪ እንዲሁም በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ለዜጐች የሥራ ዕድል ፈጥሮ ወደ ሥራ ለማሠማራትና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚረዱ መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው ባለመያዛቸው ለሥራ ፈላጊዎች የሚፈጠረው የሥራ ዕድል እና የምግብ ዋስትና ለማን፣ በየትኛው የሥራ ዘርፍ፣ የት እንደተፈጠረ እና እንደተረጋገጠ በሚያሳይ መልኩ መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው እንዳይገኝ ከማደረጉም በተጨማሪም ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚላኩ ሪፖርቶች በተያዘላቸው ጊዜ ያለመላክ፣ የሚላከውም ሪፖርት እርስ በርስ መጣረስና የመደጋገም ችግሮች እንዲስተዋሉ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የሪፖርት አላላክና የግብረ መልስ

## አሰጣጥ ሥርዓትን በተመለከተ

168. ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራም አፈፃፀምን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላትና የክልል ከተሞች ወጥ የሆነ እና ወቅቱን የጠበቀ ጥራት ያለው ሪፖርት እንዲልኩ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግና የተላኩ ሪፖርቶችን ገምግሞ ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

169. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራም አፈፃፀምን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላትና የክልል ከተሞች ወጥ የሆነ እና ወቅቱን የጠበቀ ጥራት ያለው ሪፖርት እንዲልኩ ሊያደርግና የተላኩ ሪፖርቶችን ገምግሞ ግብረ-መልስ መስጠት እንዳለበት በአምስት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ /2008-2012/ መሰረት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

170. ይሁን እንጂ የፌደራል ኤጀንሲው ኃለፊነቱን ለመወጣት እንዲያስችለው በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ እና ተዓማኒነት ያለው መረጃ መሰብሰቢያ እና የሪፖርት ማቅረቢያ የአሰራር ማኑዋል ተዘጋጅቶ ለክልሎች እና ለከተማ አሰተዳደሮች ባለሙያዎች ስልጠና ቢሰጥም የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ፣ በአማራ፣ በሀረሪ ክልሎች ፣ በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬደዋ ከተማ አሰተዳደር ከህዳር 25 ቀን እስከ ታህሳስ 09 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ በ2010 በጀት አመት የዝግጅት እና የተግባር ምዕራፍ ሥራዎች ላይ በተደረገው ድጋፍና ክትትል ስራ ከተጠቃለለ ሪፖርት ለማወቅ እንደተቻለው፡-

- በክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች የሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች መያዝ የሚገባቸው ዝርዝር መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ በአግባቡ ተደራጅተው ያልተያዙ መሆኑን እና የተፈጠሩትም የስራ ዕድሎችን ጥቅል መረጃ ከመያዝ በዘለለ በጊዜያዊ የተፈጠረ የሥራ ዕድል ለማን፣ በየትኛው የስራ ዘርፍ፣ የት እንደተፈጠረ በሚያሳይ መልኩ መረጃ አለመያዙን፣
- ዝርዝር የኢንተርፕራይዞችን መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽን በተሟላ ሁኔታ ተይዘው እየተጠቀሙበት እንዳልሆነና ወጥነት ባለው የመረጃ የመሰብሰቢያ ፎርማት መሰረት ከማሰባሰብ አንጻር እጥረት ያለበት መሆኑ፣

- ኤጀንሲው እና ክልሎች የጋራ ዕቅድ አቅደው በወቅቱ ካለመላካቸውም በዘለለ በየዕሩብ አመቱ እና በየአመቱ የሚላከው የአፈጻጸም ሪፖርቶች ጥራት የሌለው መሆኑ፣ እንዲሁም በኤጀንሲው የዕቅድ አፈፃፀም ላይ የተገለፀው እና ከክልሎች የመጣው አፈፃፀም እርስ በርስ የሚጣረስ መሆኑን ከኤጀንሲው በጥር 02/2010 በተላከው የሪፖርት ግብረ መልስ በተጻፈ ደብዳቤ ለማወቅ ተችለዋል፡፡

171. በተመሳሳይ በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በሰባት ክልል ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለመጠይቅ ከሰጡት መልስ ከተሰበሰበ ማስረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለው በኤጀንሲ በሥራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያለውን የክትትል፣ የግምገማና የሪፖርት አቀራረብ እና ወቅታዊነቱን የጠበቀ ግብረ መልስ የአሰጣጥ ሥርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመኖሩን፣ እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚዎች በተደራጀ አግባብና ወቅታዊነቱን ጠብቆ ተገቢውን ሪፖርት እንዲልኩ ድጋፍና ክትትል ያለማድረግ ችግር መኖሩን ጠቅሰው ይህም ችግር በኤጀንሲው ለመቅረፍ የተሠራ ሥራ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

172. ስለሁኔታው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አጠቃላይ የስራዎችን አፈጻጸም አሰመልክቶ የጽሑፍ ግበረ-መልስ ከመስጠት ባለፈ የአካል ሱፐርቪዥን በማካሄድ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት ግብረ መለስ እንደሚሰጡ ጠቅሰው ክልሎች የሚልኩ የዕቅድ አፈፃፀም በመደበኛ በአምስቱ ዋና ዋና ዘርፎች ላይ የተፈጠረው የሥራ ዕድል ዘርፍ ተደምሮ የሚሰጠው አጠቃላይ ውጤት ከክልል የተወሰደው ጠቅላላ ድምር ጋር ሲነጻጸር እኩል እንደማይመጣና ከክልል የሚቀርቡ የግዙፍ ፕሮጀክቶች የተፈጠረ የስራ ዕድል አፈጻጸም በዋናው ሪፖርት አጠቃለው የማያቀርቡ በመሆኑ በዚህ ላይ ማስተካከያ ማደረግ እንደሚያስፈልግ መልሰ ሰጥተዋል፡፡

173. በመሆኑም የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲው በስራ እድል ፈጠራ እና በምግብ ዋስትና ስትራቴጂ መሰረት በክልሎችና በከተማ አሰተዳደሮች ለዜጐች የሥራ ዕድል ፈጥሮ ወደ ሥራ ለማሠማራትና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ለሚደረጉ አንቅስቃሴዎች የሚረዱ መረጃዎች በአግባቡ

ተደራጅተው ባለመያዛቸው በበጀት አመቱ በተያዘላቸው ጊዜና በተቀላጠፈ መልኩ እንዳይላክ ከማደረጉም በተጨማሪም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳሮች በትክከለኛው አፈጻጸማቸው  ማሰረጃ መሠረት ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዳይለይ እና ተገቢውን ድጋፍና ክትትል በወቅቱ እንዳያገኙ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

# ክፍል ሶስት

***መደምደሚያ***

174. ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኘሮግራም አፈፃፀምን በተመለከተ በፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በሶስት ክልሎች፣ በአንድ ከተማ አስተዳደርና በሰባት የክልል ከተሞች በታዩት ግኝቶች ላይ የሚከተለት የመደምደሚያ ሃሣቦች ላይ ተደርሷል፡፡

- ስለሆነም በከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኘሮግራም አፈፃፀምን በተመለከተ የዘረጋው የአሠራር ሥርዓት ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡
    - በከተሞች የሥራ እድል የሚፈጠርባቸው አምስት ዘርፎች/ የጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ የንግድ ዘርፍ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ እና የከተማ ግብርና ዘርፍ/ ማስፈጸሚያ የህግ ማዕፎች የአተገባበር ክፍተቶች ያለባቸው ከመሆኑም በላይ ሌሎች መውጣት ያለባቸው የህግ ማዕቀፎች ለምሳሌ ለከተማ ግብርና የሚሆን መሬት ለረጅም ጊዜ ለመጠቀም የሚያስችል የአሰጣጥ መመሪያ እና የከተማ ግብርና ዘርፍ የሚመራበት የከተማ ግብርና ፖሊሲ አለመውጣታቸው፣ የከተማ ግብርና ልማት ስትራቴጂ ቢዘጋጅም ያልፀደቀ መሆኑ፣
    - የጥቃቅንና ኢንተርኘራይዞች ልማት ስትራቴጂ በ2005 ዓ.ም የወጣ ቢሆንም በአፈፃፀም የታዩ ክፍተቶችን በመገምገም እስከ አሁን ማሻሻያ ያልተደረገበት መሆኑ፣
    - ኤጀንሲው ከክልል ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች ጋር የጋራ ዕቅድ አቅዶ እየሠራ ቢሆንም መደበኛ የግንኙነት ጊዜን መሰረት በማድረግ የዕቅዱን አፈፃፀም በጋራ የማይገመገሙ መሆኑን እና በአፈጻጸም ወቅት

ያጋጠሙትን ችግሮች በፍጥነት እየፈቱ እና አማራጭ መፍትሔ እያስቀመጡ ከመሄድ አንጻር ክፍተቶች መኖራቸው፣

- በኤጀንሲው አቅም የማይፈቱትን ችግሮች ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ ላይ ውስንነቶች መኖራቸው፣
- በክልሎች ለዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሮ ወደ ሥራ ለማሠማራት ፌደራልና ክልሎች የጋራ ዕቅድ አቅደው ወደ ሥራ ቢገቡም ሥራ አጥ ዜጎችን ከሥራ ዕድል ይፈጠርልኝ ጥያቄ ፍላጎት አኳያ እየተፈጠረ ያለው የሥራ ዕድል ፈጠራ በአምስቱም ዘርፎች /በጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ በንግድ ዘርፍ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ እና ከተማ ግብርና ዘርፍ/ በየበጀት ዓመቱ የሚታየው አፈፃፀም በአብዛኛው ዝቅተኛ በመሆኑ የሥራ ፈላጊውን ፍላጐት የማያሟላ መሆኑን፣
- ኤጀንሲው በሁሉም የክልል ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች የተናበበ ተቋማዊ አደረጃጀት እስከ ታችኛው መዋቅር እንዲፈጠር ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- በክልል ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች የዘርፉ አደረጃጀት ወጥነት የሌለውና የተበታተነ በመሆኑ የዘርፉ አደረጃጀት ራሱን ችሎ ተዋቅሮ መሥራት ሲኖርበት ከሌላ ዘርፍ ጋር ተለጣፊ ሆኖ መደራጀቱ፣
- በክልሎች የስራ ዕድል ፈጠራ ሥራ በአንድ ተቋም ተጀምሮ የማይጠናቀቅ በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አጋር አካላትን የሚያስተሳስር የአሰራር ስርዓት በአስገዳጅነት አለመኖሩ፣
- በዘጠኙ ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ከ2009-2010 በጀት ዓመት በአምስቱ የሥራ ዘርፎች ጥቅል አፈፃፀማቸው ከፍተኛ ቢያሳይም በየዘርፎቻቸው ሲታይ ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላቸው የሥራ ዘርፎች ያሉ መሆናቸው፣
- ከኤጀንሲው የተሰበሰበው ማስረጃና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች /አማራ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ/ የእቅድና አፈፃፀማቸው ሲነፃፀር ልዩነት የሚያሳይ መሆኑ፣

- ሥራ ለሌላቸው ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጠራና በኢንተርፕራይዞች ልማት ሥራ በየደረጃው የሚገኙ ዘርፉን እንዲመሩና እንዲያስፈፀሙ ኃላፊነት የተሰጣቸው ክልል አመራሮችና ፈጻሚዎች ለስትራቴጂው ትኩረት ሰጥቶ በወጥነት ከመተግበር አኳያ ውስንነቶች መኖራቸው፣

- በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አፈፃፀምን አስመልክቶ በኤጀንሲው የሚሰጠው ግብረ-መልስ ወቅታዊነት የሌለው መሆኑ፣

- ኤጀንሲው አዳዲስና አዋጭ የሆኑ የሥራ ዕድል አማራጮችን በጥናት በመለየት በየዘርፎቻቸው የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ወደ ክልሎች የወረደ ቢሆንም በፌደራልና በክልል ከተሞች ለሥራ ዕድል መጠቀሚያ የሚሆኑ የተፈጥሮ ጸጋዎችን ከመለየት፣ የተለዩትን በተደራጀ አግባብ ምን ያህል ሥራ ፈላጊ ሊሰማራባቸው እንደሚችል በሚያሳይ መልኩ በማመላከትና በማቀድ በተለዩት የአካባቢ ፀጋዎች ፈጥኖ ሥራ ፈላጊዎችን ከማሰማራት አንፃር ክፍተቶች የሚታይባቸው መሆኑ እና ተለዩ የተባሉትንም የአካባቢ ጸጋዎችን ወደ ታች በማውረድ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ በኩል በተሟላ መልኩ እየተሠራ አለመሆኑ፣

- በሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳሮች የሚገኙ የአንድ ማዕክል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ለተገልጋዮቻቸው ሁሉን አቀፍ አግልግሎት መስጠት እንዲያስችላቸው በአንድ ማዕክል አገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል መመሪያ 001/2010 እና የአንድ ማዕከል አግልግሎት መስጫ ጣቢያ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ለክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች ለትግበራ እንዲወርድ ቢደረግም የአንድ ማዕክል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በስታንዳርዱ መሠረት ለመሥራት በግብዓት የተሟሉ ባለመሆኑ ስታንዳርዱና መመሪያው በሚፈለገው ደረጃ እየተተገበረ አለመሆኑ፣

- ከዩኒቨርስቲዎች ከቴ/ሙ.ያ ምሩቃንና ሌሎች ሥራ ፈላጊዎችን በትምህርት ደረጃ፣ በጾታና በዕድሜ ለይቶ በትክክል መመዝገብን በተመለተ በክልል ከተሞች የሚገኙ አብዛኞቹ የአንድ ማዕከል ጣቢያዎች በተዘጋጀው መዝገብ

መሠረት በተሟላ መልኩ ከመመዝገብ እና የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን ዜጎች ከመዝገብ ላይ አቀናንሶ ከመሥራት አንጻር ክፍተቶች መኖራቸው፣

- በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለኢንተርፕራይዞች የሚገነባው የመስሪያና የመሸጫ ሼዶች ግንባታ፣ የለማ መሬት በወቅቱ፣ በተፈለገው መጠን የማዘጋጀት እና ግንባታቸው በተጠናቀቁ የማምረቻና መሸጫ ሕንጻዎችና ሼዶች ለተጠቃሚዎች ከመተላለፋቸው በፊት አስፈላጊውን መሠረተ ልማቶች በማሟላት ላይ የሥራ ክፍተቶች መኖራቸው፣
- አንቀሳቃሾች በውዴታ የቆጠቡትን ገንዘብ በፈለጉበት ጊዜና ወቅት ማውጣት ያለመቻላቸው ለቁጠባው መደበኛ ባንኮችን የሚመርጡ መሆናቸውና ግዴታ ካልሆነ በቀር በአነሰተኛ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለመቆጠብ ፍላጎት አለመኖር፣
- በኢንተርፕራይዞች የተረጋጋ የቁጠባ ሥርዓት የሌለ መሆኑ፣
- ለኢንተርኘራይዞች የሚሠራጨው ብድር በታቀደው ልክ አለመፈፀሙና የተሰራጨውን ብድር ወቅቱን ጠብቆ ያለማሰመለስ ችግሮች በመኖራቸው መልሶ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ አዳዲስ ኢንትርፕራዞች ለማበደር ማነቆ መሆኑን፣
- ኢንተርኘራይዞች መደበኛ ብድር ቁጠባ ለመውሰድ 20 በመቶ የቅድመ ብድር ቁጠባ፣ የቤት ካርታ እና የመኪና ሊብሬ ያለው ዋስትና የሚጠየቁ በመሆኑ አገልግሎቱን ማግኘት አለመቻል፣
- የፋይናንስ ተቋሞች ቀልጣፋና ዘመናዊ አገልግሎት ለኢንተርኘራይዞች አለመስጠታቸው፣
- የብድሩ ተጠቃሚ የሆኑት ኢንተርኘራይዞች የሚሰጣቸውን ብድር ለታለመለት ዓላማ ያለማዋል ችግር አለመኖሩና የክልል ፈፃሚዎች ብድሩን የማስመለስ ሥራዎች ላይ የሥራ ክፍተቶች ያሉባቸው መሆኑ፣
- የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ ኢንተርፕራይዞችን በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ፣ በመደገፍ ከሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ካደረጋቸው፡-

- ✓ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሚገነባው የመሥሪያ ሼድ እና የመሸጫ ሼድ ከክልል ከተሞች ውጭና ለግብይት በማይመች ቦታ በመሆኑ፣
- ✓ በክልል በሚገኙ ከተሞች የገበያ ዕድሎችን የሚያሳድጉ ባዛርና ኢግዚብሽን አለማከሄድ፣
- ✓ የምርት ማሳያና መሸጫ ማዕከል አለመኖሩና የግብዓት አቅርቦት ችግር መኖሩ፣
- ✓ በፌደራልና በክልል በጀት በሚሠሩ ፕሮጀክቶች ትስስር ለመፍጠር የአሠራር ወጥነት አለመኖር፣
- ✓ የሚፈጠረው የገበያ እድልና የተደራጀ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር አለመመጣጠን፣
- ✓ የመንግሥት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎችና ሆስፒታሎች የሚፈጠሩትን ሥራዎች ላይ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር አለማድረግ፣
- ✓ የገበያ ትስስር ባለመኖሩ ወደ ሥራ ገብቶ የስራቸውን ምርቶች በመሸጥ ተጠቃሚ መሆን አለመቻል፣
- ✓ በሥራ እድል ፈጠራ ዙሪያ የተደራጁትን ከማበረታታት አንፃር ማለትም ገበያ ፈላጊዎችን ከምርቱ ተጠቃሚ አካል ጋር የማስተዋወቅ ክፍተት መኖሩ፣
- ✓ በምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ለመተግበር በኤጀነሲው የተላከው የህግ ማዕቀፎች እስከታችኛው እርከን ደረስ በማውረድ እንዲተገበሩ አለመደረጉ እና በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙት ችግሮችን ለይቶ በማውጣት በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ፣

- የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ቀድሞ ከተመረጡ 11 ከተሞች በተጨማሪ በአዲስ መልክ የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም የሚተገበርባቸውን 44 ከተሞች በፌደራል ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ

ከተሞችን የመለየት ስራ ቢሠራም ኘሮግራሙ በአዲስ መልክ የሚተገበርባቸው ከተሞች የሚያስፈልገውን የበጀት ምንጭ በመንግሥት ደረጃ ለምን ያህል ከተሞች ማስተግበሪያ እንደሚያስፈልግ ተወስኖ ባለመጽደቁ የልየታ ሥራው ብቻ የተፈፀመ መሆኑ፣

- ኤጀንሲው በስትራቴጂው መሠረት ሥራዎችን መሠራታቸውን ለማረጋገጥ በክልል ደረጃ ከማሳወቅና በጋራ ተናቦ ከመሥራት ይልቅ አልፎ ቀጥታ ወደታች ከሚገኙ ከክልል ከተሞች ቢሮዎችና ፈፃሚ አካላት ጋር አሰራሮችን የመከታተል ሁኔታ በመኖሩ በክልል ደረጃ ያሉ የሥራ ኃላፊዎች ወደ ፈፃሚዎች ወርዶ ክትትል የማድረግ ውስንነቶች መኖራቸው፣
- በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመለየትና በመፍታት የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች ወደ ዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ እንዲታቀፉ የቅድመ ዝግጅት እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችል ማኑዋሎችን በማዘጋጀት የክህሎት ስልጠናዎች የመሰጠት እና የተገልጋዮች እርካታ ለማወቅ የሚስችል ዳሰሳ ጥናት በእቅድ ይዞ አለመሰራቱ፤
    - ✓ በአከባቢ ልማት ስራዎች በአተገባበሩ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍቻ ማኑዋል በወቅቱ ፀድቀው ወደ ሥራ ባለመግባታቸው ስትራቴጂውን ተረድቶ በመሥራት ላይ የሥራ ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን፣
    - ✓ በሁሉም ክልሎችና ከተሞች ልዩ ድጋፍ የሚያሰፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የተሀድሶ አግልግሎት ማግኘት እንዲችሉ የልየታ ረቂቅ ማኑዋል እና የድርጊት መርሃ-ግብር ረቂቁ ሰነድ ጸድቆ ስራ ላይ አለመዋሉ፣
- ህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር እንዲላቀቅ የተቀመጡ አማራጮች ላይ በየደረጃው ለሚገኙ ፈፃሚዎች ተከታታይነት ያለው እና ሊያሠራ የሚችል ስልጠና በየእርከኑ አለመሰጠቱ፣

- በልየታ ወቅት የማይገባቸውን ቤተሰቦችን እንዲጠቀሙ የማደረግ ችግር ሲኖር መጠቀም ያለባቸው እንዳይካተቱ የማደረግ ችግር መኖሩ፣
- በአከባቢ ልማት ስራዎች ለሚሳተፉ ዜጎች በአረንጓዴ ልማት፣ በተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት፣ በውብት፣ በመናፈሻ እና ዘላቂ ማሪፊያ ልማት አሰተዳደር፣ በጽዳት አሰተዳደር፣ የአከባቢ ጥበቃና ሌሎች በተቀናጀ መልኩ ለምግብ ዋስትና ትግበራ በተመረጡ ከተሞች ህበረተሰቡን በሚፈለገው መልኩ አለማሳተፉ፣
- በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎች በአከባቢ ልማት ስራዎች ላይ በማሳተፍ የበጀት እጥረት፣ የአቅም ግንባታ ችግሮች፣ የነጻ የህክምና አግልግሎት አለማግኘት እና የልማትና የሴፍቲ መሣሪያዎች በወቅቱ አለመሟላቱ፣
- ኤጀንሲው የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና አፈጻጸም ለማረጋገጥ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ከግልና ከመንግስት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን እንዲሁም በከተሞች የምግብ ዋስትና የሚውል ሀብት ከህበረተሰቡ፣ ከባለደርሻ አካላትና የልማት አጋሮችን በማሰተባበር የሚፈለገውን ሀብት በአገር ውስጥ በማሰባበሰብ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ አለማድረጉ፣
- ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያሰችሉ ኘሮጀክቶችን የሚገመግምበት የግምገማ ሠነድ (Project appraisal Document) አዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን ወደ ክልልና ከተማ አስተዳደሮች የተላከ አለመሆኑ፣
- የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት የተጋለጡ እና ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ቢሠራም ከማያስችሉት ውስጥ፡-
    - ✓ በፌደራሉና ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተከታታይነትና ዘላቂ የሆነ የግንዛቤ አፈጣጠር ሥራ በወጥነት እስከ ታችኛው እርከን ያለመሥራት፣

- ✓ በዘርፉ የተሟላና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ድጋፍ መስጠት የሚችል አመራርና ባለሙያ እጥረት መኖሩ በየደረጃው ለዘርፉ ልማት በቂ በጀት አለመመደብ፣
- ✓ ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች በቀጥታ ድጋፍና በአከባቢ ልማት ሥራዎች በማሳተፍ የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ የግብዓት ችግሮች መኖራቸው፣
- ✓ በልየታ ወቅት ከነበረው የጥራት መጓደል የቀጥታ ድጋፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተቀመጠው ቁጥርና መጠቀም የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር ያለመጣጣም ችግር መኖሩ፣

- ኤጀንሲው የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና አፈፃፀም ዙሪያ የሚሰጠው አገልግሎት ተከታታይነት ያለው የጋራ መድረክ እና የእርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ መደረክ በመፍጠር እየሠራ አለመሆኑ፣
- ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከባለድርሻ አካላትና የዘርፉ አጋሮችን የትብብር መስኮችን በመለየት፣ መደበኛ የዕቅድ ዝግጅትና የአፈፃፀም የግምገማ ግንኙነት ጊዜ ጠብቆ የመገምገም እና በታቀደው ልክ የመፈጸም ችግሮች መኖራቸው፣
- ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸምን ውጤታማ ለማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ መፍትሄ የሚሹ የግብዓት ችግሮችን (ትራንስፖርት፣ ውሃ. መብራት፣ የመስሪያ ቦታ፣ የመሸጫ ቦታ፣ ጥሬ እቃ….) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ችግሩን እየፈታ አለመሆኑ፣
- ኤጀንሲው ሥራ ፈላጊዎች እንደየ ፍላጐታቸውና ችሎታቸው የሚሠማሩበት የሥራ ዘርፎችን ፓኬጅ ቀርጾ ወደ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ቢልክም ፓኬጅ መሠረት የስራ ዕድል እየተፈጠረ አለመሆኑ፣
- ኤጀንሲው በዘረጋው ሥርዓት መሠረት ከሚዲያ ጋር በመቀናጀት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር፣ የሕዝብ መድረኮች በመፍጠርና የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም በከተሞች የምግብ

ዋስትና ማረጋገጥና የሥራ ዕድል አፈጣጠር ላይ ተከታታይነት ያለው እና በሚፈለገው ደረጃ እስከ ታችኛው እርከን ወርዶ ለተገልጋዮች፣ ለማህበረሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ አለመፍጠሩን

- ኤጀንሲው በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም ተገልጋዮች በወጡት ስትራቴጂዎችና የህግ ማዕቀፎች ላይ ተከታታይነት ባለው መልኩ እስከ ታችኛው የእርከን ደረጃ ወርዶ በስልጠና ከማብቃት አንጻር ክፍተት በመኖሩ ምክንያት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ስራተኞች ስልጠና ሳያገኙ እንዲሰሩ መደረጋቸው፣
- ኤጀንሲው  የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትናን አፈፃፀም ዙሪያ ከፌደራል እስከ ክልል ከተሞች ዘመናዊ የመረጃ  አሰባሰብ፣ አያያዝና ልውውጥ ለማገዝ የሚየስችል የዳታ ቤዝ ልማት ሶፍትዌር አልምቶ ተግባራዊ አለማደረጉ፡፡

- ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከኤጀንሲው ጋር ባቀዱት የጋራ እቅድ መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ኘሮግራም አፈፃፀም ዙሪያ የተሰሩ ሥራዎችን ሠርተው በወቅቱ እና ጥራቱን የጠበቀ የአፈፃፀም ሪፖርት መላክ ላይ ውስንነቶች መኖራቸው፣

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሣቦች

የፌደራል የከተሞች የሥራ እድል አጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በከበሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኘሮግራም ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች በሀገራችን የሚኙትን ሥራ አጥ ዜጐች ከመቀነስና መሥራት ለማይችሉ የቀጥታ ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም በኘሮግራሙ የታቀፉ ዜጐችን በአከባቢ ልማት በማሠማራት እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከምግብ እጦት ችግር ከማላቀቅ አንፃር የሚሠሩ ሥራዎች የሚፈለገውን ውጤት በሚያመጣ መልኩ በወጥነት እየተሠራ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል በኦዲቱ ወቅት የታዩትን የአሠራር ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች ቀርበዋል፡፡

- ኤጀንሲው በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 በተቀመጠው መሠረት የሥራ እድል ፈጠራ ሥራዎችን ለማፋጠን የሚረዱ የህግ ማዕቀፎችና ስትራቴጂዎችን በማፀደቅና በስራ ላይ በማዋል እንዲሁም ማሻሻያ ያልተደረገላቸው የህግ ማዕቀፎችን በአተገባበር ላይ የሚፈጥሩት ክፍተቶችን በጥናት በመለየት እና በመገምገም ወቅታዊ እንዲሆኑ በማሰደረግ ከፌደራል እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ወርደው ወጥነት ባለው መልኩ ተፈጻሚ እንዲሆኑ በመደገፍ፣ በማስተባበር እና ህጉን ተከትለው የማይሠሩ አካላትን በመከታተል ለበላይ አካላት በማሳወቅ፣ በአስገዳጅነት እንዲፈጸሙ እና የተጠያቂነት ሊያመጣ የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ በስራ ላይ በትክክል አፈፃፀሙን ሊከታተል እንዲሁም በሥራ ዕድል ፈጠራን አስመልክቶ የሚሰጡ አገልግሎቶች እና ድጋፎች እሰካሁን ያመጡትን ለውጥ በጥናት በማረጋገጥና በመገምገም የማሰተካኪያ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ለዜጐች የሥራ ዕድል ፈጥሮ ወደ ሥራ ለማሠማራት እንዲቻል በአምስቱም በዕድገት ተኮር ዘርፎች በሚገኙት ዝርዝር ንዑስ የስራ መሰኮች መሠረት የዘርፉን ሀገራዊ የልማት

ዕቅድ በማዘጋጀት የግንኙነት ጊዜ ጠብቆ በታቀደው የጋራ ዕቅድ መሠረት መተግበሩን በመከታተልና በመገምገም በአፈጻጸሙ ወቅት ያጋጠሙትን ችግሮች በፍጥነት እየፈቱ እና አማራጭ መፍትሔ እያሰቀመጡ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በማሰደረግ በኤጀንሲው አቅም የማይፈታውን ለሚለከተው አካል በማሳወቅ ችግሩ እንዲቃለል ክትትል በማደረግ እንዲሁም ክፍተቶቹ መታረማቸውን በማረጋገጥ እሰከታችው መዋቅር ድረስ በየበጀት ዓመቱ ሥራ አጥ ዜጐች ከሥራ ዕድል ይፈጠርልኝ ጥያቄ ከፍላጎት አኳያ በሚያሟላ እና በተናበበ መልኩ በታቀደው ልክ አፈፃፀሙን ዕቅድ ይዞ በመከታተል ሊሰራ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው ከፌደራል እስከ ክልል ከተሞች በጥናት የተደገፈ የተናበበ አደረጃጀትና የተጠናከረ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት እና አጋርነት በመፍጠር የስትራቴጂው ማስፈፀሚያ ስልቶችን ወደ ፈፃሚው በመላክ መፈጸማቸውን እስከታችኛው እርከን ወርዶ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ በከተሞች እየተበራከተ የመጣውን የስራ ፍላጎትና የሥራ አጥ ቁጥር ትረጉም ባለው ሁኔታ ሊቀንስ በሚያስችል መልኩ በወጥነት በመናበብ ሊሥራ እና የማያሠሩ ማነቆዎችን በጋራ ለይቶ በማውጣት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት እና የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ በማሰደረግ ማስፈፀሚያ ስልቶቹ ውጤት ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ የተናበበ አደረጃጀት ስርዓት ዘርግቶ እንዲፈጸሙ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩ ሥራ ለሌላቸው ዜጐች አዳዲስ አዋጭ የሆነ የሥራ ዕድል አማራጮችን፣ ከፌድራል ከተሞች እሰከ ክልል ከተሞች የሚገኙ ጸጋዎችን በጥናት በመለየት የተለዩትን በተደራጀ አግባብ ምን ያህል ሥራ ፈላጊ ሊሰማራባቸው እንደሚችል በሚያሳይ መልኩ በማመላከት፣ ለክልሎች እና ለከተሞች በማውረድ በየደረጃው የሚገኙ ዘርፉን እንዲመሩና እንዲያስፈፀሙ ኃላፊነት የተሰጣቸው አመራሮችና ፈጻሚዎች ጋር በመሆን እስከታችኛው እርከን ድረስ በመውረድ ስራ ፈላጊዎችን በየዘርፎቻቸው እንዲደራጁ በማሰደረግ በተለዩት የስራ መስኮች መሰረት በትክክል መሰማራታቸውንና ተጠቃሚ መሆናቸውን መናበብ እንዲቻል የድጋፍና የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ በተሟላ መልኩ ሊደግፍ፣ ሊያስተባብር አፈፃፀሙንም ሊከታተል እና በሚታዩ ጉድሎቶች ላይ በቅርበት በመስራት የማስተካከያ

እርምጃ እንዲወሰድ በማደረግ እና የስራ እድል አማራጮችን እንዲፈጠሩ ትርጉም ባለው መልኩ ሊሰራ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው በሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች የሚገኙ የአንድ ማዕክል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ለተገልጋዮቻቸው ሁሉን አቀፍ አግልግሎቶች መስጠት እንዲያስችላቸው በተዘጋጀው የአሰራርና አገልግሎት አሰጣት ስታንዳርድ መሠረት መተግበሩን የድጋፍና የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ በክልል ደረጃ ካሉ ፈፃሚ አካላት ጋር በመሆን እስከ ማዕከላት ወርዶ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በስታንዳርዱ መሠረት ለመሥራት ማነቆ የሆኑትን ችግሮች ለይቶ በማውጣት በየጊዜው የማሻሻያ ሥራ ሊሠራ በተሻሻለውም መሠረት በትክክል መተግበሩን ሊከታተል እና ተገልጋዮችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በአምስት አመቱ ስትራቴጂክ /2008-2012/ ዕቅዱ እና ድርጅታዊ የጥናት ሰነዱ ላይ ባስቀመጠው መሠረት ከዩኒቨርስቲዎችና ቴክኒና ሙያ ኮሌጆች ተመርቀው የሚወጡ ምሩቃንና ሌሎች ሥራ ፈልገው የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው የሚጠይቁ ሥራ ፈላጊ ዜጎችን በ9 ክልሎችና በ2 ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በሚመለከታቸው ባለድሻ አካላት በትምህርት ደረጃ፣ በጾታ፣ በዕድሜ ተለይተው በአግባቡና በትክክል እንዲመዘገቡና ወደ ስራ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጠር በማደረግ ትርጉም ባለው መልኩ ሥራ እንዲፈጠርላቸው የሚያስችል የድጋፍና የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ሊሠራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የሥራ ዕድል ለተፈጠረላቸው ዜጎች አገልግሎት የሚውሉ አዳዲስ የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ግንባታ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነው የለማ መሬት በወቅቱና በተፈለገው መጠን እንዲዘጋጅላቸው፤ እንዲሁም ግንባታቸው በተጠናቀቁ የማምረቻና መሸጫ ሕንጻዎችና ሼዶች ለተጠቃሚዎች ከመተላለፋቸው በፊት አስፈላጊው መሠረተ ልማቶች እንዲሟላላቸው ከፌደራል እስከ ክልል ካሉ ፈፃሚ አካላትና ጉዳዩ ቀጥታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የመስሪያና የመሸጫ ፍላጎት ችግርን በሚቀርፍ መልኩ በቅርበት ሊሠራ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ሊደግፍ፣ ሊያስተባብርና ሊከታተል፣ በስራ እድል ፈጠራ ስራ የሚውል የመሰረተ ልማትን ለማሟላት ትኩረት ሰጥተው የማይሠሩ የሚመለከታቸው አካላትን

ተጠያቂነት ሊያመጣ በሚያሰችል መልኩ ለመንግሥት በማሳወቅ ችግሩ እንዲፈታ የማስተካከያ እርምጃ ሊያስወስድ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጐች በሚያገኙት ገቢ ቆጠበው እና በሚሠጣቸው ብድር ወደ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሥራ ሂደት እስከ ሚተላለፉ ድረስ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸው ወደ ስራ የሚገቡ ዜጎች ጥቃቅንና አነሰተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያገኙትን ገቢ በዘርፉ ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ቁጠባ መቆጠብ እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም የተሰጠውን ብድር ለታለመለት ዓላማ እንዲውልና በወቅቱ የተሠራጨውን ብድር ከማስመለስ በተጨማሪ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ስራቸውን ለመጀመር ወይንም ለማስፋፋት በሚያሰችል መልኩ በታቀደው ልክ የብድሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑና የፋይናንስ የብድር አቅርቦትን ችግር ለመፍታትና ለማመቻቸት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ በጋራ ሊሠራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ ኢንተርፕራይዞችን በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ፣ በመደገፍ እና ተደራሽነት ያለው ባዛርና ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት፣ የገበያ ዕድል ከሚፈጥሩ ከግልና ከመንግስት ተቋማት ጋር /ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከሆስፒታሎች፣ ከማረሚያ ቤቶች..ወዘተ/ ጠንካራ የሆነ ግንኙነት ፈጥሮ በሀገር ውስጥ የገበያ ተስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ እርስ በራሳቸው የገበያ ትስስር እንዲፈጠር በማሰደረግ በተጨማሪ ዘላቂ በሆነ መልኩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲ ገበያዩ እንዲቻል የገቢያ ትስሰር ጥናቶችን በማጥናት ተግባራዊ በማደረግ ገበያ ፈላጊዎችን ከምርቱ ተጠቃሚው አካል ጋር እንዲተዋወቅና አንዲገናኙ እንዲሁም በየክልሉ ኢንተርፕራይዞችን ለማበረታት በገቢያ ተስስር መመሪያ የታገዘ አፈጻጸም እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጠሩ በማመቻቸት ቀልጣፋና ውጤት አምጪ ድጋፍና ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ነድፎ መርሃ ግብሮችንና የህግ ማህቀፎችን እሰከታችኛው እርከን ድረስ በመወረድ በአተጋባበሩና በአፈፃፀሙ ዙሪያ ዕቅድ አውጥቶ በሚፈለገው ደረጃ የክልል እና ከተማ አስተዳደር ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፈፃሚዎች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂን እና

የስትራቴጂ ማስፈፀሚያ ስልቶችን በትክክል በስራ ላይ ተግበባራዊ በማደረግ አፈጻጸማቸውን በጥናት በማደረግ እና በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙትን ችግሮች ተለይተው በወቅቱ መታረማቸውን በማረጋገጥ እንዲሁም በጥናቱና በስትራቴጂው መሰረት እስካሁን የድጋፉ አሰጣጥ ውጤታማነትን እሰከታችኛው መዋቅር ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ድጋፍ እና ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው በ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ማሰረጃ መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ቀድሞ ከተመረጡ 11 ከተሞች በተጨማሪ በአዲስ መልክ የከተሞች የምግብ ዋስትና ኘሮግራም የሚተገበርባቸውን 44 ከተሞች በፌደራል ደረጃ ተግባራዊ ለማደረግ ከተሞችን የመለየት ስራ መስራታቸውን በ2010 በጀት አመት ዕቅድ አፈጻጸም ላይ በተጠቀሰው መሰረት በኘሮግራሙ አተገባበር ዙሪያ የሚያሰፈልገውን በጀት ምንጭ በመንግሥት ደረጃ ለምን ያህል ከተሞች ማስተግበሪያ እንደሚያስፈልግ በማስወሰንና በማጸደቅ በመርሃ ግብሩ ዕቅድ መሠረት በአዲስ መልክ የሚተገበርባቸውን ከተሞችን ላይ ተደራሽነት ባለው መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተስብ ክፍሎችን ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ከፌደራል እስከ ክልል ታችኛው መዋቅር ድረስ ወጥ የሆነ የኘሮግራም ማስፈፀሚያ አሠራርና አደረጃጀት ስርዓት በሁሉም ክልሎችና ከተሞች በወጥነት ሊዘርጋና በኑሮ ማሻሻያ የሚደረገው እንቅስቃሴ ችግር ፈቺ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆንና ኘሮግራሙ ባልተተገበረባቸው ከተሞች እንዲተገበር የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ በሁሉም ከተሞች ውጤት በሚያመጣ መልኩ ድጋፍና ክትትል በማደረግ ሊሠራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሀብት ከህብረተሰቡ፣ ከባለድርሻ አካላትና ከልማት አጋሮች እንዲሰበሰብ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ እና የምግብ ዋስትናን ፕሮግራም ቀጣይነት ያለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡
- ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያሰችሉ ኘሮጀክቶችን የሚገመግምበት የግምገማ ሠነድ (Project appraisal Document) በማዘጋጀት ኘሮግራሙ ወደ ሚተገበርባቸው ከተሞች ልክ፣ ከተሞችም ለዜጐች የምግብ ዋስትናቸው

ሊያረጋግጥ በሚያስችል መልኩ ሥራዎችን እየሠሩ መሆኑን በመገምገሚያው ሰነድ መሠረት ክትትል በማድረግ በሁሉም ክልልከተሞችና ከተማ አሰተዳደሮች ላይ የፕሮጄክቱ አፈጻጸሙ ቀልጣፋና ውጤቴማነቱን በመገምገም በአሠራር ላይ ያጋጣሙ ችግሮችን ለይቶ በማውጣት በወጥነት የማስተከከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት ለየተጋለጡ እና ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች  የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል  ከፌደራል እሰከ ክልል ከተሞች በወጥነት በአከባቢ ልማት ስራዎችና በቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ መሆኖቸውን በጥናት በማረጋገጥ በዘላቂነት እያንዳንዱ ግለሰብ የነፍስ ወከፍ የምግብ የዕለት ፍጆታን እሰከ 2200 ካሎሪ እንዲደረስ እና የተመጣጠነ የስርዓት ምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ  እና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ለማደረግ ሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ዘርግቶ ውጤት የሚያመጣ ተከታታይነት ያለው ስራ ሊሠራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በኑሮ ማሻሻያ ለሚታቀፉ ዜጎች በሚኖሩበት አከባቢ ምቹ አደረጃጀቶችን በመፍጠር በቀላሉ ገቢያቸውን ሊያሳድጉ የሚያስችላቸውን አሰራሮችን በሁሉም ክልሎች እና ከተሞች በኩል ላይ በተሟላ ሁኔታ ሥርዓት በመዘርጋት አፈጻጸሙን ሊከታተልና ድጋፉ በኑሮ ማሻሻያ በታቀፉ ዜጎች  ላይ  ያመጣውን የኢኮኖሚ  ለውጥ መመዘን በሚያስችል መልኩ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በከተሞች ለዜጐች የሚፈጠረው የሥራ እድል ፈጠራና ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጐች የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ የሚሠራው ሥራ የሚፈለገውን ችግሮችን ለመፍታት በሚያስችልና የኢኮኖሚ ለውጥ ከማስገኘት የፌደራል ከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ  ከፌደራል እስከ ክልል ከተሞች እና ከተማ አስተዳደሮች ታችኛው መዋቅር ድረስ በመወረድ ቋሚ እና ወጥነት ያለው መድረክ በማዘጋጀት የእርስ በእርስ ልምድ ልውውጥ የጋራ መድረክ የሚፈጥርበት ሥርዓት ዘርግቶ ሊሠራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ እና ለዜጐች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው የዘርፉ አጋሮችን የትብብር መስኮችን በመለየት፣ ከሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላትና ባለድርሻ አካላት የስምምነት ሰነዶችን በማዘጋጀትና በመፈራረም

በተሟላ መልኩ በጋራና በተናጥል በማቀድ አፈጻጸሙንና አተገባበሩን በጋራ በመገምገም የሚያጋጥሙትን ችግሮችን በቅንጅትና በጋራ በመፍታት በከተሞች የሥራ እድል ፈጠርና የምግብ ዋስትና ስራዎችን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈጸም በሰምምነት ሰነዱ መሰረት አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው ለዜጐች በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራ እንዲፈጠርላቸው እና የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥላቸው ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፈጻሚና አሰፈጻሚ አካላት እንዲሁም በባለድርሻ አካላት አካላት የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ወጥና ዘላቂነት እንዲኖረው በሥራ ዕድል ፈጠራና በምግብ ዋስትና ኘሮግራም ዙሪያ የሚሠሩ ስራዎች በተቀናጀና በተናበበ ሁኔታ ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸምን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማደረግ እንዲቻል በአገር አቀፍ ደረጃ መፍትሄ የሚሹ የግብዓት ችግሮችን (ትራንስፖርት፣ ውሃ. መብራት፣ የመስሪያ ቦታ፣ የመሸጫ ቦታ፣ ጥሬ እቃ….) እንዲሁም በምግብ ዋሰትና ፕሮግራም ኑሮአቸውን ለማሻሻል በአከባቢ ልማት ላይ ተሰማርተው እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለሚረዱ ዜጐች የመሥሪያ መሳሪያዎች እና የአደጋ መጠበቂያ ቁሳቁሶች ችግር ፈቺ በሆነ መልኩ እንዲቀርፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲሟላላቸው የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመፍጠር ሊስራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሥራ ፈላጊዎች እንደየ ፍላጐታቸውና ችሎታቸው የሚሠማሩበት የሥራ ዘርፎችን ፓኬጅ ቀርጾ ወደ ክልሎች እና ከተማ አሰተዳደሮች በላከው መሠረት በክልሎችና በከተሞች ላይ ክትትል በማድረግ የሥራ ዘርፎችን ፓኬጅ መሠረት የማይሰሩትን ክልሎችና ከተሞችን በመለየት እንዲሁም በወረደው ፓኬጅ መስረት ያልተተገበሩትን ዘርፎችን ከፍተት ለይቶ በማውጣት በማጥናት ውጤት በሚያመጣ መልኩ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ እና የፓኬጆቹ አፈጻጸም ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ከላይ እስከታች ባሉ ከተሞች የመረጃ ልውውጡ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆንና መረጃዎች በጥራት እና በፍጥነት ለመሰብሰብ፣ ለመያዘና ለማሠራጨት የዳታቤዝ ማዕከላት እንዲገነባ በማሰደረግና ልማት ሶፍትዌር በማልማት

ከፌደራል እስከ ክልል ከተሞች የሚያገናኝ የመረጃ ቋት ዝርጋታ ሥርዓት ተግባራዊ በማደረግ የመረጃዎች ወቅታዊነት ችግር በመቅርፍ ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ሊሠራ ይገባል፡፡


- ኤጀንሲው ከሚዲያ ጋር በመቀናጀት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር፣ የሕዝብ መድረኮች በመፍጠርና የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ሰትራቴጂዎችን ከማሰተዋወቅና እንዲሁም በዘርፉ የወጡትን የአሰራር የህግ ማዕቀፎች ዙሪያ በከተሞች የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የሥራ ዕድል አፈጣጠር እሰከታችኛው እርክን በመወረድ በጥናት ላይ የተደገፈ ለሁሉም ማህረሰብ ተደራሽነት ያለው የሕዝብ መድረኮች በመፍጠር የተዛባ አለመለካከትን ለመቀየር የሚያስችልና ውጤት በሚያመጣ መልኩ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ሊሰጥ እንዲሁም የተሰጠው ግንዛቤ ምን ውጤት እንዳመጣ በጥናት በማረጋገጥ እሰከታችኛው እርከን በመወረድ ከፍተቶችን ለማረም በሚያስችል መልኩ ለሲራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኘሮግራም ዙሪያ ማንዋሎችን በማዘጋጀት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላት፣ ለተገልጋዮች፣ ለባለድርሻ አካላትና ለማህበረሰቡ እንዲሁም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የትምህርት፣ የስነ ልቦናና የክህሎት ትምህርትና የሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል በፍኖተ ካርታ በመተጋዝ እና ስልጠናውን ለማካሄድ የሚያግዙ ሰነዶችን በማዘጋጀት እሰከታችኛው መዋቅር በማወርድና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በከተሞች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርና በምግብ ዋስትና ኘሮጀክት ሥራ የሚያደርገው እንቅስቃሴ አፈጻጸሙ ወጥነት ያለው እና ውጤት አምጪ በሆነ መልኩ እንዲተገበር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ከላይ እስከታች ባሉ ከተሞች የመረጃ ልውውጡ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆንና መረጃዎች በጥራት እና በፍጥነት ለመሰብሰብ፣ ለመያዝና ለማሠራጨት የዳታቤዝ ማዕከላት እንዲገነባ በማሰደረግ የሶፍትዌር ልማት በማልማት ከፌደራል እስከ ክልል ከተሞች የሚያገናኝ እና የሚያሰተሳሰር የመረጃ ቋት ዝርጋታ

ሥርዓት ተግባራዊ በማደረግ የመረጃዎች ወቅታዊነት ችግርና የመረጃ ጥራት ክፍተት በመቅርፍ ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ሊሠራ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ኘሮግራም አፈፃፀምን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላትና የክልል ከተሞች ወጥ የሆነና ጥራቱን እና ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት እንዲልኩ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግና በወቅቱ በማይልኩት ክልሎች እና ከተማ አሰተዳደሮች ለሚመለከተው ለበላይ አካል በማሰወቅ ችግሩ እንዲፈታ ሊያደረግና የተላኩ ሪፖርቶችን በመገምገም ወቅቱን የጠበቀ ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡


አባሪ 1

## የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር



አባሪ 2

**የሥራ ዕድል ፈጠራ ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት የላቀ ስዕላዊ መግለጫ /High level map**



## የአንድ ማዕከል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት የላቀ ስዕላዊ መግለጫ

ሁሉንም አገልግሎቶች ከአንድ ቦታ ይቅረብልኝ ጥያቄ/ ፍላጎት/ አቅጣጫ፣

⇓

የአንድ ማዕከላት ስታንዳርድ ማዘጋጀት

⇓

በክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ ሊተገበሩ የሚችሉ ዲዛይኖችን ማዘጋጀት

⇓

በዲዛይኑ መሰረት ግንባታዎች መካሄዳቸውን መከታተል

⇓

የአንድ ማዕከላትን በሰው ሃይል፣ በቁሳቁስ እና በስልጠና አቅማቸውን መገንባት

⇓

በአንድ ማዕከላት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ኦቶሜት ማድረግ


⇓

ማዕከላቱን በአፈፃፀማቸው መሰረት መለየትና እውቅና መስጠት


⇓

የረካ ተገልጋይና ባለድርሻ አካል፣


## የገበያ ልማትና ግብይት ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ ደረጃ የሥራ ፍሰት ማፕ/High Level Mapping/



## የከተሞች ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስተባበሪያ የስራ ፍሰት



**የኑሮ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት የላቀ ስዕላዊ መግለጫ**



አባሪ 3

## መመዘኛ መስፈርቶች

| ተ/ቁ | መመዘኛ መስፈርት | አስተያየት |
|---|---|---|
| 1. | ኤጀንሲው የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ ሥራዎችን ለማፋጠን የሚረዱ የህግ ማቀፎችንና ስትራቴጂዎችን ነድፎ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ሊያፀድቅ ሲጸድቅም አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 2 | ኤጀንሲው የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ የዘርፉን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 3 | ኤጀንሲው ከፌደራል እስከ ከተሞች የተናበበ አደረጃጀትና አሠራር ሥርዓቶችን በማዘጋጀት እና አጋርነት በመፍጠር የስትራቴጂው ማስፈፀሚያ ስልቶች እንዲፈጸሙ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 4 | ኤጀንሲው በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እያቻሉ ለማይሠሩ ሥራ ለሌላቸው ዜጐች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 5 | ኤጀንሲው አዋጭ የሆኑ የሥራ ዕድል አማራጮችን በጥናት በመለየት በየዘርፎቻቸው የሥራ ዕድል ፈጠራን ሥራ ሊያስተባብርና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 6 | ኤጀንሲው በሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች የሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ለተገልጋዮቻቸው ሁሉን አቀፍ አግልግሎቶች መስጠት እንዲያስችላቸው የአሰራርና አገልግሎት አሰጣት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅ እና በስታንዳርዱ መሠረት መተግበሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ | |
| 7 | ኤጀንሲው የሥራ ባህል እንዲጐለብትና እንዲዳብር በሥራ ፈጠራ ዙሪያ ያለውን የተዛቡ አመለካከቶች የሚለውጡ ሥራዎች ጉዳዩ በሚመለከታቸው ፈጻሚ አካላት መሠራታቸውን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 8 | ኤጀንሲው ከዩኒቨርስቲዎችና ከቴ/ሙያ ምሩቃንና ሌሎች ሥራ ፈላጊ ዜጐችን በትምህርት ደረጃ፣ በጾታ፣ በዕድሜ ለይቶ በትክክል ሊመመዝገብ ይገባል፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| 9 | ኤጀንሲው የሥራ ዕድል ለተፈጠረላቸው ዜጐች አገልግሎት የሚውሉ አዳዲስ የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ግንባታ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነው የለማ መሬት በወቅቱና በተፈለገው መጠን የተዘጋጀላቸው መሆኑን፤ እንዲሁም ግንባታቸው በተጠናቀቁ የማምረቻና መሸጫ ሕንጻዎችና ሼዶች ለተጠቃሚዎች ከመተላለፋቸው በፊት አስፈላጊው መሠረተ ልማቶች የተሟላላቸው መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 10 | ኤጀንሲው የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጐች በሚያገኙት ገቢ ቆጥበው ኢንተርፕራይዝ እንዲያቋቁሙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 11 | ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ሊነድፍ፣ መርሃ ግብሮችን ሊያዘጋጅ፤ ሲፈቀድም አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል | |
| 12 | ኤጀንሲው በክልልና ከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮጀክቶችን ለመመዘን የሚያስችሉ የአፈጻጸም መለኪያዎችን አዘጋጅቶ ለከተሞች በማሳወቅ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም በመለከኪያዎቹ መሠረት መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡ | |
| 13 | ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ በኑሮ ማሻሻያ ደረጃ የሚታቀፉ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ያሉባቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመለየት ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶችን ሊዘረጋ ይገባል | |
| 14 | ኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚውል ሀብት ከህብረተሰቡ፣ ከባለድርሻ አካላትና ከልማት አጋሮች እንዲሰባሰብና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ ሊያደረግ ይገባል፡፡ | |
| 15 | ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያሰችሉ ፕሮጀክቶችን የሚገመግምበት የግምገማ ሠነድ (Project appraisal Document) በማዘጋጀት ተግባራዊ መደረጉንና በሰነዱ መሠረት አፈፃፀማቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 16 | ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት የተጋለጡ እና ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት መሻሻሉንና የምግብ ዋስትናቸው መረጋገጡን ክትትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 17 | ኤጀንሲው በኑሮ ማሻሻያ ለሚታቀፉ ዜጎች በሚኖሩብት አከባቢ ምቹ አደረጃጀቶችን በመፍጠር በቀላሉ ገቢያቸውን ሊያሳድጉ የሚያስችላቸውን አሰራሮችን ሊዘረጋ እና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 18 | ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና የጋራ መድረክ በማዘጋጀት | |

| | | |
|---|---|---|
| | ከተሞች የእርስ በእርስ ልምድ ልውወጥ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ሊሠራ ይገባል፡፡ | |
| 19 | ኤጀንሲው ለዜጎች የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥ እና የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ከባለድርሻ አካላትና የዘርፉ አጋሮችን የትብብር መስኮችን በመለየት፣ የስምምነት ሰነዶችን በማዘጋጀት በጋራ ሊሠራ ፣አፈጻጸሙን ሊከታተልና ሊገመግም ይገባል፡፡ | |
| 20<br><br><br><br>21 | ኤጀንሲው ለዜጎች የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥላቸውና የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው በአስፈጻሚና በባለድርሻ አካላት የሚሰጠው ክትትልና ድጋፍ ዘላቂነት ያለው መሆኑን የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ሊከታተል ይገባል፡፡<br>ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸምን ውጤታማ ለማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ መፍትሄ የሚሹ የግብዓት ችግሮችን (ትራንስፖርት፣ ውሃ. መብራት፣ የመስሪያ ቦታ፣ የመሸጫ ቦታ፣ ጥሬ እቃ….) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ችግሩን ሊፈታ ይገባል፡፡ | |
| 22 | ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሥራ ፈላጊዎች እንደየ ፍላጐታቸውና ችሎታቸው የሚሠማሩበት የሥራ ዘርፎችን ፓኬጅ ቀርጾ ሊሠራ ይገባል፡፡ | |
| 23 | ኤጀንሲው ከሚዲያ ጋር በመቀናጀት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የሕዝብ መድረኮች በመፍጠርና የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም በከተሞች የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የሥራ ዕድል አፈጣጠር ላይ ተከታታይነት ያለው ግንዛቤ ሊሰጥ ይገባል፡፡ | |
| 24 | ኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትና እና የስራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ ማንዋሎችን በማዘጋጀት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላት፣ ለተገልጋዮች፣ ለባለድርሻ አካላትና ለማህበረሰቡ የትምህርትና የሥልጠና ስራዎችን በስፋት እንዲሰሩ የሚያግዝ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በከተሞች እንዲፈጠር ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 25 | ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና ኘሮግራም ተጠቃሚ ለሆኑ ዜጎች የስነ ልቦናና የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙና ተከታታይ የሆነ የአቅም ግንባታ ሥራ እንዲከናወን ማደረግ ይኖርበታል፡፡ | |
| 26 | ኤጀንሲው በከተሞች የምግብ ዋስትና መረጋገጥና የሥራ ዕድል ፈጠራ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ከላይ እስከታች ባሉ ከተሞች የመረጃ ልውውጡ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆን | |

| | | |
|---|---|---|
| | እንዲሁም መረጃዎች በጥራት እና በፍጥነት ለመሰብሰብ፣ ለመያዘና ለማሠራጨት የዳታቤዝ ልማት ሶፍትዌር በማልማት ሊሠራ ይገባል፡፡ | |
| 27 | ኤጀንሲው የከተሞች የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራም አፈፃፀምን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላትና የክልል ከተሞች ወጥ የሆነና ጥራቱን እና ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት እንዲልኩ ሊያደርግና የተላኩ ሪፖርቶችን ገምግሞ ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ | |

**አባሪ 4**

**በ5ቱ የስራ ዘርፎች ለመፍጠር የታቀዳው የስራ ዕድል እና የተፈጠረ የሥራ ዕድል ዝርዝር ማስረጃ ሠንጠረዥ 1**

| ተ.ቁ | | የሥራ ዘርፎች | በ2009 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | | በ2010 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% |
| 1 | አዲስ አበባ | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 41280 | 13408 | 32.48 | 21217 | 6563 | 30.93 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 51600 | 20006 | 38.77 | 79490 | 34783 | 44 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 37152 | 2988 | 8.04 | 11978 | 2167 | 18 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 41280 | 34835 | 84.39 | 26908 | 61755 | 230 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 35088 | 9729 | 27.73 | 21513 | 12306 | 57.20 |
| | | ድምር | 206400 | 80966 | 39.23 | 161106 | 117574 | 72.98 |
| 2 | ድሬደዋ | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 4902 | 4135 | 84.35 | 4797 | 3380 | 70.46 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 6128 | 11591 | 189.15 | 12332 | 12852 | 104.22 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 4412 | 672 | 15.23 | 958 | 433 | 45.20 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 4902 | 4255 | 86.80 | 2975 | 3472 | 116.71 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 4167 | 2548 | 61.15 | 2483 | 2303 | 92.75 |
| | | ድምር | 24511 | 23201 | 94.66 | 23545 | 22440 | 95.31 |
| 3 | አማራ | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 80742 | 32023 | 39.66 | 92863 | 37982 | 40.90 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 71510 | 59295 | 82.92 | 50198 | 59029 | 117.59 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 34434 | 19285 | 56.01 | 47230 | 19607 | 41.51 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 43765 | 45113 | 103.08 | 27336 | 52220 | 191.03 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 19660 | 31798 | 161.74 | 9748 | 33006 | 338.59 |
| | | ድምር | 250111 | 187514 | 74.97 | 227375 | 201844 | 88.77 |
| 4 | ደቡብ | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 77760 | 46027 | 59.19 | 57960 | 37679 | 65.01 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 47775 | 41595 | 87.06 | 50400 | 45869 | 91.01 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 39812 | 27454 | 68.96 | 45360 | 28241 | 62.26 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 39813 | 48956 | 122.96 | 55440 | 46059 | 83.08 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 31850 | 38643 | 121.33 | 42840 | 24682 | 57.61 |
| | | ድምር | 237010 | 202675 | 85.51 | 252000 | 182530 | 72.43 |
| 5 | ኦሮሚያ | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 77400 | 73457 | 94.91 | 87801 | 79044 | 90.03 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 96751 | 136678 | 141.27 | 40375 | 116120 | 287.6 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 69660 | 68745 | 98.69 | 50359 | 47620 | 94.56 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 77400 | 122302 | 158.01 | 97963 | 67447 | 68.85 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 65791 | 73410 | 111.58 | 86469 | 57940 | 67.01 |
| | | ድምር | 387002 | 474592 | 122.63 | 362967 | 368171 | 101.43 |
| 6 | ትግራይ | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 30960 | 26027 | 84.07 | 33134 | 17630 | 53.21 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 38700 | 39782 | 102.80 | 49700 | 23385 | 47.05 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 27864 | 17198 | 61.72 | 38104 | 15717 | 41.25 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 30960 | 49608 | 160.23 | 28164 | 23319 | 82.80 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 26316 | 31542 | 119.86 | 16567 | 15015 | 90.63 |
| | | ድምር | 154800 | 164157 | 106.04 | 165669 | 95066 | 57.38 |
| 7 | ሀረረ | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 1032 | 1073 | 103.97 | 900 | 572 | 63.56 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 1290 | 6248 | 484.34 | 4400 | 4806 | 109.23 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 929 | 283 | 30.46 | 600 | 154 | 25.67 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 1032 | 918 | 88.95 | 1920 | 966 | 50.31 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 877 | 425 | 48.46 | 2708 | 644 | 23.78 |
| | | ድምር | 5160 | 8947 | 173.39 | 10528 | 7142 | 67.84 |
| 8 | በንሻንጉል | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 3892 | 677 | 17.39 | 1036 | 390 | 37.64 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 1680 | 3708 | 220.71 | 1684 | 2260 | 134.20 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 785 | 1002 | 127.64 | 1684 | 739 | 43.88 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 1341 | 1778 | 132.59 | 1590 | 500 | 31.45 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 481 | 1365 | 283.78 | 700 | 495 | 70.71 |
| | | ድምር | 8179 | 8530 | 104.29 | 6694 | 4384 | 65.49 |
| 9 | ጋንቤላ | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 561 | 357 | 63.64 | 1312 | 1112 | 84.76 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 1593 | 1039 | 65.22 | 2214 | 1859 | 83.97 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 410 | 301 | 73.41 | 1230 | 1080 | 87.80 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 633 | 808 | 127.6 | 1558 | 1287 | 82.61 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 5 | | | |
| | | በንግድ ዘርፍ | 1357 | 974 | 71.78 | 1230 | 1641 | 133.41 |
| | | ድምር | 4554 | 3479 | 76.39 | 7544 | 6979 | 92.51 |
| 10 | ሶማሌ | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 5062 | 4312 | 85.18 | 2789 | 2427 | 87.02 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 3000 | 7000 | 233.33 | 5900 | 4675 | 79.24 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 1500 | 1078 | 71.87 | 6154 | 5231 | 85 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 2250 | 2700 | 120 | 9700 | 8245 | 85 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 1500 | 1802 | 120.13 | 5853 | 4976 | 85.02 |
| | | ድምር | 13312 | 16892 | 127 | 30396 | 25554 | 84 |
| 11 | አፋር | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 1032 | 164 | 15.89 | 301 | 1166 | 387 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 1290 | 781 | 60.54 | 480 | 1989 | 414 |
| | | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 400 | 312 | 78 | 300 | 1476 | 492 |
| | | በአገልግሎት ዘርፍ | 1032 | 395 | 38.28 | 1188 | 1666 | 140 |
| | | በንግድ ዘርፍ | 877 | 60 | 6.84 | 810 | 2028 | 250 |
| | | ድምር | 4631 | 1712 | 36.97 | 3079 | 8325 | 270 |

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሠንጠረዥ 2

| ተ.ቁ | የሥራ ዘርፎች | በ2009 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | | በ2010 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% |
| 1 | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 26916 | 15016 | 58 | 21217 | 6563 | 31 |
| 2 | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 4348 | 21655 | 50 | 79490 | 34783 | 44 |
| 3 | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 5176 | 3206 | 62 | 11978 | 2167 | 18 |
| 4 | በአገልግሎት ዘርፍ | 20708 | 35832 | 173 | 26908 | 61755 | 230 |
| 5 | በንግድ ዘርፍ | 7246 | 1247 | 172 | 21531 | 12306 | 57 |

በአጠቃላይ በ2009 በበጀት ዓመት ከአምስቱ ዘርፎች ውስጥ በሶስቱ ዘርፍ /በማኑፋክቸሪንግ፣ በኮንስትራክሽን፣ በከተማ ግብርና እና በንግድ ዘርፍ/ ዝቅተኛ አፈፃፀም መመዝገቡ እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት ከአምስቱ የሥራ ዘርፎች ውስጥ አንድ ዘርፍ /የአገልግሎት ዘርፍ/ ብቻ ከፍተኛ አፈጻጸም ሲያሳይ አራቱ ዘርፎች አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ መሆኑን ሪፖርታቸው ያሳያል፡፡

## የደቡብ ክልል የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሠንጠረዥ 2

| ተ.ቁ | የሥራ ዘርፎች | በ2009 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | | በ2010 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% |
| 1 | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 73760 | 46027 | 62 | 66424 | 37679 | 57 |
| 2 | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 47775 | 41595 | 87 | 57760 | 45869 | 79 |
| 3 | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 39812 | 27454 | 69 | 51984 | 35454 | 68 |
| 4 | በአገልግሎት ዘርፍ | 39813 | 48956 | 112 | 63536 | 46059 | 72 |
| 5 | በንግድ ዘርፍ | 31850 | 38643 | 121 | 490696 | 24682 | 50 |

የአማራ ክልል የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሠንጠረዥ 3

| ተ.ቁ | የሥራ ዘርፎች | በ2009 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | | በ2010 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% |
| ተ.ቁ | የሥራ ዘርፎች | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% |
| 1 | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 55478 | 15558 | 28 | 72546 | 16186 | 22 |
| 2 | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 60490 | 39339 | 65 | 37411 | 26159 | 70 |
| 3 | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 24820 | 16564 | 66.7 | 21295 | 16574 | 78 |
| 4 | በአገልግሎት ዘርፍ | 33935 | 26818 | 79 | 20763 | 30488 | 147 |
| 5 | በንግድ ዘርፍ | 14164 | 27116 | 191 | 9748 | 26563 | 272 |

በአጠቃላይ በ2009 በጀት ዓመት በዜጎች የሥራ እድል ፈጠራው በሶስቱ ዘርፎች /በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍና በከተማ ግብርና ዘርፍ/ አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ መሆኑ፣ እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሲሆን በኮንስትራክሽን ዘርፍ እና በከተማ ግብርና ዘርፍ በታቀደው ልክ አለመከናወኑን ከአፈፃፀሙ ለመረዳት ተችሏል፡፡

**የኦሮሚያ ክልል የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት**

**የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሠንጠረዥ 4**

| ተ.ቁ | የሥራ ዘርፎች | በ2009 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | | በ2010 በጀት ዓመት የታቀደና የተከናወነ የሥራ ዕድል ፈጠራ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% |
| ተ.ቁ | የሥራ ዘርፎች | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ% |
| 1 | በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ | 61920 | 30870 | 50 | 86703 | 79044 | 91 |
| 2 | በኮንስትራክሽን ዘርፍ | 62888 | 43150 | 68.6 | 40375 | 140295 | 347 |
| 3 | በከተማ ግብርና ዘርፍ | 55728 | 51235 | 92 | 37769 | 32897 | 87 |
| 4 | በአገልግሎት ዘርፍ | 61920 | 68058 | 100 | 97963 | 105588 | 108 |
| 5 | በንግድ ዘርፍ | 49343 | 57777 | 100 | 86469 | 57940 | 67 |

በአጠቃላይ የክልሉ የሥራ እድል ፈጠራ በ5ቱም ዘርፍ የ2010 በጀት ዓመት ጥሩ የሚባል ሲሆን የ2009 በጀት ዓመት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እና በኮንስትራክሽን ዘርፍ ዝቅተኛ አፈፃፀም ይታያል፡፡

## አባሪ 5

## በአማራ ክልል የ2009 በጀት ዓመት የመሬት አቀርቦትና አጠቃቀም ሠንጠረዥ 1

| ተ.ቁ | ዞን | የተዘጋጀ የለማ መሬት በካ.ሜ. | | | | ከተዘጋጀው መሬት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ለሼድ ግንባታ | ለክላስተር ግንባታ | ለከተማ ግብርና ግንባታ | ድምር | ለሼድ | ለክላስተር ግንባታ | ለከተማ ግብርና | ድምር |
| 1 | ጐንደር ከተማ | 198525 | 1500 | 1500 | 201525 | 960 | 1500 | 1500 | 3960 |
| 2 | ደሴ ከተማ | 67500 | 0 | 7320 | 74820 | 45111 | 0 | 7320 | 52431 |
| 3 | ባ/ዳት ከተማ | 58500 | 0 | 520514 | 579014 | 32249 | 0 | 148000 | 180249 |
| 4 | ሰሜን ጐንደር | 25544 | 0 | 397097 | 422641 | 14102 | 0 | 337954 | 352056 |
| 5 | ደቡብ ጐንደር | 57494 | 0 | 109174 | 166668 | 44756 | 0 | 57497 | 1021253 |
| 6 | ምዕ/ጐንደር | 71753 | 0 | 607922 | 679675 | 41514 | 0 | 136338 | 177852 |
| 7 | ምስ/ጐንደር | 80546 | 0 | 754939 | 835485 | 48813 | 0 | 639873 | 688686 |
| 8 | አዊብ/ሔ/አስ/ዞን | 41043 | | 334837 | 375880 | 40577 | 0 | 334837 | 375414 |
| 9 | ሰሜን ሸዋ | 148334 | 35642 | 269473 | 453449 | 194682 | 5520 | 213021 | 413223 |
| 10 | ኦሮሞ ብሔ/አስ/ዞን | 8157 | 0 | 149390 | 157547 | 4582 | 0 | 116390 | 120972 |
| 11 | ዋግኽምራ ብሔ/አስ/ዞን | 15455 | 0 | 13140 | 28595 | 5518 | 0 | 15527 | 21045 |
| 12 | ደቡብ ወሎ | 143932 | 0 | 839371 | 983303 | 73524 | 0 | 835705 | 909229 |
| 13 | ሰሜን ወሎ | 224969 | 20954 | 401208 | 647131 | 204450 | 11458 | 271023 | 486931 |
| | **ድምር** | **1141752** | **58096** | **4405885** | **5605733** | **750838** | **18478** | **3114985** | **3884301** |

ሠንጠረዥ 2

## በአማራ ክልል የ2010 በጀት ዓመት የመሬት አቀርቦትና አጠቃቀም

| | | የተዘጋጀ የከተማ መሬት በካ.ሜ. | | | ከተዘጋጀው የከተማ መሬት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ዞን | ለሼድ ግንባታ | ለከተማ ግብርና ግንባታ | ድምር | ለሼድ | ለከተማ ግብርና | ድምር |
| 1 | ጐንደር ከተማ | 401635 | 30401 | 432036 | 29204 | 37668 | 66872 |
| 2 | ደሴ ከተማ | 26523 | 4360 | 30883 | 5260 | 4360 | 9620 |
| 3 | ባ/ዳር ከተማ | 73226 | 564214 | 636440 | 62690 | 11824 | 74514 |
| 4 | ማዕከላዊ ጐንደር | 123624 | 601958 | 725582 | 57251 | 414762 | 472013 |
| 5 | ሰሜን ጐንደር | 8080 | 66508 | 74588 | 7044 | 38024 | 45068 |
| 6 | ደቡብ ጐንደር | 34613 | 10866219 | 10900832 | 6089 | 8383851 | 8389940 |
| 7 | ምዕ/ጐንደር | 79001 | 148166 | 227168 | 47047 | 103084 | 150131 |
| 8 | ምዕ/ጐጃም | 161993 | 366178 | 528171 | 89730 | 252942 | 342672 |
| 9 | ምስ/ጐጃም | 363415 | 1983585 | 2347000 | 332923 | 1396481 | 1729404 |
| 10 | አዊብ/ሔ/አስ/ዞን | 253625 | 309830 | 563455 | 121982 | 236390 | 358372 |
| 11 | ሰሜን ሸዋ | 1118646 | 592681 | 1711327 | 179340 | 218171 | 397511 |
| 12 | ኦሮሞ ብሔ/አስ/ዞን | 11002 | | 11002 | 11002 | | 11002 |
| 13 | ዋግኽምራ ብሔ/አስ/ዞን | 11520 | 4825 | 16345 | 11520 | 4825 | 16345 |
| 14 | ደቡብ ወሎ | 163659 | 1400898 | 1564557 | 127771 | 1378397 | 1415160 |
| 15 | ሰሜን ወሎ | 234183 | 338078 | 572261 | 122252 | 219576 | 341828 |
| | **ድምር** | **3064745** | **17277901** | **20342646** | **12111050** | **12700355** | **13911460** |

## አባሪ 6

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ10 ክፍለ ከተሞች ለምግብ ዋስትና ኘሮግራም /በአከባቢ ልማትና በቀጥታ ድጋፍ/ ተመዝግበው ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች

| ተ.ቁ | ክፍል ከተማ | የተሠጠ ኮታ | አባውራ/እማውራ ብዛት | | | የቤተሰብ ብዛት | | | የተጠቃሚ ብዛት | | | በአከባቢ ልማት | | በቀጥታ ድጋፍ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ከኮታ በላይ የተመዘገቡ | በኮታቸው ያልተመዘገቡ | ከኮታ በላይ የተመዘገቡ | በኮታቸው ያል ተመዘገቡ | ድምር |
| 1 | ጉለሌ | 14955 | 1733 | 4540 | 6273 | 7329 | 9582 | 16911 | 6340 | 8580 | 14920 | 39 | | | 4 | 43 |
| 2 | አቃቂ | 11017 | 1320 | 2479 | 3799 | 5174 | 6227 | 11401 | 4827 | 6189 | 11016 | 0 | | 1 | | 1 |
| 3 | ልደታ | 18894 | 1263 | 2534 | 3797 | 10172 | 12731 | 22903 | 8225 | 10747 | 18972 | 40 | | | 118 | 158 |
| 4 | ንፋስ ስልክ | 8784 | 628 | 2298 | 2926 | 4585 | 5626 | 10211 | 3907 | 4878 | 8785 | 0 | | | 1 | 1 |
| 5 | አዲስ ከተማ | 22136 | 1349 | 4513 | 5862 | 11926 | 15655 | 275811 | 9270 | 12421 | 21691 | | 344 | 789 | | 1133 |
| 6 | አራዳ | 8809 | 814 | 2170 | 2984 | 4466 | 5983 | 10449 | 3627 | 5202 | 8829 | | 25 | 4 | | 29 |
| 7 | ቦሌ | 781 | 50 | 179 | 229 | 385 | 483 | 868 | 335 | 446 | 781 | 0 | | 0 | | 0 |
| 8 | ቂርቆስ | 14495 | 1186 | 2466 | 3652 | 5557 | 6913 | 12470 | 4460 | 6213 | 10673 | 2907 | | 915 | | 3822 |
| 9 | ኮልፌ | 10012 | 730 | 2171 | 2901 | 5898 | 7503 | 13401 | 3992 | 5037 | 9029 | 467 | | 516 | | 983 |
| 10 | የካ | 14336 | 1182 | 3818 | 5000 | 4930 | 6555 | 11485 | 6201 | 8235 | 14436 | | 365 | | 35 | 400 |
| | **ድምር** | **123918** | **10255** | **27168** | **37423** | **60422** | **77258** | **137680** | **51184** | **67948** | **119132** | **3453** | **734** | **2225** | **158** | **6570** |